ውሱን

# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር
# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ማቋቋም አስፈላጊነትና አፈጻጸም
## (ረቂቅ)

አዲስ አበባ
ህዳር 1992

መኩ/ባስ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር
የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ማቋቋም አስፈላጊነትና አፈጻጸም

(ረቂቅ)

አዲስ አበባ
ህዳር 1992

# ማውጫ


ምዕራፍ 1 በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ማቋቋም አስፈላጊነት ........ 1

1.1 መግቢያ ........ 1
1.2 የዚህ ዶክመንት ዓላማ ........ 3
1.3 ወሳኝ ኩነቶች ........ 4
1.4 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ትርጉም ........ 5
1.5 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ተግባር ........ 6
1.6 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጥቅም ........ 8
1.7 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ታሪካዊ አመሠራረት ........ 10
1.8 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አሁን ያለበት ሁኔታ ........ 12
1.9 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሁኔታ በኢትዮጵያ ........ 14

ምዕራፍ 2 የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት አጠቃላይ ይዘትና አፈጻጸም ........ 17

2.1 የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ዓላማ ........ 17
2.2 የሚመዘገቡ ወሳኝ ኩነቶች ዓይነትና ትርጉም ........ 17
2.3 የወሳኝ ኩነቶች አስመዝጋቢ ........ 19
2.4 የወሳኝ ኩነቶች መዝጋቢ ........ 20
2.5 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አፈጻጸም ........ 21

2.6 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ቦታ ............................ 22
2.7 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽህፈት ቤት........................ 23
2.8 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የጊዜ ገደብ ...................... 23

2.9 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባን በጊዜ አለማስመዝገብ የሚያስከትለው ቅጣት ...................................................24
2.10 የወሳኝ ኩነቶች መረጃዎች ሚስጥራዊነት.................................................25
2.11 ወሳኝ ኩነቶች ማረጋገጫ ..................................25
2.12 የወሳኝ ኩነቶች ዶክሜንቶች እርማት ..........................................................26
2.13 የወሳኝ ኩነቶች መዝገቦች አያያዝና አጠባበቅ ..............................................27
2.14 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የሰው ኃይልና ሥልጠና...................................................30
2.15 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሎጀ ስቲክ ክፍል ............32
2.16 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ............................................32
2.17 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሂደት ግመገማ ...................33
2.18 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በጀት ................................35

ምዕራፍ 3 የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ዶክሜንቶች..............................37

3.1 የወሳኝ ኩነቶች መዝገቦች ...................................37
3.2 የወሳኝ ኩነቶች ምስክር ወረቀቶች ..........................45
3.3 የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሪፓርት ቅጽ ............48

3.4 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ መመሪያ ........................55

ምዕራፍ 4 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅር ........................................62

4.1 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅር ዓይነቶች ........................62

4.2 የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅር ዓይነቶች ........................................ 69

4.3 በኢትዮጵያ የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ድርጅታዊናአስተዳደራዊ መዋቅር .................... 78

ምዕራፍ 5 የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ተባባሪ ድርጅቶችና አስተባባሪ ኮሚቴዎች ................................ 89

5.1 የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ተባባሪ ድርጅቶች ........................................ 89

5.2 የተባባሪ ድርጅቶች ዋናዋና ተግባርና ኃላፊነት ........................................ 90

5.3 አስተባባሪ ኮሚቴዎችና ተግባራቸው .................... 97

ምዕራፍ 6 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና
ስታቲስቲክስ ሕግ አስፈላጊነት.................... 99

6.1 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሕግ ይዘት ..................... 101
6.2 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና አገራዊና
አለም አቀፍ ሕጎች ........................................... 102
6.3 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት
ሕግ ማን ያውጣ? .............................................. 110

Bibiliography........................................................ 114

መዝገቦች

የልደት መዝገብ ..............................................41
የሞት መዝገብ..................................................42
የጋብቻ መዝገብ ..............................................43
የፍቺ መዝገብ ................................................44

ሰርቲፊኬቶች

የልደት ሰርቲፊኬት ..........................................49
የሞት ሰርቲፊኬት ............................................50
የጋብቻ ሰርቲፊኬት..........................................51
የፍቺ ሰርቲፊኬት ............................................52

## ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጾች

የልደት ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ ........................................57
የሞት ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ ........................................58
የጋብቻ ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ ........................................59
የፍቺ ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ ........................................60

# ምዕራፍ 1

## በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ማቋቋም አስፈላጊነት

### 1.1 መግቢያ

የሕዝብ ቆጠራና የሥነ-ሕዝብ የናሙና ጥናቶች ለኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊና ሥነ ሕዝባዊ ዕቅድ አውጪዎች መሠረታዊ የመረጃዎች ምንጭ በመሆን ያገለግላሉ። የሕዝብ ቆጠራ በየ10 ዓመቱ የሚካሄድ ሆኖ የአንድን አገር ወይም የተወሰነ ክልል መረጃ ሲሰጥ የናሙና ጥናት ደግሞ በናሙና በተመረጡ ቦታዎች መረጃ የማግኛ ዘዴ ነው። ሆኖም ሁለቱም የመረጃ ምንጮች የየዓመቱን የሕዝብ ብዛትና የዕድገት መጠን መረጃ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ አይሰጡም። ከዚህም በላይ የሚሰበሰቡት የኩነቶች መረጃ ኩነቶቹ እንደተከሰቱ ሳይሆን ከተከሰቱ ከረጂም ጊዜ በኋላ የሚሰበሰቡ በመሆኑ እንደሚፈለገው ጥራታቸው አስተማማኝ ሊሆን አይችልም። በመሆኑም የመረጃውን ሽፋንና ጥራት ለማሻሻል የተለያዩ ቴክኒኮችን በመጠቀም ልዩ ልዩ የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ዕድገት አመልካቾች ግምቶችን ማግኘት አስፈላጊ ሆኖአል።

በሕዝብ ቆጠራና በናሙና ጥናት በየዓመቱ ስንት ልጅ እንደተወለደ፣ ስንት ሰው እንደሞተ፣ ስንት ጋብቻዎች እንደ ተፈፀሙና ስንት ግለሰቦች ወይም ቤተሰቦች እንደ ፈለሱ የሚያመለክት መረጃ ማግኘት አይቻልም። እነዚህ መረጃዎች ደግሞ የአሁኑና የወደፊቱን የሕዝብ ብዛት ዕድገት ለማወቅ ወሳኝ ናቸው። ማንኛውም የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕቅዶች ዓላማ የህብረተሰቡን ዕድገት ለማሻሻል እስከሆነ ድረስ

የየዓመቱ፣ የሥነ ሕዝብ በተለይም የወሳኝ ኩነቶች መረጃን በጥራት ማግኘት አማራጭ አይኖረውም::

ሌላው በሕዝብ ቆጠራና በናሙና ጥናት የሚገኙ መረጃዎች ለስታቲስቲክስና ለአስተዳደር አገልግሎት ብቻ ከመዋል ባሻገር የግለሰቦችን ሕጋዊ ሰውነትና ማንነት የሚገልፁ ሕጋዊ መረጃዎችን ለመስጠት አያገለግሉም::

፡አንድ ጠብረተሰብ ከኢኮኖሚው፣ ማህበራዊውና ፖለቲካዊው እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ መልኩ በግለሰቦችና በግለሰቦች፣ በግለሰቦችና በድርጅቶች፣ በግለሰቦችና በመንግሥታዊ ተቋሞች፣ በግለሰቦችና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች መካከል ቀጥታ ግኑኝነቶች ይፈፀማሉ:: ለነዚህ ግኑኝነቶች ተፈጻሚነት የግለሰቦችን ማንነትና ሕጋዊ ሰውነት የሚያረጋግጡ ሕጋዊ ምስክር ወረቀቶች ተፈላጊነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ከመምጣቱ ባሻገር በተለያዩ አካባቢዎች የወቅቱ ዋንኛ ጥያቄ በመሆን ላይ ይገኛሉ:: ምክንያቱም የሕጋዊ ምስክር ወረቀቶች መኖር በኢኮኖሚው፣ በማህበራዊውና በፖለቲካው መስክ ሕጋዊ ጥያቄዎችን ለመመለስ ከፍተኛ ጠቀሜታ በመኖሩ ነው::

ሌላው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አስፈላጊነት እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ የተለያዩ የአለም አቀፍ ሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ ሕጐችን ከተቀበሉት አገሮች አንዷ ነች:: በሕገ መንግሥቱም ሆነ በአለም አቀፍ ሕጐች የፀደቀውን የግለሰቦችን ሰብአዊ መብት ለማስጠበቅ የግለሰቦችን ማንነት ሕጋዊ ሰውነት የሚገልፅ መረጃ (ምስክር ወረቀት) አስፈላጊ ይሆናል::

በመሆኑም ከላይ በጥቅሉ የተዘረዘሩትን ሕጋዊ፣ አስተዳደራዊ፣ ስታቲስቲካዊና የግለሰቦችን ማንነት የሚገልፅ ሕጋዊ መረጃ ሊገኝ የሚችለው በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ነው::

ስለዚህ ሥርዓቱን የመዘርጋት አስፈላጊነት አጠያያቂ አይሆንም።

## 1.2 የዚህ ዶክመንት ዓላማ

የዚህ ዶክመንት ዋና ዓላማ በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ሲቋቋም በቅደም ተከተል መከናወን ያለባቸውን ቴክኒካል ተግባራትንና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባን አስመልክቶ በሚቀረፀው ሕግ ውስጥ መካተት ያለባቸውን ተግባራት ለማመልከት ነው።

ይህ ዶክሜንት በ6 ምዕራፎች የተከፈለ ነው። ምዕራፍ 1 መግቢያ ሲሆን በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ማቋቋም አስፈላጊነት፣ የወሳኝ ኩነቶች ምንነት፣ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ትርጉም፣ ተግባር፣ ጥቅምና ታሪካዊ አመሰራረት ይገልፃል። ምዕራፍ 2 በኢትዩጵያ የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት አጠቃላይ ይዘትና አፈፃፀምን ያብራራል። ምዕራፍ 3 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ዶክሜንቶችና ይዘታቸው ይዘረዝራል። ምዕራፍ 4 በኢትዩጵያ የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት የሚኖረውን ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅር አማራጮችን ያመለክታል።።። ምዕራፍ 5 የሚቋቋመው የምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ተባባሪ ድርጅቶችንና የአስተባባሪ ኮሚቴዎችን ኃላፊነትና ተግባር ይገልፃል። በምዕራፍ 6 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሕግ፣ የሕጉ ይዘትና እንዲሁም ሌሎች ከምዝገባው ሥርዓት ጋር ግንኙነት ያላቸው ሕጎች ተመልክተዋል።

## 1.3 ወሳኝ ኩነቶች

ወሳኝ ኩነቶች የሚባሉት ልደት፣ ሞት፣ ጋብቻና ፍቺ ናቸው። ወሳኝ የተባሉበትም ዋናው ምክንያት የአንድን ሀገር ሕዝብ ብዛትና ዕድገት ስለሚወስኑ፣ ለሕብረተሰቡ እድገት ለሚከናወነው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ዕቅዶችንና በሕገ መንግሥትና በዓለም አቀፍ ሕጎች መሠረት የግለሰቦችን ሰብዓዊ መብቶችን ተፈጻሚ ለማድረግ ወሳኝ የመረጃ ምንጭ በመሆናቸው ነው።

ልደትና ሞት የሕዝብ ብዛትንና ዕድገትን በቀጥታ ይወስናሉ። ይኸውም የሕዝቡ ቁጥር እየጨመረ፣ እየቀነሰ ወይም ባለበት ሊቆይ የሚችለው በየዓመቱ በሚከናወነው ልደትና ሞት መካከል ባለው ልዩነት መጠን ነው። በየዓመቱ የሚወለደው ከሚሞተው የበለጠ፣ ያነሰ ወይም እኩል ከሆነ የሕዝቡም ብዛት በዚያው መሠረት እየጨመረ፣ እየቀነሰ ወይም ባለበት ይቆያል።

ጋብቻና ፍቺ የሕዝብን ብዛትና ዕድገትን በተዘዋዋሪ መንገድ ይወስናሉ። ይኸውም ጋብቻ የቤተሰብ መሠረት ነው። ከጋብቻ ውጭ ልጆች መውለድ ተቀባይነት በሌለበት ሕብረተሰብ አብዛኛው የሚከሰተው ልደት በጋብቻ ወይም ቤተሰብ ከተመሠረተ በኋላ ነው። በመሆኑም ህብረተሰቡ ራሱን እየተካ የሚሄደው ጋብቻን በመመሥረት ይሆናል። ፍቺ የቤተሰብ መፍረስን ያስከትላል። የፍቺ ቁጥር በሚበዛበት አካባቢ በየዓመቱ የሚከሰተው የልደት ቁጥር አነስተኛ ይሆናል። የሕዝብ ብዛት እድገትም በዚያው መጠን አነስተኛ ይሆናል።

## 1.4 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ትርጉም

### 1.4.1 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ትርጉም

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ማለት ተከታታይ፣ ቋሚና አስገዳጅ የሆነ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍቺ ኩነቶችንና ከኩነቶቹ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ግለሰቦች የሚመለከቱ ሥነ-ሕዝብ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ባህሪያትን ጭምር መመዝገብ ነው። በዚህ ትርጉም መሠረት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሦስት ባህርያት አሉት። እነሱም ተከታታይነት፣ ቋሚነትና አስገዳጅነት ናቸው።

ተከታታይነት፡- ተከታታይነት የሚያመለክተው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አንዴ ከተጀመረ መቋረጥ የሌለበት መሆኑን ነው። ይኸውም ማንኛውም ወሳኝ ኩነት እንደተከሰተ መመዝገብ አለበት። ምዝገባውም አንዴ ከተጀመረ በተከታታይ መቀጠል አለበት።

ቋሚነት፡- ቋሚነት የሚያመለክተው አንድ በቋሚነት የወሳኝ ኩነቶችን ምዝገባ የሚያካሂድ ሴርቲፊኬቶችን የሚሰጥና ስታቲስቲካዊ መረጃ የሚያዘጋጅ በሕግ የተቋቋመ ድርጅት መኖር እንዳለበት የሚገልፅ ነው። ይህ ተቋም የሚመሠረተው በምዝገባው ሕግ መሠረት ይሆናል።

አስገዳጅነት፡- አስገዳጅነት የሚያመለክተው ዜጎች መብቶቻቸውን ለማስከበርና የሚጠበቅባቸውን ግዴታ ለመወጣት በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሕግ መሠረት የመመዝገብ የዜግነት ግዴታ እንዳለባቸው ነው። አስገዳጅነት ቀደም ብሎ ለተገለፁት ማለት ለተከታታይነትና ለቋሚነት በትክክል ለመተግበር አስፈላጊ መሣሪያ ነው። በመሆኑም ሕጉ ማን ምን ማስመዝገብ እንዳለበት፣ የምዝገባው የጊዜ

ገደብ ምን ያህል መሆን እንዳለበት፣ በሕጉ መሠረት የማያስመዘግቡ እንደሚቀጡ ይደነግጋል። ያለእነዚህ ደንቦች አስገዳጅነት-ትርጉም የለውም።

### 1.3.2 የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ትርጉም

ስታቲስቲክስ ማለት የሕብረተሰብን ኤኮኖሚያዊ፣ ሥነ ሕዝብ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎችን የሚያመለክቱ አሀዛዊ መረጃዎችን በሣይንሣዊ መንገድ መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማጠናቀርና ውጤቱን ለኢኮኖሚያዊና ለማህበራዊ እቅድ ዝግጅት ለተመራማሪዎችና ለሌሎች መረጃ ተጠቃሚዎች የማሠራጨት ተግባር ነው።

በዚህ መሠረት የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ማለት አጠቃላይ የወሳኝ ኩነቶችን ብዛት፣ የኩነቶችንና ከኩነቶች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ግለሰቦች የሚመለከቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ሥነ ሕዝብና ማህበራዊ ሁኔታዎችን ሊያመለክቱ የሚችሉ አሀዛዊ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማጠናቀርና ውጤቱን ለኤኮኖሚያዊና ለማህበራዊ ዕቅድ አዘጋጆች ለተመራማሪዎችና ለሌሎች መረጃ ተጠቃሚዎች የማሠራጨት ተግባር ነው።

## 1.5 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ተግባር

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሁለት ተግባሮች ይኖሩታል። እነሱም ሕጋዊና ስታቲስቲካዊ ተግባሮች ናቸው።

### 1.5.1 ሕጋዊ ተግባር

ዛሬ ግለሰቦች (ባደጉትም ሆነ በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች) ከፍተኛና የተወሳሰቡ ግንኙነቶችን እርስ በርስ፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር

ያከናውናሉ። ለእነዚህ ግንኙነቶች ተፈፃሚነት የግለሰቦችን ማንነት የሚገልፁ ሕጋዊ ፅሁፎች ያስፈልጋሉ። የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ህጋዊ ተግባር እነዚህን ህጋዊ ፅሁፎችን (ምስክር ወረቀቶችን) ማዘጋጀት ነው።

የምዝገባው ሕጋዊ ተግባር በዚህ ብቻ አይወሰንም። በአንዳንድ ሀገሮች የምዝገባውን ሥራና አገልግሎት ሰፋ አድርጎ በመመልከት መዝጋቢው ባለው ሥልጣን ሌሎች ሕጋዊ ሥልጣኖችም ሊኖሩት ይችላሉ። እነዚህም ለምሳሌ ጋብቻን በተመለከተ ጋብቻው የተፈፀመው መሟላት ያለባቸውን ጉዳዮች ተሟልተው የተፈፀመ መሆኑን የመመርመርና ካልተሟሉ ጋብቻውን ውድቅ ለማድረግ የሚችልበት ሥልጣንም ይኖረዋል። ለምሳሌ በ1952 ፍትሐ ብሔር ሕግ በገጽ 127 በቁጥር 600 ጋብቻ እንዳይፈፀም ስለመከልከል «በንዑስ ቁጥር 2» ጋብቻውን የሚከለክል ነገር ቢኖር የተወሰነ ወይም እርግጠኛ ምክንያት መኖሩን የክብር መዝገብ ሹም የተረዳ እንደሆነ ጋብቻው እንዳይፈፀም ይከለክላል ይላል። በዚህ መሠረት የምዝገባው ሕጋዊ ተግባር ምዝገባ ማካሄድና ሰርተፊኬት መስጠት ብቻ ሣይሆን ራሱ ጋብቻው በትክክል ተፈጽሟል ብሎ የመቀበል ወይም ያለመቀበል ሥልጣንንም ያጠቃልላል።

### 1.5.2 ስታቲስቲካዊ ተግባር

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ እንደተባበሩት መንግሥታት አመለካከት የአንድ ሀገር የሥነ ሕዝብ መረጃ የጀርባ አጥንት ነው። በዚህ መሠረት የተመዘገቡት የወሳኝ ኩነቶች ብዛትና ከነሱ ጋር ግኑኝነት ያላቸው የሕዝብ መረጃዎች ለኢኮኖሚያዊና ለማህበራዊ ዕድገት ዕቅድ ለማዘጋጀት ይጠቅማሉ።

የምዝገባውን ስታቲስቲካዊ ተግባር በተመለከተ የወሳኝ ኩነቶችን ብዛትና ከወሳኝ ኩነቶች ጋር ግኑኝነት ያላቸውን ግለሰቦች የሚመለከቱ ሥነ ሕዝብ፡ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መረጃዎችን መዝግቦ በወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሪፓርት ቅጽ ሞልቶ ወደ ወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ጽ/ቤት መላክ ነው።

## 1.6 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጥቅም

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሦስት የተለያዩ ጥቅሞች አሉት። እነሱም አስተዳደራዊ፡ ሕጋዊና ስታቲስቲካዊ ናቸው።

### 1.6.1 አስተዳደራዊ ጥቅም

በሕብረተሰቡ ውስጥ በየዓመቱ የሚወለዱትን ሕፃናት፡ የሚሞቱትን ሰዎች፡ የጋብቻዎችንና የፍቺዎችን ብዛት ማወቅ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ ጥቅሞች ይሰጣል። የእናቶችንና የሕጻናትን ጤንነት ለመጠበቅ አስፈላጊውን ዝግጅት ለማድረግ፡ የአስተማሪዎችንና የትምህርት ቤቶችን ብዛት ለመተመንና ብሎም አስተማሪዎችን ለማሠልጠንና ት/ቤቶችን ለማሠራት ለማዘጋጀት፡ የጤና ተቋሞችንና ሐኪሞችን ለማዘጋጀት፡ አስፈላጊውን መድኃኒት ለማምረትና ለማሠራጨት፡ መኖሪያ ቤቶችን ለመሥራት ሌሎችን አስፈላጊና መሠረታዊ የሆኑትን እንደ ምግብና ልብስ የመሳሰሉትን በዕቅድ ለማምረትና ለማቅረብ ይጠቅማል።

### 1.6.2 ሕጋዊ ጥቅም

የሰዎች የልደት ጊዜ፡ ከማን እንደተወለዱ፡ የት እንደተወለዱ፡ የጋብቻ ሁኔታቸውን ... ወዘተ የሚያመለክት መረጃ ለትምህርት፡ ለጋብቻ፡ ለውርስ፡ ለኢንሹራንስ፡

ለመምረጥ፣ ለመመረጥ፣ ለጡረታና እንዲሁም ለውትድርና አገልግሎት እንዲመለመሉ ይጠቅማል። እነዚህን መብቶችና ግዴታዎች ከምዝገባ ጽ/ቤት በሚሰጣቸው ሕጋዊ የምስክር ወረቀት መሠረት ያስከብራሉ።

እንዲሁም የአንድ ሰው መሞት በሕጋዊ መንገድ ታውቆና ተመዝግቦ የሚያስገኘው ሕጋዊ ምሥክር ወረቀት የሟች ዘመዶች ውርስ፣ ኢንሹራንስ፣ ጡረታ ... ወዘተ በማግኘት ረገድ ይጠቅማሉ።

ሕጋዊ ጋብቻ በወቅቱ ከተመዘገበ ለተጋቢዎች የምስክር ወረቀት ያስገኛል። የምሥክር ወረቀቱም በጋብቻ ላይ ለሚነሱት ክርክሮች እንደ ማስረጃ ያገለግላል። ከሁለቱ ተጋቢዎች የሚወለዱት ልጆች የወላጆችን እንክብካቤ የማግኘት መብታቸው እንዲጠበቅ ከማድረጉም በላይ ለውርስ፣ ለኢንሹራንስ ... ወዘተ መብቶች ማስከበሪያ ሕጋዊ መረጃ ይሆናል።

በተመሣሣይ ሁኔታ በሕጋዊ መንገድ የተፈፀመ ፍች በወቅቱ ከተመዘገበ የምስክር ወረቀት ያስገኛል። የምስክር ወረቀቱም የሕጋዊና የመብት ጥያቄዎችን ለመፍታት እንደ ሕጋዊ መረጃ ያገለግላል። ለምሳሌ ከሁለቱ ተፋቺዎች መካከል አንዱ ሌላ ባል/ሚስት ለማግባት ቢፈልግ የማግባት መብታቸውን ለማስከበር ይረዳል።

### 1.6.3 ስታቲስቲካዊ ጥቅም

ከምዝገባው በተገኘው ስታቲስቲካዊ መረጃ መሠረት የሕዝቡን ብዛትና ስርጭት፣ ሕዝቡን በዕድሜና በፆታ በመከፋፈል ለትምህርት፣ ለሥራ፣ ለጡረታ፣ ለጋብቻ፣ ለመምረጥ፣ ለመመረጥ፣ ለውትድርና አገልግሎት ብቁ የሆኑትን ብዛት ለማወቅ ይጠቅማል። ከላይ የተጠቀሱትን

መረጃዎች መሠረት በማድረግ አስፈላጊውን ዕቅድ ለመንደፍ ይጠቅማል። በሌላ አንገር በየዓመቱ የሚወለዱትንና የሚሞቱትን ግለሰቦች ብዛት መሠረት በማድረግ የየዓመቱን የሕዝቡን ብዛት ዕድገት ምጣኔ ለማወቅና ብሎም የወደፊቱን የሕዝብ ብዛት ለመተንበይ ይጠቅማል።

እንዲሁም ሴቶች በዕድሜአቸው ስንት ልጆች እንደሚወልዱ በማወቅና ይህንን መሠረት በማድረግ የሥነ ሕዝብ ፓሊሲን ለመንደፍ፣ ዕቅድ ለማዘጋጀትና ውጤቱን ለመከታተል፣ እንዲሁም የቤተሰብ ምጣኔን በማስተማር ከሚፈለገው በላይ የሆነ የሕዝብ ብዛት ዕድገትን ለመግታት ይጠቅማል።

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ለማህበራዊ ተመራማሪዎች የሚጠቅም መሠረታዊ መረጃ ያቀርባል። በተለይ ለሶሾሎጂስቶችና ለስነ ሕዝብ ተመራማሪዎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ያስገኛል። ከምዝገባው የሚገኙት መረጃዎች እንደ ማህበራዊ ዕድገት አመልካቾች በመሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚከሰተውን የሕዝብ ብዛት ዕድገትና ለውጥ ለመገምገምና የተለያዩ የአስተዳደር ክፍሎችን በነዚህ አመልካቾች መሠረት በማወዳደር አስፈላጊውን የማሻሻያ ዕቅድ እንዲዘጋጅ ይረዳል።

## 1.7 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ታሪካዊ አመሠራረት

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ከክርስቶስ ልደት በፊት በግብፅ፣ በግሪክና በሮም በመንግስት ደረጃ ለገቢ ማስገኛ ምንጭና ለውትድርና አገልግሎት የሚውሉ ግለሰቦችን ለመመልመል ተብሎ ይከናወን ነበር።

ሆኖም የወሳኝ ኩነቶች ማስታወሻዎች መያዝ በመጀመሪያ ጊዜ ጽንሰ ሃሳቡ የፈለቀው በቤተ ክህነት ነበር። ቤተ ክህነት

ምዝገባውን ያካሂድ የነበረው የሕጻናትን ጥምቀት፣ የቀብርንና የሠርግን ስነ ስርዓቶች ለማስፈፀም ነበር።

እ.ኤ.አ. በ720 ከክርስቶስ ልደት በኋላ በጃፓን ውስጥ በተወሰኑ ቀበሌዎች የልደት፣ የሞትና የጋብቻ ምዝገባ ይካሄድ እንደነበር ይነገራል። ነገር ግን ምዝገባው ለሃይማኖታዊ ወይም ለሕብረተሰቡ የሚጠቅም ጉዳይ ማከናወኑ አይታወቅም።

ከ15ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በአውሮፓ በተለይ በስፓኝ ውስጥ በየቤተክርስቲያኑ ቀደም ብሎ ይካሄድ የነበረው ምዝገባ ተሻሽሎ ዘመናዊ መልክ ያዘ። እ.ኤ.አ በ1538 በእንግሊዝ አገር ውስጥ የነበሩት ቀሳውስት በየቤተክርስቲያኑ የሚጠመቁ ሕጻናት፣ የሚጋቡ ሰዎችና የሚቀበሩ ሙታን መመዝገብ እንዳለባቸው ለጳጳሱ ትዕዛዝ ተላለፈ። ከአንድ ዓመት በኋላ ማለት በ1539 ደግሞ በፈረንሳይ አገር ውስጥ ስለ ጥምቀት፣ ሠርግና ቀብር በየቤተክርስቲያኑ ተመሳሳይ ምዝገባ እንዲጀመር ተደረገ። እንዲሁም በ17ኛው ክፍለ ዘመን በሌሎች ሀገሮች ማለት በሲዊዲን /በ1608/፣ በካናዳ /በ1610/፣ በፊንላንድ /በ1628/ እና በዴንማርክ /በ1614/ በየአድባራትና በየቤተክርስቲያኑ የልደት፣ የጥምቀት፣ የሠርግና የቀብር ስነ ስርዓት እንዲመዘገብ ተደረገ።

ቀጥሎም እ.ኤ.አ. በ1639 የታላቋ ብሪታኒያ ግዛት በነበሩት በማሳቹሴትስና በፕላይማውዝ አስተዳደር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ተጀመረ። የሚመዘገቡት ኩነቶች የመንግስት መደበኛ ሠራተኞችን የሚመለከቱ ብቻ ነበሩ። በሚቀጥሉትም ዘመናት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በመንግስት ደረጃ ስለታሰበበት ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል እንዲያጠቃልል ተደረገ።

ከዚያም እ.ኤ.አ. በ1804 በንጉስ ናፖሊዮን አማካይነት በወጣው የፈረንሳይ ሕገ መንግስት ውስጥ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባን በሚመለከት አንድ ክፍል በተብራራ ሁኔታ ተጨመረ:: በዚህ አዋጅ ውስጥ ኩነቱን ማስመዝገብ ግዴታ መሆኑ፣ ማን እንደሚያስመዘግብ፣ ምን መመዝገብ እንዳለበት .... ወዘተ ተብራርቷል:: በተጨማሪም እያንዳንዱ ሰው ሕጋዊና ሰብዓዊ መብቱ ሊጠበቅለት የሚችለው የወሳኝ ኩነቱን እንደተከናወነ ሲያስመዘግብ ብቻ ነበር:: በናፖሊዮን ሕገ መንግስት ውስጥ የተጠቀሱት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ደንቦችን ብዙ የምዕራብ አውሮፓ፣ የላቲን፣ የመካከለኛው ምሥራቅና የአፍሪካ (ኢትዮጵያን ጨምሮ) ሀገሮች ገልብጠው በህጋቸው አካተውታል::

በመጨረሻም እ.ኤ.አ. ከ1839 ጀምሮ ዊልያም ፋር የተባለ የእንግሊዝ ተወላጅ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አሁን ባለው መልኩ በለሙ አገሮች እንዲስፋፋ አደረገ:: ይህ ሰው ለአርባ ዓመታት ያህል በዚሁ ሥራ ተሰማርቶ በቆየበት ጊዜ ስለምዝገባው ጉዳይ ጠለቅ ያሉ ጥናቶችን አካሂዶ ምዝገባው እንዴት ሊሻሻል እንደሚችል ብዙ ዘዴዎችን ለ20ኛው ክፍለ ዘመን ለጤናና ለሕዝብ ባለሙያዎች አበርክቶአል:: በተጨማሪም እሱ ያወጣቸው የአመዘጋገብ ዘዴዎችን መሠረት በማድረግ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አሁን ወደ ሚገኝበት ሳይንሳዊ ደረጃ ሊደርስ ችሎአል::

## 1.8 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አሁን ያለበት ሁኔታ

በአሁኑ ጊዜ ያለውን የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሁኔታ በአደጉትና በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ከፍሎ ማየት ይቻላል::

ባደጉትና በተለይ አነስተኛ የሕዝብ ቁጥር ባላቸው ሀገሮች የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ዋናው የሥነ-ሕዝብ መረጃ ምንጭ

በመሆን ያገለግላል። የህብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ከፍተኛ ደረጃ በመድረሱና በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የሚገኙት መረጃዎች ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳይ፣ ለግለሰብ፣ ለህብረተሰብ፣ ለአስተዳደርና ለሕግ መድረኮች እንደ ማስረጃነት ማገልገላቸውና በከፍተኛ ደረጃ በመፈለጋቸው የሚሰጡት ጥቅም ከፍተኛ ነው። በመሆኑም የመረጃዎች አመዘጋገብ በሰው ኃይል ከመሠራት አልፎ በኮምፒዩተሮች በመጠቀም በመሆኑ የመረጃዎቹ አስተማማኝነት ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ መሆኑ ይታወቃል። ለዚህም ኖርወይ፣ ዴንማርክ፣ ስዊዲን፣ ሆላንድ፣ ሲዊዘርላንድ እንደ ምሳሌ የሚጠቀሱ ሀገሮች ናቸው።

በማደግ ላይ ባሉ በተለይ በአፍሪካ ከሰሃራ በታች ባሉ ሀገሮች የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ዕድገት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። በነዚህ ሀገሮች ምዝገባው የተጀመረው በቅኝ ገዢዎች ዘመን ወይም ከመቶ ዓመታት በፊት ቢሆንም እስከ ዛሬ ድረስ ሊሸፍን የቻለው በዓመት ከሚከሰቱት የወሳኝ ኩነቶች ውስጥ ከመቶ 20 - 40 ብቻ እንደሆነ ይነገራል። ለዚህ ምክንያቱ ሕብረተሰቡ በኢኮኖሚ፣ በሶሻል፣ በባሕልና በተለይ በትምህርት ደረጃ ዝቅተኛ መሆኑና፣ ከምዝገባው የሚገኙት መረጃዎች ለሕግና ለአስተዳደር አገልግሎት በማስረጃነት የሚጫወቱት ሚና ዝቅተኛ መሆንና የስርዓቱ አዘረጋግ ከሥር መሠረቱ ጥንቃቄ የተወሰደበት ባለመሆኑ ሲሆን አስፈላጊው ክትትል፣ ማሻሻልና በተለይም ሕብረተሰቡን ለማስተማርና ለመቀስቀስ የተደረገው ጥረት ደካማ በመሆናቸው ነው።

## 1.9 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሁኔታ በኢትዮጵያ

### 1.9.1 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሕጐች

በኢትዮጵያ በ1957 የታወጀው የፍትሐብሔር ሕግ የልደት፣ የሞትና የጋብቻ ምዝገባዎች መከሄድ እንዳለባቸው ይጠቅሳል። ፍትሐብሔሩ የሀገር አስተዳደር ሚኒስቴር ምዝገባውን በኃላፊነት እንዲመራ ያዛል (1952 የፍትሐብሔር ሕግ ይመልከቱ)።

በፍትሐብሔሩ የተጠቀሰው የምዝገባው ይዘትና ዓላማ ለእያንዳንዱ ዜጋ ሕጋዊ መብቱን ለማስከበር የተደነገገ ሆኖ እናገኘዋለን። ነገር ግን ፍትሐብሔሩ ለሕብረተሰቡ የሶሻልና የኢኮኖሚ ልማት ለማቀድ የሚረዱትን ሥነ ሕዝብና ማህበራዊ ጠባዮች መመዝገብ እንዳለባቸው አይገልጽም። ሕጉ የተከሰቱትን ክንውኖች ሁሉ በማያወላውል ሁኔታ መመዝገብ እንዳለባቸው ካለማስገደዱም በላይ የክንውኖችን ምዝገባ ለማስጀመርና ሕጉንም ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ የለውም።

የስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው ነጋሪት ጋዜጣ ውስጥ /ትዕዛዝ ቁጥር 79 እና አዋጅ ቁጥር 303፣ 1964/ ጠቅላይ ጽ/ቤቱ ስለ ልደት፣ ሞት ጋብቻና ፍች ስታቲስቲክስ መሰብሰብ እንዳለበት ያዛል። እንዲሁም ለከተማ ነዋሪዎች ማህበራትና ማዘጋጃ ቤቶች ማጠናከሪያ በወጣው አዋጅ /ቁ.104/ 1969 ነጋሪት ጋዜጣ /በምዕራፍ 3 ቁ. 14 ውስጥ እያንዳንዱ የከተማ ነዋሪዎች ማኅበር ጽሕፈት ቤት ለልደት፣ ለሞትና ለጋብቻ አንዳንድ መዝገብ መያዝ እንዳአለበት ይደነግጋል። ነገር ግን ከላይ በተጠቀሱት መንግስታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች ምዝገባውን በብሔራዊ ደረጃ ለመጀመር የተወሰዱ እርምጃዎች የሉም።

### 1.9.2. ናሙና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ጥናት

የስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤት ለሙከራ በ1969 ናሙና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በገጠር በ4 ገበሬ ማህበራትና በከተሞች በ5 በተመረጡ ቀበሌዎች አካሂዶ ነበር። የሙከራ ጥናቱ ዋና ዓላማ ወደፊት በብሔራዊ ደረጃ የሚቋቋመውን የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት አስመልክቶ በሕግ፣ በቴክኒክ፣ በአስተዳደርና በበጀት በኩል ሊገጥሙት የሚችሉትን ችግሮች በቅድሚያ ለማጥናት ነበር።

ምዝገባው ለአንድ ዓመት ከተካሔደ በኋላ በተደረገው ግመገማ የተገኘው ውጤት ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል። ለዚህም ምክንያቱ በመጀመሪያ ደረጃ የቀበሌውና የገበሬ ማህበራቱ ጽ/ቤቶች ኃላፊዎች ለሥራው ከነበራቸው ዝቅተኛ ግንዛቤ ባሻገር ሕብረተሰቡን ስለአዋጁና ስለምዝገባው ጥቅም ለማስረዳት ያደረጉት ጥረት ዝቅተኛነት ነበር።

ጽህፈት ቤቱ ለሁለተኛ ጊዜ በ1975 ዓ.ም በገጠሩ በ12 ክፍለ ሀገራት በተመረጡ 500 ገበሬ ማህበራት ሌላ የሙከራ ናሙና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና የቤተሰብ ጥናት አካሂዷል። ይህ የሙከራ ምዝገባ ሙሉ በሙሉ በስታቲስቲክስ ጽ/ቤት ሠራተኞች የተከናወነ ነበር። ከዚህ የሙከራ ጥናት በተገኘው ልምድ መሠረት በ1979 ዓ.ም ለሦስተኛ ጊዜ የምዝገባውንም ሆነ የመረጃ አሰባሰቡን ዘዴ በበለጠ በማሻሻልና የገበሬ ማህበሩንም ቁጥር ወደ 750 ከፍ በማድረግ ከሙከራ ጥናት ወደ መረጃ በጥራት ማግኘት ደረጃ ከፍ ተደረገ። በዚህ ጥናት በተገኘው መረጃ መሠረት ሶስት ጥራዝ የመረጃ መተንተንና ማጠናቀር ሥራ የተካሄደባቸው ስታቲስቲካዊ ሪፖርቶች ተዘጋጅተው ተሰራጭተዋል።

ናሙና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ጥናት ለ10 ዓመታት ከተቋረጠ በኋላ በ265 በተመረጡ የገጠርና የከተማ ቆጠራ ቦታዎች ከ1990 እስከ 1991 ተካሂዶ በአሁኑ ወቅት ደግሞ በ80 የቆጠራ ቦታዎች በመካሄድ ላይ ነው፡፡

### 1.9.3. የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በሌሎች ድርጅቶች

ዓላማውና አፈጻፀሙ ከዘመናዊ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጋር ተመሳሳይ ባይሆንም በተለያዩ ሕዝባዊና መንግስታዊ ድርጅቶች የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ይካሄዳል፡፡ ከነዚህ ድርጅቶች ውስጥ የታወቀው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡ በአዲስ አበባ የልደት፣ የሞትና የጋብቻ ምዝገባ ለረጅም ጊዜ ሲካሄድ መቆየቱ ይታወቃል፡፡ ሆኖም ምዝገባው በምዝገባው ሕግ መሠረት ሳይሆን በግለሰቦች ፍላጎት ላይ ብቻ ተመርኩዞ የሚካሄድ ነው፡፡ ሌላው የሚሰበሰበው መረጃ ይዘትና ሽፋኑ ዝቅተኛ ነው፡፡ ተገልጋዮችም ቢሆኑ የተወሰኑ የሕብረተሰብ አባላት ብቻ ናቸው፡፡

ሌሎች የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የሚካሄድባቸው ድርጅቶች ሆስፒታሎች፣ የጤና ጣቢያዎች፣ ክሊኒኮች፣ ቤተክርስቲያናትና ፍርድ ቤቶች ናቸው፡፡ በእነዚህም ድርጅቶች የሚከናወነው ምዝገባ ሽፋኑ ዝቅተኛና ከድርጅቶቹ ሥራ ጋር ግንኙነት ያላቸው ብቻ ናቸው፡፡

## ምዕራፍ 2

# የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት አጠቃላይ ይዘትና አፈጻጸም

በዚህ ምዕራፍ የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ይዘትና የምዝገባ አፈጻጸም ተዘርዝሯል፡፡

## 2.1 የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ዓላማ

- በገጠርና በከተማ ተከታታይ፣ ቋሚና አስገዳጅ የሆነ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍቺ ምዝገባ ማካሄድ፣
- ለእያንዳንዱ ለተመዘገበ የወሳኝ ኩነት በሕግ ፊት ተቀባይነት ያለው ሕጋዊ ምስክር ወረቀት መስጠት፡፡
- ከምዝገባው የተገኘውን መረጃ ለሕግ፣ ለአስተዳደርና ለስታቲስቲክስ ጠቀሜታ እንዲውል ማድረግ፡፡

## 2.2 የሚመዘገቡት ወሳኝ ኩነቶች ዓይነትና ትርጉም

ዘመናዊ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻ፣ የፍቺ፣ የመለያየት፣ የማደጎ... ወዘተ ምዝገባን ያጠቃልላል፡፡ ሆኖም እንደ ተባበሩት መንግስታት አመለካከት በጣም አስፈላጊ የሆኑትና ለአስተዳደራዊ፣ ለሕጋዊና ለስታቲስቲካዊ ተግባር የሚያገለግሉት ልደት፣ ሞት፣ ጋብቻና ፍች ናቸው፡፡ በመሆኑም የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት እነዚህን ብቻ እንደሚመዘግብ ይጠበቃል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የነዚህ ወሳኝ ኩነቶች ትርጉም ይቀርባል፡፡

አንድ ልደት ተፈጸመ የሚባለው ሕጻኑን ካረገዘች ሴት ማሕፀን ሕፃኑ እንደወጣ ወዲያውኑ ሕይወት ያለው መሆኑ

ከታወቀ ነው:: ሕፃኑ ሕይወት ያለው መሆኑ የሚታወቀው ሕፃኑ ከናቱ ማሕፀን እንደወጣ ወዲያውኑ ካለቀሰ፣ ከተነፈሰ፣ ልቡና እትብቱ ላይ ትርታ ከታየ ወይንም ከተንቀሳቀሰ ነው:: ከላይ የተጠቀሱት ምልክቶች ካልታዩ ሕፃኑ የተወለደው ከሞተ በኋላ ነው::

ሞት ማለት አንድ በሕይወት ይኖር የነበረ ግለሰብ ወይም በሕይወት የተወለደ ሕፃን በአደጋ፣ በበሽታ ወይም ባልታወቀ ምክንያት በሕይወት ያለ መሆኑን የሚያሳውቁ ምልክቶች ሙሉ በሙሉ ለዘለቄታው ሲለቁትና እንደገና ነፍስ ለመዝራት የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ ነው::

ጋብቻ ማለት ለአካለ መጠን የደረሱ ሴትና ወንድን በሕጋዊ መንገድ እንደ ባህሉ ወይም ታዋቂነት ባለው መንገድ አገናኝቶ አንድ አካል አድርጎ የሚያዋህድ ወይም የሚያስተሳስር ድርጊት ነው::

የጋብቻ አፈጻጸም እንደየአገሩ፣ ሃይማኖት፣ ብሔረሰቡና ባሕሉ ዓይነት ሊለያይ ይችላል:: በኢትዮጵያ ሶስት የጋብቻ አፈጻጸም ዓይነቶች በፍትሐብሔር ሕግ መሠረት ሕጋዊነት አላቸው:: እነዚህም ብሔራዊ ወይም ሲቪል ጋብቻ፣ ሃይማኖታዊ ጋብቻና ልማዳዊ ጋብቻ ናቸው::

ብሔራዊ ወይም ሲቪል ጋብቻ ለአካለ መጠን የደረሱ አንድ ወንድና አንድ ሴት በክብር መዝገብ ሹም ፊት ቀርበው ፈቃዳቸውን በፊርማቸው ሲያረጋግጡና የክብር መዝገብ ሹሙም ተቀብሎ ሲመዘግበውና በሕግ ስም ሲያስታውቅ ነው::

ሃይማኖታዊ ጋብቻ ለአካለ መጠን የደረሱ አንድ ወንድና አንድ ሴት እንደ ሃይማኖታቸው ወይም ከሁለቱ በአንደኛው ሃይማኖት መሠረት በሕግ የሚፀና ጋብቻ ሲፈጽም ነው::

ለምሳሌ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት የተክሊል ጋብቻ ያለቁርባን ወይም በቁርባን ሲፈፀም እንዲሁም በእስልምና ሃይማኖት የኒካህ የታሠረ ጋብቻ ሃይማኖታዊ ጋብቻዎች ናቸው።

ልማዳዊ ወይም ባህላዊ ጋብቻ ለአካለ መጠን የደረሱ አንድ ወንድና አንድ ሴት በጎሳቸው ልማድ ወይም ባህል ወይም ከሁለቱ ባንዱ ጎሳ ልማድ መሠረት በሕግ የሚፀና ጋብቻ ሲፈፅም ነው።

ፍቺ ማለት በአንድ ባልና ሚስት /ሁለቱም በሕይወት ያሉ/ መካከል በብሔራዊ ወይም በሃይማኖታዊ ወይም በልማዳዊ መንገድ ተመሥርቶ የነበረ ጋብቻ ሙሉ በሙሉ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ሲፈርስና ሁለቱም ወይም አንዱ ባስፈለጋቸው ጊዜ ሌላ ባል/ሚስት ለማግባት የሚያስችላቸውን መብት የሚያስገኝ ድርጊት ነው።

## 2.3 የወሳኝ ኩነቶች አስመዝጋቢ

የወሳኝ ኩነቶች አስመዝጋቢ የልደት፣ የሞት የጋብቻና የፍቺ ኩነቶችን እንደተከናወኑ ለማስመዝገብ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ በምዝገባ ጽ/ቤት ተገኝቶ ማስመዝገብ እንዳለበት በሕግ ኃላፊነት የተሰጠው ግለሰብ ነው። አስመዝጋቢ ተፈላጊውን መረጃ በትክክል መስጠት የሚችል ግለሰብ መሆን አለበት።

ከዚህ ቀጥሎ እያንዳንዱን ወሳኝ ኩነት ማን ማስመዝገብ እንዳለበት ተዘርዝሯል።

### 2.3.1. የልደት አስመዝጋቢ

- አባት እና እናት

- አባት/እናት
- የአባት/የእናት የቅርብ ዘመድ

2.3.2. የሞት አስመዝጋቢ

ሀ. አባት
ለ. እናት
ሐ. ባል/ ሚስት
መ. እህት/ ወንድም
ሠ. የሟች የቅርብ ዘመድ

2.3.3 ጋብቻ አስመዝጋቢ

ሙሽራውና ሙሽራይቱ

2.3.4 ፍቺ አስመዝጋቢ

ሁለቱ ተፋቺዎች

## 2.4 የወሳኝ ኩነቶች መዝጋቢ

መዝጋቢ(የክብር መዝገብ ሹም) የልደት፡ የሞት፡ የጋብቻና የፍቺ ኩነቶችን እንዲመዘግብ በሕግ ኃላፊነት የተሰጠው ግለሰብ ነው:: የምዝገባው ሥርዓት ዓላማ ግቡን እንዲመታ መዝጋቢው ኃላፊነቱን በትክክል መወጣት የሚችል መሆን አለበት::

የወሳኝ ኩነቶች መዝጋቢ ቀጥሎ የተመለከቱ ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል::

- የልደት፡ የሞት፡ የጋብቻና የፍቺ ኩነቶችን መመዝገብ

- ለእያንዳንዱ ለተመዘገበ የወሳኝ ኩነት ሕጋዊ ሰርተፊኬት መስጠት
- እያንዳንዱን ኩነት ከመመዝገቡ በፊት በትክክል ለመፈጸሙ ማረጋገጫ ማግኘት፣
- የምዝገባው ሂደት በምዝገባ ሕግና ደንብ መሠረት መከናወኑን ማረጋገጥ፣
- የምዝገባው ጽ/ቤት በሚገኝበት ቀበሌ ውስጥ የተከሰቱት ኩነቶች በሙሉ መመዝገባቸውን ማረጋገጥ፣
- ኩነቱንና ከኩነቱ ጋር ግኑኝነት ያላቸውን ግለሰቦች የሚመለከቱ መረጃዎች በትክክል መመዝገብ፣
- የምዝገባው የጊዜ ገደብ መከበሩን መከታተል፣
- ሕብረተሰቡን ስለ ወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሕግና ደንብ ማስተማር፣
- የምዝገባ ዶክሜንቶችን በጥንቃቄ መያዝና መጠበቅ፣
- የምዝገባ ዶክሜንቶችን ሚስጥራዊነት መጠበቅ፣
- የተመዘገቡ ወሳኝ ኩነት መረጃዎችን ለወሳኝ ኩነት ስታቲስቲክስ ጽ/ቤት ሪፖርት ማድረግ፣
- አንዳንድ የመዝገቦች ኮፒ ወደ ማዕከላዊው መዝገብ ቤት መላክ፣
- ሌሎች በምዝገባው ሕግ የተካተቱ ተግባሮችን መፈፀም፣

## 2.5 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አፈጻጸም

የወሳኝ ኩነቶች የሚመዘገቡት ኩነቱ እንደተከሰተ ለምዝገባ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ነው። አስመዝጋቢ ኩነቱ እንደተከሰቱ ወደ ምዝገባ ቢሮ ሪፖርት ያደርጋል። መዝጋቢ አስመዝጋቢን መታወቂያ ካርድ እንዲያሳየው ይጠይቃል። ቀጥሎም የሚመዘገበው ወሳኝ ኩነት በትክክል ለመከሰቱ የሚያረጋግጥ መረጃ (ለምሳሌ የሐኪም ሰርተፊኬት/የዓይን ምስክር) እንዲያቀርብ ይጠይቃል። በቀረበው የማረጋገጫ

መረጃና ከአስመዝጋቢ በሚሰጠው ተጨማሪ መረጃ መሠረት ኩነቱን መዝግቦ ካጠናቀቀ በኋላ ለአስመዝጋቢ የምስክር ወረቀት ይሰጣል:: የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ዝርዝር አፈጻጸም በተመለከተ በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ በገጽ 28 የተመለከተውን ፍሎው ቻርት (Flow Chart) ይመልከቱ:

## 2.6 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ቦታ

ኩነቶች ከኩነቶች ጋር ግንኙነት ካላቸው ግለሰቦች መደበኛ መኖሪያ ቦታ ውስጥ ወይም ውጪ ሊፈፀሙ ይችላሉ::

መደበኛ መኖሪያ ቦታ ማለት ግለሰቡ ወይም ቤተሰቡ ስድስት ወርና ከዚያ በላይ ያለማቋረጥ የኖረበት ቦታ ወይም ለዘለቄታው መኖር የጀመሩበት ቦታ ማለት ነው::

ኩነቶች ሁልጊዜ በመደበኛ መኖሪያ ቦታ መመዝገብ አለባቸው:: ሆኖም ኩነቶችን በመደበኛ መኖሪያ ቦታ መመዝገብ አልፎ አልፎ ችግር ያስከትላል:: ይኸውም ኩነቱ የተፈፀመላቸው ግለሰቦች (ለምሣሌ ወታደሮች፣ ተማሪዎችና ነጋዴዎች) የተለያዩ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ መኖሪያ ቦታዎች ሊኖሩአቸው ይችላል:: ሌሎች ደግሞ መደበኛ መኖሪያ ላይኖራቸው ይችላል/ ለምሣሌ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ የሚኖሩ/:: አንዳንዶቹ ደግሞ ጥገኛ ሊሆኑ ይችላሉ:: ሆኖም ወሳኝ ኩነቶች መመዝገብ ያለባቸው ኩነቱ በተፈፀመላቸው ግለሰቦች መደበኛ መኖሪያ ቦታ መሆን አማራጭ አይኖረውም::

ወሳኝ ኩነቶች በሚከተሉት ግለሰቦች መደበኛ መኖሪያ ቦታ መመዝገብ አለባቸው::

- ልደት - በሕፃኑ እናት መደበኛ መኖሪያ ቦታ
- ሞት - በሟች መደበኛ መኖሪያ ቦታ

- ጋብቻ - በተጋቢዎች መደበኛ መኖሪያ ቦታ
- ፍቺ - በባል/በሚስት መደበኛ መኖሪያ ቦታ

## 2.7 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽህፈት ቤት

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ መካሄድ ያለበት በገጠርና በከተማ ቀበሌዎች መሆን ይኖርበታል፡፡ የምዝገባው ጽ/ቤት አማካይ ቦታ ቢሆን ምዝገባውን ከማቀላጠፉም ባሻገር የሕብረተሰቡን የጉዞ ጊዜና ድካም ስለሚቀንስ ምዝገባውን የተሟላ ያደርገዋል፡፡ በተለይ የገጠር ቀበሌዎች ሰፊና ቤቶቹ የተራራቁ ስለሚሆን መዝጋቢው አማካይ ስፍራዎችን በመምረጥ ወይም ቀበሌውን በትናንሽ መንደሮች በመከፋፈል ንዑሳን የምዝገባ ጣቢያዎችን በመፍጠር በተወሰነ ጊዜ በመንደሮቹ በመገኘት ምዝገባውን ሊያከናውን ይችላል፡፡ ይህም ሲደረግ የመንደሮቹ ነዋሪዎች ዝግጁ እንዲሆኑ መዝጋቢው የሚመጣበትን ቀን በቅድሚያ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 2.8 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የጊዜ ገደብ

አንድ ወሳኝ ኩነት ከተፈፀመ በኋላ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡ ለእያንዳንዱ ኩነት የመመዝገቢያ ጊዜ መወሰን ያስፈልጋል፡፡ የምዝገባ የጊዜ ገደብ አጭር መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም በአስመዝጋቢዎች ግዴለሽነት ወይም መርሳት ኩነቶች ሳይመዘገቡ እንዳይቀሩ ለማድረግ ይረዳል፡፡ እያንዳንዱ ወሳኝ ኩነት በተገደበለት የጊዜ ገደብ ካልተመዘገበ በሕጉ ላይ በሰፈረው ደንብ መሠረት የወሳኝ ኩነቱን ማስመዝገብ በሚገባው ግለሰብ ላይ ቅጣት መፈፀም አለበት፡፡

የእያንዳንዱ ኩነት የመመዝገቢያ የጊዜ ገደብ የተለያየ ይሆናል፡፡ የጊዜ ገደቡ ማጠር ወይም መርዘም በጂዖግራፊ አቀማመጥ፣ የአየር ጠባይ፣ የቤቶች አቀማመጥ፣ ባህልና

እምነት ላይ የተመሠረተ ይሆናል:: እያንዳንዱ ኩነት ከዚህ ቀጥሎ ከተመለከቱት ቀናት ባልበለጠ ጊዜእት ቢመዘገብ ይመረጣል::

ሀ. ልደት - በ15 ቀናት
ለ. ሞት - በ3 ቀናት
ሐ. ጋብቻ - በ7 ቀናት
መ. ፍቺ - በ7 ቀናት

## 2.9 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባን በጊዜ አለማስመዝገቡ የሚያስከትለው ቅጣት

ስለምዝገባ ባህል፣ ልምድና ግንዛቤው በሌለበትና የምዝገባውን ሥርዓት አዲስ በሚጀምር አገር ቀርቶ ከፍተኛ ደረጃ በደረሱና የረጅም ጊዜ የምዝገባ ልምድ ባካበቱት አገሮችም ቢሆን ፈጽሞ አለማስመዝገብና የምዝገባ የጊዜ ገደብን አሳልፎ ማስመዝገብ ይኖራል:: አለማስመዝገብና ዘግይቶ ማስመዝገብ ሁለቱም ተመሣሣይ ችግሮች ያስከትላሉ:: ይኸውም በዓመቱ ውስጥ የተከሰቱትን ኩነቶች ሣይመዘገቡ እንዲቀሩ ያደርጋሉ:: ፈጽሞ አለማስመዝገብና ዘግይቶ ማስመዝገብ በሁለት ምክንያቶች ሊከሰቱ ይችላሉ:: እነሱም በምዝገባ ጽ/ቤቱና በሕብረተሰቡ በኩል የሚፈጠሩ ችግሮች ናቸው::

ወሳኝ ኩነቶችን ፈጽሞ ያላስመዘገቡና ዘግይተው ያስመዘገቡ አስመዝጋቢዎች በሕግ በተደነገገው መሠረት መቀጣት ይኖርባቸዋል:: ሆኖም ከቅጣቱ በፊት ለሕብረተሰቡ ስለምዝገባው አስፈላጊውን ትምህርት መስጠቱ መቅደምና መዘውተር አለበት:: ቅጣትን መጣል የመጨረሻው አማራጭ መሆን ይኖርበታል:: ለቅጣት ቅድሚያ መስጠትና ማክበድ ከአዎንታዊ ይልቅ አሉታዊ ገፅታዎች ሊያመዝኑ ስለሚችሉ ጥንቃቄ መውሰድ ያስፈልጋል:: ለምሳሌ ቅጣቱን በመፍራት

አስመዝጋቢው ኩነቱ የተከሰተበትን ጊዜ በመቀየር ሊያስመዘግብ ይችላል።

## 2.10 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ መረጃዎች ሚስጢራዊነት

ለመዝጋቢው ሪፖርት ተደርገው የተመዘገቡት መረጃዎች ምስጢራዊነት መጠበቅ አለበት። መረጃዎቹን ለሕግ፣ ለአስተዳደርና ለስታቲስቲካዊ አገልግሎት ካልሆነ በስተቀር ለሌላ ጉዳይ ማዋል አይቻልም። መረጃዎቹ መተላለፍ ያለባቸው በሕግ ኃላፊነት ለተሰጠው ግለሰብ ወይም ድርጅት ካልሆነ በስተቀር በሌሎች እጅ መግባት የለባቸውም።

## 2.11 የወሳኝ ኩነቶች ማረጋገጫ

አንድ ወሳኝ ኩነት ከመመዝገቡ በፊት በትክክል ለመፈፀሙ ማረጋገጫ ያስፈልጋል። አስመዝጋቢው ይኸንን ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርበታል። እንደ ወሳኝ ኩነቱ ዓይነትና ቦታ ማረጋገጫው የሕግ ዶክሜንት ለምሣሌ የፍርድ ቤት ውሳኔ፣ የሐኪም ሰርቲፊኬት፣ የዓይን ምስክር ወይም ከላይ የተጠቀሱትን ሁሉ ሊያጠቃልል ይችላል።

ከዓይን ምስክር ይልቅ የጽሑፍ ማስረጃ የበለጠ ተቀባይነትና ታማኝነት ይኖረዋል። ስለሆነም የዓይን ምስክር ተቀባይነት የሚያገኘው የጽሑፍ ማስረጃ ማቅረብ በማይቻልበት ሁኔታ ብቻ ነው። ለምሳሌ በገጠር የሐኪም ሰርተፊኬት ላይገኝ ስለሚችል የዓይን ምስክር ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል።

## 2.12 የወሳኝ ኩነቶች ዶክሜንቶች እርማት

የወሳኝ ኩነቶች መዝገቦችና ምስክር ወረቀቶች የጽሁፍ ግድፈትና የመረጃ አሞላል ስህተት ከተገኘባቸው መታረም ይገባቸዋል። እነዚህ ስህተቶች እንዴት መታረም እንዳለባቸውና የማረም ኃላፊነት የተሰጠው ለማን እንደሆነ በምዝገባ ሕግና ደንብ ውስጥ መካተት አለበት

የመዝገቦችንና የምስክር ወረቀቶችን እርማት ማን ያከናውን ለሚለው መልሱን በሶስት አማራጮች ከፍሎ ማየት ይቻላል።

<u>አንደኛው የእርማት አማራጭ</u> እርማቱ መከናወን ያለበት በፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረት መሆን ይኖርበታል የሚል ነው። ሆኖም በመዝገቦችና በምስክር ወረቀቶች ላይ የተከሰቱ ስህተቶችን በፍርድ ቤት ዉሣኔ መሠረት ማስተካከል ጊዜ የሚወስድ፣ ከፍተኛ ገንዘብ የሚጠይቅና ውስብስብ በመሆኑ አስቸጋሪ ይሆናል።

<u>ሁለተኛው የእርማት አማራጭ</u> እርማቱ በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ክፍል መከናወን አለበት የሚል ነው። የዚህ ዓይነት የእርማት አሠራር ቀልጣፋ፣ ብዙ ገንዘብ የማይጠይቅና ቀላል ነው።

<u>ሦስተኛው የእርማት አማራጭ</u> እርማቱ በፍርድ ቤት ውሣኔና በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ክፍል አማካይነት ይፈፀም የሚል ነው።

በተመሣሣይ ሁኔታ እርማቱ እንዴት ይከናወን ለሚለው መልሱን እንዲሁ በሦስት አማራጮች ከፍሎ ማየት ይቻላል።

አንደኛው የእርማት አማራጭ ስህተቱን ወዲያውኑ እንደተፈፀመ ማረም ነው። ይኸውም የተሳሳተውን መረጃ አርሞ ምንም ስህተት እንዳልተፈፀመ አድርጉ መተው።

ሁለተኛው የእርማት አማራጭ የተሳሳተውን መረጃ በቀጭኑ ሠርዞ በአናቱ ላይ ትክክለኛውን መረጃ መጻፍ።

ሦስተኛው የእርማት አማራጭ አዲስ መዝገብ ወይም ምስክር ወረቀት ማዘጋጀት። በዚህ ጊዜ ስህተት የተፈፀመበትን መዝገብና ሰርቲፊኬት መሠረዝና በምዝገባ ፋይል ውስጥ ማኖር ያስፈልጋል። ይኸውም መዝገቦቹ ተከታታይ ቁጥር የተሰጣቸው ስለሆነና እንዳይጐድሉ ስለሚያስፈልግ ነው። የዚህ ዓይነት የእርማት መንገድ ጥቅሙ መዝገቡም ሆነ ምስክር ወረቀቱ ያልተደለዙና ንፁህ እንዲሆኑ ያደርጋል።

ከሦስቱ አማራጮች በአንዱ እርማቱ ከተከናወነ በኋላ የታረሙት መዝገቦች በሁለት ኮፒ ተሠርተው አንደኛው ወደ ማዕከላዊ መዝገብ ቤት ሲላክ ሌላው በምዝገባው ክፍል መቀመጥ ይኖርበታል።

## 2.13 የወሳኝ ኩነቶች መዝገቦች አያያዝና አጠባበቅ

በየቀበሌዎች የተሞሉት መዝገቦች ተሰብስበው በማዕከላዊ የወሳኝ ኩነቶች መዝገብ ቤት መከማቸት አለባቸው። ማዕከላዊ የወሳኝ ኩነቶች መዝገብ ቤት የተሞሉ መዝገቦች ከየምዝገባ ጽህፈት ቤቶች ተሰብስበው የሚቀመጡት ማዕከል ነው። ማዕከላዊ መዝገብ ቤት መዝገቦችን በአስፈለገ ጊዜ ለሕጋዊ፣ ለአስተዳደራዊና ለስታቲስቲካዊ አገልግሎት እንዲውሉ ያደርጋል። በተጨማሪም መዝገቦችን በማዕከላዊው የወሳኝ ኩነቶች መዝገብ ቤት ማከማቸት የምዝገባውን ሂደት፣ የመዝገቦችን ደህንነትና ሚስጥራዊነት ለመከታተልና ለመጠበቅ ይረዳል።

ሆኖም መዝገቦችን በአንድ ማዕከል ማሰባሰብ ሰፊ ቦታና ከፍተኛ ገንዘብ ይጠይቃል። በመሆኑም የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ሕግና ደንብ ይህንን በማመዛዘን መዝገቦች በየትኛው አካል ሥር፣ የትና እንዴት መከማቸትና መንቀሳቀስ እንዳለባቸው በዝርዝር መደንገግ ይኖርበታል።

የተማከለ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ባለበት አገር ማዕከላዊው ወይም ሀገር አቀፉ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽህፈት ቤት በየአስተዳደር ክልሉ ከተሞሉት መዝገቦች አንዳንድ ኮፒ በመውሰድ በማዕከላዊ መዝገብ ቤት ያከማቻል። እያንድንዱ የምዝገባ ጽህፈት ቤት ደግሞ የራሱን ኮፒ ያስቀራል።

ያልተማከለ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ባለበት አገር የወሳኝ ኩነቶች መዝገቦችን በማዕከላዊ መዝገብ ቤት ለማከማቸት በተለይ ከሎጀስቲክና ከመገናኛ ትራንስፖርት አስቸጋሪነት የተነሣ አዳጋች ይሆናል። በመሆኑም ባልተማከለ፣ ሰፊና ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ባለበት አገር ማዕከላዊ የወሳኝ ኩነቶች መዝገብ ቤት በእያንዳንዱ ክልል ዋና ከተማ ሊቋቋም ይችላል። ለምሣሌ በኢትዮጵያ በእያንዳንዱ ክልል ዋና ከተማ ማዕከላዊ የወሳኝ ኩነቶች መዝገብ ቤት ለማቋቋም ይቻላል። እንዲሁም በሰፋፊ ክልሎች ለምሳሌ በኦሮሚያ፣ በአማራና፣ በደቡብ ክልሎች፣ በእያንዳንዱ ዞን ማዕከላዊ የወሳኝ ኩነቶች መዝገብ ቤት ማቋቋም ቀልጣፋ አሠራርን ሊፈጥር ይችላል።

የማዕከላዊው የወሳኝ ኩነቶች መዝገብ ቤት ሹም ኃላፊነቱና ተግባሩ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን መዝገቦች እንቅስቃሴ መከታተል፣ መቆጣጠር፣ ደህንነታቸውን መጠበቅ፣ መዛገቦች ሲፈለጉ በአጭር ጊዜ እንዲገኙ ማዘጋጀት፣ ከጥፋት፣ ከስርቆት፣ ከቃጠሎ፣ የተጠበቁና ለረጅም ጊዜ አገልግሎት

እንዲሰጡ ማድረግ ነው። በመሆኑም ከፍተኛ የመዘገብ አያያዝና አጠባበቅ ችሎታ እንዲኖረው ሥልጠና እንዲሰጠው ያስፈልጋል።

የመዝገቦች አያያዝ ደረጃ የሚለካው መዝገቦቹ በተፈለጉ ጊዜ በሚወጡበት ፍጥነት መሠረት ነው። በመሆኑም መዝገቦቹ ሲፈለጉ በአጭር ጊዜና በቀላሉ ሊወጡ በሚችሉበት ሁኔታ መዘጋጀት አለባቸው።

ሌላው የመዝገቦች አያያዝ በመዝገቦች ዓይነት ይወሰናል። መዝገቦቹ ጥራዝ ወይም የባህረ መዝገብ ከሆኑ ሁለት ጥራዞች ወይም ባህረ መዝገቦች ተዘጋጅተው አንዱ በምዝገባ ክፍል ሲቀመጥ ሌላው ወደ ማዕከላዊው መዝገብ ቤት ይላካል። በጥራዙ ወይም በባህረ መዝገቡ ውስጥ ያሉት መረጃ የያዙ ቅጠሎች በቅደም ተከተል ቁጥር የተሠጣቸው መሆን አለባቸው። በዚህ መሠረት አንድ ጥራዝ ለምሳሌ ከ1-100 የሚደርሱ ኩነቶችን መረጃ የያዙ ቅጠሎች ሊይዝ ይችላል። በዚህ ጊዜ በምዝገባ ጽ/ቤት የሚቀመጡት ጥራዞች በቁጥሮችና በዓመተ ምህረት ቅደም ተከተል ሲሆን በማዕከላዊው መዝገብ ቤት የሚቀመጡት በአካባቢ፣ በተራ ቁጥርና፣ በዓመተ ምህረት ቅደም ተከተል መሆን አለበት።

መዝገቦች በብትን ወረቀት ከሆኑ የእያንዳንዱን ዓመት መዝገቦች በተሰጣቸው የአመዘጋገብ ተራ ቁጥርና አካባቢ ማዘጋጀትና በማያያዝ በባለ ቀለበት ኢቃፊ ውስጥ ማስቀመጥ ያስፈልጋል። መዝገቦቹ ካርዶች ከሆኑ ከላይ በተገለፀው ዘዴ ወይም በሣጥን ወይም በመደርደሪያ ላይ ማስቀመጥ ይቻላል።

መዝገቦች ከብዙ ጊዜ ማገልገል፣ ከወረቀቶች ጥራት ማነስና ከአያያዝ ጉድለት የተነሣ ከጥቅም ውጭ እየሆኑ ሊሄዱ ይችላሉ። እንዲሁም በውሃና በእሣት ምክንያት ሊበላሹ

ይችላሉ። እንዲሁም በስርቆትም ምክንያት ሊጠፉ ይችላሉ። በመሆኑም የሚከተሉት ጥንቃቄዎች መደረግ አለባቸው።

መዝገቦች በጥራዝ ወይም በባህረ መዝገብ የሚዘጋጁ ከሆነ በአጠራረዝ ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ አለበት። ሲጠረዙም በሥራው ችሎታ ባለው ድርጅት መጠረዝ አለባቸው። ሲያረጁም መታደስ አለባቸው። ማን መጠረዝና ማደስ እንዳለበት በምዝገባ ሕግ ውስጥ መደንገግ አለበት። በሚከማቹበት ጊዜ የአካባቢው ተስማሚነት ማለትም የብርሃንና የአየሩ ሁኔታ በተመለከተ ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል። ይኸውም የቀለም መልቀቅን፣ የጽሁፎች መጥፋትን፣ የቶሎ ማርጀትንና ከጥቅም ውጪ መሆንን ለመከላከል ነው። መዝገቦች ከእንስሳት፣ ከበራሪ ነፍሳት፣ ከአይጦችና ከመሣሠሉት አጥፊ ፍጥረታት የተጠበቁ መሆን አለባቸው። በተጨማሪም መዝገቦች ከሌቦችና ከርጥበት/ ከወሃ የተጠበቁ እንዲሆኑ አስፈላጊው ጥንቃቄ አስቀድሞ በከፍተኛ ደረጃ መወሰድ አለበት።

## 2.14 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የሰው ኃይልና ስልጠና

በምዝገባው ሥራ ቁጥራቸው በርካታ ያሉ ሠራተኞች እንደሚሳተፉ እሙን ነው። ሠራተኞች ቋሚ ወይም ጊዜአዊ ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲሁም የምዝገባው ጽ/ቤት ሠራተኞች ወይም ከሌላ መ/ቤት በትውስት የመጡ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ በተለያዩ ዘርፎች በገጠርና በከተማ ተመድበው የሚሠሩ የጤና ጥበቃ ሠራተኞች እንዲሁም አስተማሪዎችና ተማሪዎች በምዝገባው ሊሳተፉ ይችላሉ።

አስመዝጋቢዎች ወደ ምዝገባ ጽ/ቤት መጥተው ኩነቱን ማስመዝገብ እንዳለባቸው ቢታመንም በአስመዝጋቢዎቹ ላይ ብቻ የሚያተኩር የምዝገባ አፈፃፀም (በተለይ የምዝገባ ባህል ከመለመዱ በፊት) ውጤቱ ዝቅተኛ ይሆናል። በተለይ

በገጠሩ አካባቢ የመገናኛ ችግር ባለበት፣ የመሬቱ አቀማመጥ ውጣ ውረድ በበዛበትና ቤቶች ተራርቀው በተቀመጡበትና የምዝገባ ጥቅም በህብረተሰቡ ዘንድ በደንብ ባልታወቀበት ሁኔታ ግለሰቦች መጥተው ሪፖርት ሲያደርጉ ብቻ ምዝገባ እናካሂዳለን ብሎ መጠበቁ ትክክለኛ አይሆንም። በመሆኑም በመንደሮችና በሠፈሮች አካባቢ በጠቋሚነት የሚያገለግሉ ያገር ሽማግሌዎች፣ ተማሪዎች፣ አስተማሪዎች፣ የጤና ሠራተኞች፣ የባህል አዋላጆች፣ የግብርና ሠራተኞች...ወዘተ በምዝገባው እንዲሳተፉ ማድረግ ጥሩ ውጤት ለማግኘት ይጠቅማል።

በሁሉም አቅጣጫ ተመድበው ለምዝገባው ተፈጻሚነት የበኩላቸውን ሥራ በማከናወን ላይ የሚገኙ ሠራተኞች ሥራቸውን ለማሻሻል የሚጠቅም ሥልጠና በየወቅቱ ማግኘት ይገባቸዋል። በተለይ በምዝገባው የመጀመሪያ አመታት የሠራተኞች ስልጠና ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው። የምዝገባን ውጤት ዝቅተኛ ከሚያደርጉት ችግሮች አንዱና ዋንኛው የሰለጠነና ስለምዝገባው ዓላማና ግብ የጠለቀ ግንዛቤ ያለው የሰው ኃይል እጥረት ነው።

የሥልጠና አሰጣጥ ቀጥሎ በተመለከቱት ዘዴዎች ሊከናወን ይችላል።

- በሥራ ላይ የሚሰጥ ስልጠና፣
- በመደበኛ ከፍተኛ ትምህርት ቤቶች፣
- የልምድ ልውውጥ በማድረግ፣
- የሰለጠነ የሰው ኃይል እርዳታ ማግኘት

## 2.15 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሎጂስቲክ ክፍል

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤት የምዝገባውን እንቅስቃሴ በትክክል ለመምራት የሎጅስቲክ ክፍል ያስፈልገዋል። የሎጂስቲክ ክፍል የተሞሉትን ፎርሞችና መዝገቦች በሚገባ መጠበቅና ለማዕከላዊው መዘገብ ቤትና ለወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ጽ/ቤት በየጊዜው መላክ ይኖርበታል።

ከላይ ወደታችና ከታች ወደላይ የሚላኩትን በሚገባ ቆጥሮና መዝግቦ መረከብና በማይበላሹበትና በማይጠፉበት ሁኔታ ማስቀመጥ አለበት።

በምዝገባ ጽሕፈት ቤት ቀሪ የሆኑትን መዝገቦችንና ቅጾችን ወሳኝ ኩነቱ በተፈፀመበት ዓመት በመደርደር በአስፈላጊ ጊዜ ያለ ችግር መረጃዎቹ በሚገኙበት ሁኔታ ማስቀመጥ አለበት።

## 2.16 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የሕዝብ ግንኙነት ክፍል

ከሌሎች አገሮች በተገኙት ልምዶች መሠረት ለወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ እድገት እንቅፋት ከሆኑት ምክንያቶች አንዱና ዋንኛው ሕብረተሰቡ ኩነቶችን በተሰጠው የጊዜ ገደብ አለማስመዝገብ ነው። ለዚህም ዋናው ምክንያት ሕብረተሰቡ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የሚሰጠውን ጥቅም በትክክል አለመረዳት ነው። ለሕብረተሰቡ ትብብር ዝቅተኛነት ምክንያት ከሆኑት መካከል የባሕልና የእምነት ተፅእኖና የትምህርት ማነስ ናቸው።

ሕበረተሰቡን ስለ ምዝገባው ጥቅምና አፈጻጸም በሚከተሉት ዘዴዎች ማስተማር ያስፈልጋል።

- በየስብሰባ ቦታው ስለ ምዝገባ ቅስቀሳ በማድረግ፣

- በሬዲዮ፡ በቴሌቪዥንና በጋዜጣ ትምህርታዊ ቅስቀሳ በማድረግ፡
- ፖስተሮች፡ መፈክሮች በየቦታው መለጠፍና በነሱም አማካይነት መልእክት ለሕብረተሰቡ በማስተላለፍ፡
- በየትምህርት ቤቱ ስለ ወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ጥቅም በማስተማር
- ሴሚናሮችና ወርክሾፖች በማዘጋጀት ውይይት በማድረግ፡
- በየቤተክርስቲያኑና፡ በየመስኪዱ ስለምዝገባው በማሣወቅ
- በሆስፒታሎችና ዕድሮች ስለምዝገባው በማስረዳት
- በየመ/ቤቱ በሚደረጉ ስብሰባዎች በማሣወቅ

ከላይ የተጠቀሱትን የማስተማሪያና ቅስቀሳ መንገዶችን ተግባራዊ ለማድረግ በምዝገባው አስተባባሪ ኮሚቴ ሥር የሚመራ የቅስቀሳና የፕሮፓጋንዳ ንዑስ ኮሚቴ በማቋቋም የሚሠራ የቅስቀሳና የፕሮፓጋንዳ ንዑስ ኮሚቴ በማቋቋም ፕሮግራሙን መምራት ይቻላል፡፡ የምዝገባ ጽ/ቤቱ ይህንን ተግባር የሚከታተል፡ ትምህርቶችን የሚያዘጋጅ፡ ከትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ ጋር አብሮ የሚያሠራ፡ የሚሠራ የሕዝብ ግንኙነት ክፍል እንዲኖረው ያስፈልጋል፡፡ የሕዝብ ግንኙነት ክፍሉ ከምዝገባው ባለሙያዎች ጋር በመሆን ተከታታይና ቋሚ የሆኑ የትምህርትና ቅስቀሳ ፕሮግራሞች በማዘጋጀት ሕብረተሰቡን የመቀስቀስ ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

## 2.17 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሂደት ግምገማ

ቀደም ብሎ ለመግለፅ እንደተሞከረው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ውጤታማ እስኪሆን ድረስ ከፍተኛ ገንዘብ፡ የሰው ኃይልና ጊዜ ይጠይቃል፡፡ መረጃውም ጥራት እያገኘ ሊሄድ የሚችለው በየጊዜው ግምገማ በማድረግና አስፈላጊና

ተከታታይ ማሻሻያዎች በማድረግ ነው። ሌላው ለህብረተሰቡ በተከታታይ በሚሰጠው ትምህርታዊ ቅስቀሳና እንዲሁም ምስክር ወረቀቶች በተለያዩ ሕጋዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በሚያገኙት ታዋቂነትና ተፈላጊነት መጠን ነው።

ተከታታይ ግምገማ ለወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ መረጃ ጥራት፣ ተዋህዶነት፣ እንዲሁም የስርዓቱን ጥንካሬና ድክመት ለመለካት ይረዳል። ግመገማዎችን የተለያዩ ቴክኒኮችን በመጠቀም ማከናወን ይቻላል። ግምገማው በመጠንና (በሽፋን) በጥራት ላይ ያተኮረ መሆን ይኖርበታል። የግምገማ መርሃ ግብር በሚገባ ተዘጋጅቶ በመርሃ ግብሩ መሠረት መካሄድ አለበት። በተገኘው ውጤትም መሠረት አስፈላጊ ማሻሻያዎች ሣይውሉ ሳያድሩ መፈፀም አለባቸው። በማደግ ላይ ባሉ አገሮች የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ከተቋቋመ ዓመታት ማስቆጠሩ ተደጋግሞ ተገልጿል። ነገር ግን ተከታታይ ግምገማዎች በየጊዜው እየተደረጉ አስፈላጊው ማሻሻል በወቅቱ ባለመደረጉ የምዝገባው ውጤት ዝቅተኛ ሆኖአል።

<u>የመጠን ወይም የሽፋን ግምገማ:-</u> የመጠን ወይም የሽፋን ግምገማ ዓላማ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በሕብረተሰቡ ውስጥ የተከሰቱትን ልደቶች፣ ሞቶች፣ ጋብቻዎችንና ፍቺዎችን ሙሉ በሙሉ መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ ይሆናል።

<u>የጥራት ግመገማ:-</u> የጥራት ግምገማ ዓላማ የተመዘገቡት የወሳኝ ኩነቶችንና ከወሳኝ ኩነቶች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ግለሰቦች የሚመለከቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መረጃዎች በትክክል መመዝገባቸውን ለመከታተል ይሆናል።

## 2.18 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በጀት

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አስፈላጊው በጀት እንዲዘጋጅለት ያስፈልጋል። በጀቱም ለዶክመንቶች፣ ለሰው ኃይል፣ ለጽሕፈት መሳሪያዎች፣ ለሥልጠና፣ ለሕብረተሰቡ ትምህርታዊ ቅስቀሳ፣ ለሎጅስቲክ፣ ለህትመት፣ ለመረጃ ማጠናቀር፣ ለግምገማ... ወዘተ የሚያስፈልግ ይሆናል። የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በመጀመሪያው ወቅት በአነስተኛ ቁጥር በገጠርና በከተማ ቀበሌዎች ጀምሮ እያደገ የሚሄድ ስለሚሆን በጀቱም በዚያን ያህል እያደገ ይሄዳል። የበጀቱ ምንጭ በምዝገባው ሕግ መደንገግ አለበት።

# የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አፈጻጸም



# ምዕራፍ 3

## የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ዶክመንቶች

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ሲቋቋም ብዛት ያላቸው ዶክመንቶች በጥቅም ላይ ይውላሉ። ከነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው። መዝገቦች፣ የምስክር ወረቀቶች፣ የስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጾች፣ የምዝገባ ሕግ ዶክመንትና መመሪያ ናቸው።

## 3.1 የወሳኝ ኩነቶች መዝገቦች

የወሳኝ ኩነቶች መዝገቦች የእያንዳንዱን የወሳኝ ኩነት መከሰት፣ ኩነቱንና ከኩነቱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ግለሰቦች የሚመለከቱ ስነ ሕዝብ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ባህሪያት የሚመዘገቡባቸው ቅጾች ናቸው።

### 3.1.1 የወሳኝ ኩነቶች መዝገቦች ዓይነት

የወሳኝ ኩነቶች መዝገቦች በአራት ይከፈላሉ። እነሱም የልደት መዝገብ፣ የሞት መዝገብ፣ የጋብቻ መዝገብና የፍቺ መዝገብ ናቸው።

የልደት መዝገብ እያንዳንዱን ልደትና ወላጆችን የሚመለከቱ ስነ ሕዝብ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ባህሪያት የሚመዘገቡበት ቅጽ ነው።

የሞት መዝገብ እያንዳንዱን ሞትና ሟችን የሚመለከቱ ስነ ሕዝብ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ባህሪያት የሚመዘገቡበት ቅጽ ነው።

የጋብቻ መዝገብ እያንዳንዱን ጋብቻና ተጋቢዎችን የሚመለከት፡ ስነ ሕዝብ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ባህሪያት የሚመዘገቡበት ቅጽ ነው።

የፍቺ መዝገብ እያንዳንዱን ፍቺና ተፋቺዎችን የሚመለከት፡ ስነ ሕዝብ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ባህሪያት የሚመዘገቡበት ቅጽ ነው።

### 3.1.2 የወሳኝ ኩነቶች መዝገቦች ቅርጽ

የወሳኝ ኩነቶች መዝገቦች በሶስት አማራጭ ቅርጾች ሊዘጋጁ ይችላሉ። እነሱም ጥራዝ ወይም ባህረ መዝገብ፣ ብትን ወረቀቶችና ካርዶች ናቸው። የምዝገባው ሥርዓት ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ በደረሰባቸው አገሮች የወሳኝ ኩነቶች መረጃ በኮምፒዩተሮች ተመዝግቦ ይቀመጣል።

ጥራዝ ወይም ባህረ መዝገብ በመጽሐፍ መልክ የሚዘጋጅ፣ ጠንካራ ልባስ ያለውና <u>ለአንድ ዓመት የሚበቁ</u> ቅጾችን የያዘ ዶኩሜንት ነው።

ጥራዞች ቅጾችን በአንድነት አቅፈው ይይዛሉ። የቅጾች መጥፋትንና መሠረቅን ያስወግዳሉ። የጥራዞች ችግር መጠናቸው ትልቅ በመሆኑ ለአያያዝ አይመቹም። ለተለያዩ ጉዳዮች (ለምሳሌ የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ፣ ለሕግና ለአስተዳደር አገልግሎቶች ኮፒዎችን ለመላክ) ፎቶ ኮፒ ለማድረግ ወይም ገንጥሎ ለመላክ አይመችም። ቅጾቹ የተጠረዙ ስለሆነ መረጃው መመዝገብ ያለበት በእጅ ጽሑፍ ነው።

ባለብትን ቅጠሎችና የካርድ መዝገቦች ተመሳሳይ ናቸው። ልዩነታቸው ባለ ብትን ቅጠል መዝገቦች ስስ ወረቀቶች ሲሆኑ ካርዶች ጠንካራ፣ ወፍራምና ለብዙ ጊዜ ሊቆዩ

የሚችሉ ወረቀቶች ናቸው። አንድ የወሳኝ ኩነት በአንድ ካርድ ወይም በአንድ ብትን ቅጠል መመዝገብ አለበት።

የብትን ቅጠሎችና የካርድ መዝገቦች አቀማመጥ በቁጥር፣ በፊደል ወይም በሌላ ቅደም ተከተል ሊሆን ይችላል። እንዳይጠፉ እየተበሱ በቀለበት ፋይሎች መቀመጥ አለባቸው። በተለይ ካርዶች በሚቆለፍና ተለክቶ በተሰራ ሳጥን ወይም በፋይሊንግ ካቢኔት መቀመጥ አለባቸው።

### 3.1.3 የወሳኝ ኩነቶች መዝገቦች ይዘት

የወሳኝ ኩነቶች መዝገቦች ይዘት መሠረቱ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጥቅሞችን ለማሳካት መሆን ይገባዋል። ይኸውም የሚመዘገቡት መረጃዎች ለሕግ፣ ለአስተዳደርና ለስታቲስቲካዊ ተግባር የሚጠቅሙ መሆን ይገባቸዋል።

የመዝገቦች ይዘት በሁለት ይከፈላል። እነሱም መሠረታዊና ጠቀሜታ ያላቸው በመባል ይታወቃሉ።

<u>መሠረታዊ መረጃዎች</u> በማንኛውም የወሳኝ ኩነቶች መዝገብ ላይ መታየት ያለባቸው ናቸው። እነዚህ መረጃዎች የምዝገባውም ሆነ የስታቲስቲክስ ዕድገት በየትኛውም ደረጃ ቢሆንም በመዝገቦች ውስጥ መጨመር አለባቸው። በመረጃ ጥንቅር ወቅትም በሠንጠረዥ ተዘጋጅተው መታየት አለባቸው።

<u>ጠቀሜታ ያላቸው መረጃዎች</u> በየወቅቱ ለሕግ፣ ለአስተዳደርና ለስታቲስቲክስ አገልግሎት አስፈላጊነታቸው እየታየ በመዝገቡ የሚጨመሩ ናቸው።

ከዚህ ቀጥሎ የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍች መዝገቦች ይዘት ዝርዝር ተመልክቷል።

ሀ. የልደት መዝገብ ይዘት

- የምዝገባ ጽ/ቤት የሚገኝበት አካባቢ
- ሕፃኑን የሚመለከት
- የሕፃኑን እናት የሚመለከት
- የሕፃኑን አባት የሚመለከት
- አስመዝጋቢን የሚመለከት
- የልደት መፈፀም ማረጋገጫ
- አስተያየት፣
- የአስመዝጋቢና የመዝጋቢ ስምና ፊርማ

ለ. የሞት መዝገብ ይዘት

- የምዝገባው ጽ/ቤት የሚገኝበት አካባቢ
- ሟችን የሚመለከት
- አስመዝጋቢን የሚመለከት
- የሞት መፈፀም ማረጋገጫ
- አስተያየት፣
- የአስመዝጋቢና የመዝጋቢ ስምና ፊርማ

ሐ. የጋብቻ መዝገብ ይዘት

- የምዝገባ ጽ/ቤት የሚገኝበት አካባቢ
- ሙሽራውንና ሙሽሪትን የሚመለከት
- ጋብቻውን የሚመለከት
- የጋብቻው መፈፀም ማረጋገጫ፣
- አስተያየት፣
- የሙሽራውና የሙሽሪት ስምና ፊርማ።

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የክልል ሀ አስተዳደር

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽህፈት ቤት

የልደት መዝገብ

| ክፍል 1 የምዝገባ አካባቢ መለያ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1.1 ክልል | 1.2 ዞን | 1.3 ወረዳ | 1.4 ገጠር/ከተማ | 1.5 ቀበሌ | 1.6 የቤት ቁጥር |
| | | | | | |

| 2 ሕፃኑን የሚመለከት | 3 የሕፃንኑን እናት የሚመለከት | 4 የሕፃኑን አባት የሚመለከት |
|---|---|---|
| 2.1 ስም | 3.1 ስም | 4.1 ስም |
| 2.2 ፆታ | 3.2 ዕድሜ | 4.2 ዕድሜ |
| 2.3 የተወለደበት ቀን | 3.3 መደበኛ መኖሪያ | 4.3 መደበኛ መኖሪያ |
| 2.4 የተወለደበት ስፍራ | 3.4 ብሔረሰብ | 4.4 ብሔረሰብ |
| 2.5 በልደት ጊዜ እርዳታ | 3.5 ዜግነት | 4.5 ዜግነት |
| 2.6 የምዝገባ ቁጥር | 3.6 የትምህርት ደረጃ | 4.6 የትምህርት ደረጃ |
| 2.7 የተመዘገበበት ቀን | 3.7 የጋብቻ ሁኔታ | 4.7 የጋብቻ ሁኔታ |

| 5 አስመዝጋቢን የሚመለከት | 6 ለልደት ማረጋገጫ የቀረበ መረጃ | 7 አስተያየት |
|---|---|---|
| 5.1 ስም | 6.1 የሀኪም ሰርቲፊኬት | |
| 5.2 ዝምድና | 6.2 የዓይን ምስክር | |
| 5.3 መደበኛ መኖሪያ | ስም | |
| | መደበኛ መኖሪያ | |
| | ስም | |
| | መደበኛ መኖሪያ | |

| 8 የመዝጋቢ፣ የአስመዝጋቢ፣ የምስክርና የምዝገባ ጽህፈት ቤት ሓላፊ ስም፣ ፊርማና ቀን | | | |
|---|---|---|---|
| 8.1 ደረጃ | 8.2 ስም | 8.3 ፊርማ | 8.4ቀን |
| መዝጋቢ | | | |
| አስመዝጋቢ | | | |
| ምስክር | | | |
| የምዝገባ ጽ/ቤት ሓላፊ | | | |

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የክልል ሀ አስተዳደር

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽህፈት ቤት

# የሞት መዝገብ

| ክፍል 1 የምዝገባ አካባቢ መለያ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1.1 ክልል | 1.2 ዞን | 1.3 ወረዳ | 1.4 ገጠር/ከተማ | 1.5 ቀበሌ | 1.6 የቤት ቁጥር |
| | | | | | |

| ክፍል 2 ሟችን የሚመለከት | | |
|---|---|---|
| 2.1 ስም | 2.6 የትምህርት ደረጃ | 2.11 የሞተበት ቀን |
| 2.2 ፆታ | 2.7 የጋብቻ ሁኔታ | 2.12 የሞተበት ስፍራ |
| 2.3 ዕድሜ | 2.8 የሥራ ዓይነት | 2.13 የተመዘገበበት ቀን |
| 2.4 ዜግነት | 2.9 መደበኛ መኖሪያ | 2.14 የምዝገባ ቁጥር |
| 2.5 ብሔረሰብ | 2.10 የሞት ምክንያት | 2.15 በሞት ጊዜ የተደረገ እርዳታ |

| ክፍል 3 አስመዝጋቢን የሚመለከት | ክፍል 4 ለሞት ማረጋገጫ የቀረበ መረጃ | ክፍል 5 አስተያየት |
|---|---|---|
| 3.1 ስም | 4.1 የሀኪም ሰርቲፊኬት | |
| 3.2 ዝምድና | 4.2 የዓይን ምስክር | |
| 3.3 መደበኛ መኖሪያ | ስም | |
| | መደበኛ መኖሪያ | |
| | ስም | |
| | መደበኛ መኖሪያ | |
| | | |

| ክፍል 6 የመዝጋቢ፣ የአስመዝጋቢ፣የምስክርና የምዝገባ ጽህፈት ቤት ሓላፊ ስም፣ ፊርማና ቀን | | | |
|---|---|---|---|
| 6.1 ደረጃ | 6.2 ስም | 6.3 ፊርማ | 6.4 ቀን |
| መዝጋቢ | | | |
| አስመዝጋቢ | | | |
| ምስክር | | | |
| የምዝገባ ጽ/ቤት ሓላፊ | | | |

ሀ. የፍቺ መዝገብ ይዘት

- የምዝገባው ጽ/ቤት አካባቢ መለያ
- ተፋቺዎች ባልና ሚስት የሚመለከት
- የፍቺው መፈፀም ማረጋገጫ፡
- አስተያየት
- የባልና ሚስት ስምና ፊርማ፡
- የምስክሮች ስምና ፊርማ

ከዚህ ቀጥሎ ብትንና የአንድ ኩነት መመዝገቢያ የልደት፡ የሞት፡ የጋብቻና የፍቺ መዝገቦች ቀርበዋል።

## 3.2 የወሳኝ ኩነቶች ምስክር ወረቀቶች

ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ዓብይ ተግባራት አንዱና ዋንኛው ለተመዘገቡ ውሳኝ ኩነቶች (ልደት፡ ሞት፡ ጋብቻና ፍቺ) ሕጋዊ የምሥክር ወረቀቶች መስጠት ነው። ምሥክር ወረቀቶች ጥቅማቸው ለሕግ፡ ለአስተዳደርና ለተለያዩ አገልግሎቶች በማስረጃነት እንዲቀርቡ ነው። ምስክር ወረቀቶች ከላይ ለተጠቀሱት አገልግሎቶች እንደማስረጃ በሚቀርቡበት ጊዜ ተቀባይነት እንዲኖራቸው በምዝገባ ሕጉ ይደነገጋል።

በተጨማሪም ሕጉ ምስክር ወረቀቶች እንዴት መስጠት እንዳባለቸው፡ ይዘታቸው ምን መሆን እንዳለበትና ቅርጻቸውን ጭምር በስፋት መግለፅ ይኖርበታል። ለምሣሌ ምስክር ወረቀቱ፣ የመዝገቡ ፎቶ ኮፒ ወይስ ከመዝገቡ የተመረጡ መረጃዎች በሌላ ቅጽ ተሞልተው መስጠት አለባቸው? የሚለው በሕጉ መደንገግ አለበት። በተጨማሪም የምስክር ወረቀቱ፣ በእጅ ወይስ በጽህፈት መኪና የተጻፈ ወይስ በሌላ ዘዴ የተሞሉ መረጃዎችን መያዝ እንዳለበት መደንገግ አለበት።

### 3.2.1 የምስክር ወረቀቶች ዓይነት

የወሳኝ ኩነቶች ምስክር ወረቀቶች ከሚከተሉት ሶስቱ በአንዱ ሊዘጋጁ ይችላሉ።

- በወሳኝ ኩነቶች መዝገቦች የተሞሉት ወሳኝ ኩነቶች መረጃዎች እንዳሉ በልዩ ቅጽ በእጅ ጽሁፉ ወይም በጽህፈት መኪና የተገለበጡ
- በወሳኝ ኩነቶች መዝገቦች የተሞሉት መረጃዎች እንዳሉ ወይም የተመረጡት ፎቶ ኮፒ የተደረጉ
- በኮምፒዩተር የተዘጋጁ

የምሥክር ወረቀቱ መረጃ ከዋናው መዝገብ ሲወስድ ስህተት እንዳይፈጠር ጥንቃቄ ያስፈልገዋል። ይህ አሠራር በፎቶ ኮፒ ከሚዘጋጁት የበለጠ ጊዜ ይወስዳል።

የምሥክር ወረቀቶች ትክክለኛነታቸው በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የበላይ ኃላፊዎች ፊርማ መጽደቅ አለባቸው።

### 3.2.2 የወሳኝ ኩነቶች ምስክር ወረቀቶች ይዘት

ቀደም ብሎ እንደተገለፀው የወሳኝ ኩነቶች ምስክር ወረቀቶች በወሳኝ ኩነቶች መዝገቦች የሠፈሩትን መረጃዎች እንዳሉ ሙሉ በሙሉ ወይም የተመረጡትን ብቻ ሊይዙ ይችላሉ።

እያንዳንዱ የምስክር ወረቀት እንደየሁኔታው የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዝ ይችላል።

ሀ. የልደት ምስክር ወረቀት ይዘት

የመዝገብ ቁጥር፣ የሕፃኑ ስም፣ የሕፃኑ ፆታ፣ የተወለደበት ቀን፣ ወር፣ ዓመት፣ የተወለደበት ቦታ፣ ዜግነት፣ ብሔረሰብ፣ ሃይማኖት፣ የአባት ስም፣ የእናት ስም፣ የምስክር ወረቀቱ የተሰጠበት ቀን፣ ወር፣ ዓመት፣ የምስክር ወረቀቱ የተሰጠበት ቦታ፣ አስተያየት፣ የመዝጋቢ/የምዝገባ ጽ/ቤት ሹም ስምና ፊርማ፣ ማህተም።

ለ. የሞት ምስክር ወረቀት ይዘት

የመዝገብ ቁጥር፣ ስም፣ የሟች ጾታ፣ ዕድሜ፣ የተወለደበት ቀን፣ ወር፣ ዓመት፣ ዜግነት፣ ብሔረሰብ፣ ሃይማኖት፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የሞተበት ቀን፣ ወር፣ ዓመት፣ የሞተበት ቦታ፣ የምስክር ወረቀቱ የተሰጠበት ቦታ፣ አስተያየት፣ የመዝጋቢ የምዝገባ ጽ/ቤት ሹም ስምና ፊርማ፣ ማህተም።

ሐ. የጋብቻ ምስክር ወረቀት ይዘት

የመዝገብ ቁጥር፣ ስም፣ ዕድሜ፣ የተወለዱበት ቀን፣ ወር፣ ዓመት፣ የተወለዱበት ቦታ፣ ዜግነት፣ ብሔረሰብ፣ ሃይማኖት፣ የምስክር ወረቀቱ የተሰጠበት ቀን፣ ወር፣ ዓመት፣ የምስክር ወረቀቱ የተሰጠበት ቦታ፣ አስተያየት፣ የመዝጋቢ /የምዝገባ ጽ/ቤት ሹም ስምና ፊርማ፣ ማህተም።

መ. የፍቺ ምስክር ወረቀት ይዘት

የመዝገብ ቁጥር፣ ስም፣ ዕድሜ፣ የተወለዱበት ቀን፣ ወር፣ ዓመት፣ የተወለዱበት ቦታ፣ ዜግነት፣ ብሔረሰብ፣ ሃይማኖት፣ የምስክር ወረቀቱ የተሰጠበት ቀን፣ ወር፣ ዓመት፣ የምስክር ወረቀቱ የተሰጠበት ቦታ፣ አስተያየት፣ የመዝጋቢ/የምዝገባ ጽ/ቤት ሹም ስምና ፊርማ፣ ማህተም።

ከዚህ ቀጥሎ የልደት የሞት የጋብቻና የፍቺ የምስክር ወረቀቶች ቀርበዋል፡፡

## 3.3 የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሌላው ተግባር ለስታቲስቲክስ ሥራ የሚውል መረጃ መሰብሰብ ነው፡፡ መዝጋቢው ለእያንዳንዱ ወሳኝ ኩነት የስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ ይሞላል፡፡ የስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ የወሳኝ ኩነቶች ብዛት፣ ወሳኝ ኩነቶችንና ከወሳኝ ኩነቶች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ግለሰቦች የሚመለከቱ ሥነ ሕዝብ፣ ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ መረጃዎች በመዝጋቢው ተሞልተው ወደ ወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ጽ/ቤት የሚተላለፍበት ቅጽ ነው፡፡ ለስታቲስቲክስ አገልግሎት የሚውሉት መረጃዎች ከመዝገቡ፣ ለምዝገባው ከቀረቡት ሌሎች ዶክመንቶችና ከአስመዝጋቢው ይወሰዳሉ፡፡

### 3.3.1 የስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ ዓይነቶች

የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ በሁለት መንገድ ሊዘጋጅ ይችላል፡፡ ይኸውም የተናጠልና የጋራ ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ ናቸው፡፡

<u>የተናጠል ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ</u> የአንድ ወሳኝ ኩነት መረጃ ብቻ ይይዛል፡፡ ለምሣሌ የአንድ ልደት ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ የአንድ ልደት መረጃ ብቻ ይይዛል፡፡ የተናጠል ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ ጥቅም አንድን ልደት በተመለከተ ብዙ መረጃዎችን ሊይዝ ይችላል፡፡ ይኸውም በቂ ቦታ ስለሚኖረው ስለ ኩነቱ በርካታ መረጃዎች ሊይዝ ስለሚችል ነው፡፡

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የክልል ሀ አስተዳደር

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽህፈት ቤት

የልደት ሰርቲፊኬት

**Birth Certificate**

የምዝገባ ቁጥር

**Registration No.**

1 የህፃን ስም
**Name of Child**

2 የህፃኑ ፆታ
**Sex of Child**

3 የተወለደበት ቀን
**Date of Birth**

4 የተወለደበት ቦታ
**Place of Birth**

5 ዜግነት
**Citizenship**

6 ብሔረሰብ
**Nationality**

7 የአባት ስም
**Name of Father**

8 የእናት ስም
**Name of Mother**

9 ሰርቲፊኬት የተሰጠበት ቀን
**Date of Issue**

10 ሰርቲፊኬት የተሰጠበት ቦታ
**Place of Issue**

11 አስተያየት
**Remark**

| | ስም<br>**Name** | ፊርማ<br>**Signature** |
|---|---|---|
| 12 መዝጋቢ<br>**Registrar** | | |
| 13 የምዝገባ ጽ/ ቤት ኃላፊ<br>**Head of Registration Office** | | |

ማህተም

**Seal**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የክልል ሀ አስተዳደር

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽህፈት ቤት

የሞት ሰርቲፊኬት

## Death Certificate

የምዝገባ ቁጥር

Registration No. ______________

1 የሟች ስም
Name of Deceased ______________

2 የሟች ፆታ
Sex of Deceased ______________

3 የሟች ዕድሜ
Age of Deceased ______________

4 ዜግነት
Citizenship ______________

5 ብሔረሰብ
Nationality ______________

6 የሞተበት ቦታ
Place of Death ______________

7 የሞተበት ቀን
Date of Death ______________

8 የሞተበት ምክንያት
Cause of Death ______________

9 ሰርቲፊኬት የተሰጠበት ቀን
Date of Issue ______________

10 ሰርቲፊኬት የተሰጠበት ቦታ
Place of Issue ______________

11 አስተያየት
Remark ______________

| | ስም<br>Name | ፊርማ<br>Signature |
|---|---|---|
| 12 መዝጋቢ<br>Registrar | | |
| 13 የምዝገባ ጽ/ ቤት ኃላፊ<br>Head of Registration Office | | |

ማኅተም

Seal

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የክልል ሀ አስተዳደር

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽህፈት ቤት

የጋብቻ ሰርቲፊኬት

**Marriage Certificate**

የምዝገባ ቁጥር

**Registration No.**

1 የባል ስም

**Name of Husband**

2 የባል ዕድሜ

**Age of Husband**

3 የተወለደበት ቦታ

**Place of Birth**

4 የሚስት ስም

**Name of Wife**

5 የሚስት ዕድሜ

**Age of Wife**

6 የተወለደችበት ቦታ

**Place of Birth**

7 ጋብቻው የተፈጸመበት ቦታ

**Place of Marriage**

8 ጋብቻው የተፈጸመበት ቀን

**Date of Marriage**

9 ሰርቲፊኬት የተሰጠበት ቀን

**Date of Issue**

10 ሰርቲፊኬት የተሰጠበት ቦታ

**Place of Issue**

11 አስተያየት

**Remark**

| | ስም<br>**Name** | ፊርማ<br>**Signature** |
|---|---|---|
| 12 መዝጋቢ | | |
| **Registrar** | | |
| 13 የምዝገባ ጽ/ ቤት ሓላፊ | | |
| **Head of Registration Office** | | |

ማህተም

**Seal**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የክልል ሀ አስተዳደር

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽህፈት ቤት

የፍቺ ሰርቲፊኬት

**<u>Divorce Certificate</u>**

የምዝገባ ቁጥር

**Registration No.**

1 የባል ስም

**Name of Husband**

2 የባል ዕድሜ

**Age of Husband**

3 የተወለደበት ቦታ

**Place of Birth**

4 የሚስት ስም

**Name of Wife**

5 የሚስት ዕድሜ

**Age of Wife**

6 የተወለደችበት ቦታ

**Place of Birth**

7 ፍቺው የተፈፀመበት ቦታ

**Place of Divorce**

8 ፍቺው የተፈፀመበት ቀን

**Date of Divorce**

9 ሰርቲፊኬት የተሰጠበት ቀን

**Date of Issue**

10 ሰርቲፊኬት የተሰጠበት ቦታ

**Place of Issue**

11 አስተያየት

**Remark**

| | ስም<br>**Name** | ፊርማ<br>**Signature** |
|---|---|---|
| 12 መዝጋቢ<br>**Registrar** | | |
| 13 የምዝገባ ጽ/ ቤት ሓላፊ<br>**Head of Registration Office** | | |

ማህተም

**Seal**

የጋራ ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ ብዛት ያላቸው ተመሣሣይ ወሣኝ ኩነቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች ይሞሉበታል:: ለምሣሌ የብዙ ልደቶች ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ የብዙ ልደቶችን መረጃ ይይዛል:: የጋራ ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ ከተናጠል ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ ጋር ሲወዳደር ወጪን ከመቆጠቡም በላይ ለአጠቃቀም አመቺ ነው::

በስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ የሚሞሉት መረጃዎች ለስታቲስቲክስ ሥራ ብቻ ሲውሉ በወሳኝ ኩነቶች መዝገቦች የተሞሉት መረጃዎች ለሕግ፣ ለአስተዳደርና ለስታቲስቲክስ አገልግሎት ይውላሉ::

በአንዳንድ አገሮች የወሳኝ ኩነቶች መዝገብ እንደ ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ ያገለግላል:: በዚህ ጊዜ የወሳኝ ኩነት መዝገቦች ለሕግ፣ ለአስተዳደርና፣ ለስታቲስቲክስ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን አጠቃለው ይይዛሉ:: በሌሎች አገሮች ደግሞ የወሳኝ ኩነት መዝገቦችና የስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጾች ተለያይተው ለየብቻ ይዘጋጃሉ:: በዚህ ጊዜ መዝጋቢው በወሳኝ ኩነት መዝገቦች መሠረታዊ የሆኑና ለሕግና ለአስተዳደር የሚያገለግሉ መረጃዎችን ከሞላ በኋላ በስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ በመዝገቡ ከሞላቸው መረጃዎች በተጨማሪ ለስታቲስቲክስ ሥራ የሚያገለግሉ መረጃዎችን አስመዝጋቢን በመጠየቅ ወይም ከቀረቡት ዶክሜንቶች በመውሰድ ይሞላል::

ለስታቲስቲክስ ሪፖርትና ለመዝገብ የተለያዩ ቅጾችን መጠቀም በመዝጋቢው ላይ የሥራ ጫና ከመጨመሩም ባሻገር ተጨማሪ ወጪ ያስከትላል:: ሆኖም የስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጾችንና መዝገቦችን ለየብቻ ማድረግ ምንም አማራጭ የለውም:: ምክንያቱም አንደኛ የስታቲስቲክስ መረጃ ሚስጥራዊ ነው:: ሁለተኛ በዛ ያለ መረጃ ይፈልጋል::

### 3.3.2 የስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ ይዘት

የስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ ይዘት የሚወሰነው በአገር አቀፍ የስታቲስቲክስ መረጃ ፍላጐት ላይ ይመሠረታል፡፡ ሆኖም መረጃዎቹ መልስ ሰጭዎች ለመመለስ ፍላጐት ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪ የተወሳሰቡና አስቸጋሪ የሆኑ መረጃዎችን ከመጠየቅ መቆጠብ ያስፈልጋል፡፡

በስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ እንዲካተቱ በተባበሩት መንግሥታት የተጠቆሙት የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና፣ የፍች መረጃዎችና ከነዚሁ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ግለሰቦች የሚመለከቱ መረጃዎች ቀጥለው ተዘርዝረዋል፡፡

#### ሀ. የልደት ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ ይዘት

የልደት ባህርይ- በልደት ወቅት የተደረገ እርዳታ፣ የልደት ቀን ፣ ወርና ዓመት፣ የልደት የምዝገባ ቀን፣ ወርና ዓመት፣ ልደቱ የተከናወነበት ቦታ፣ የልደት ዓይነት/ነጠላ ወይም መንታ/፡፡

የሕፃኑ ባህርይ- በጋብቻ ወይም ከጋብቻ ውጭ የተወለደ፣ ፆታ፣ በልደት ጊዜ ክብደት፣ የሕፃኑ እናት ባህሪይ- ዕድሜ፣ ጋብቻ የተፈጸመበት ቀን/ ወር/ዓመት/፣ በሕይወት የተወለዱ ልጆች ብዛት፣ መደበኛ የመኖሪያ ቦታ፡፡

#### ለ. የሞት ስታቲስቲካል ሪፖርት ቅጽ ይዘት

የሞት ባህሪይ- የሞት ምክንያት፣ ሞቱን ያረጋገጠው አካል፣ ሞት የተፈፀመበት ቀን፣ ወር፣ ዓመት፣ ሞት የተመዘገበበት ቀን፣ወር፣ ዓመት፣ ሞት የተፈፀመበት ሥፍራ፡፡

የሟች ባህሪይ- ፆታ፣ የሟች ዕድሜ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ መደበኛ መኖሪያ ቦታ

### ሐ. የጋብቻ የስታቲስቲክስ ሪፓርት ቅጽ ይዘት

የጋብቻ ባህሪይ- የጋብቻ ቀን፣ ወርና ዓመት፣ ጋብቻው የተመዘገበበት ቀን፣ ወር፣ ዓመት፣ ጋብቻው የተፈፀመበት ሥፍራ፣ የጋብቻ ዓይነት (ሲቪል፣ ሃይማኖታዊና ባህላዊ)።

የሙሽሮች ባህሪይ- ዕድሜ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ መደበኛ የመኖሪያ ቦታ

### መ. የፍቺ የስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ ይዘት

የፍቺ ባህሪይ- የፍቺ ቀን/ ወር/ ዓመት፣ ፍቺው የተመዘገበበት ቀን፣ ወር፣ ዓመት፣ ፍቺው የተከናወነበት ቦታ።

የተፋቺዎች ባህሪይ- ዕድሜ፣ በጋብቻ ላይ የቆዩበት ጊዜ፣ ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ብዛት፣ መደበኛ መኖሪያ ቦታ።

ከዚህ ቀጥሎ የልደት የሞት የጋብቻና የፍቺ ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጾች ቀርበዋል።

## 3.4 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ መመሪያ

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ መመሪያ የፅንሰ ሃሣቦች ፍችና ትርጉም፣ የመረጃ አጠያየቅ፣ አመዘጋገብ፣ የዶክሜንቶች አያያዝ፣ አጠባበቅ፣ አሳላክ፣ የስታቲስቲክስ ሪፓርት ቅጽ አሞላል... ወዘተ መመሪያ አካቶ የያዘ ዶክሜንት ነው።

መመሪያው በአጠቃላይ የምዝገባ ሥርዓትና ተግባሩ በተለያዩ አካባቢዎች በተመሣሣይ ሁኔታ እንዲካሄድ የሚያደርግ ዶክሜንት ነው:: መመሪያው በምዝገባ ሕግ የተደነገጉትን ድንጋጌዎችና የስታቲስቲክስ መረጃ አሰባሰብ ሕግን መሠረት በማድረግ የሚዘጋጅ ዶክሜንት ነው::

መዝጋቢዎችና ከምዝገባው ጋር ግኑኝነት ያላቸው ሁሉ መመሪያው ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ሥልጠና እንዲሰጣቸው ያስፈልጋል:: መመሪያው በእያንዳንዱ ምዝገባ ክፍል መቀመጥ ይኖርበታል::

# ምዕራፍ 4

## የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅር

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ካሉት ሦስቱ ባህርያት አንዱ ቋሚነት ነው:: ሥርዓቱ በሕግ የተደነገገ ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅር እንዲኖረው ያስፈልጋል:: ይህም ተከታታይና አስገዳጅ ምዝገባ ለማካሄድ፣ መዝገቦችንና ሌሎች የምዝገባ ዶክሜንቶችን ደህንነት ለመጠበቅ፣ ዶኩሜንቶችን ከየምዝገባ ቦታዎች ሰብስቦ በአንድ ማዕከል ለማከማቸት፣ ዶክሜንቶችን ለሕጋዊ፣ ለአስተዳደራዊና ለስታቲስቲካዊ አገልግሎት እንዲውሉ ለማድረግ ያስችላል::

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት በአዲስ መልክ ሲቋቋም በቅድሚያ ከሚታሰቡት ጉዳዩች አንዱና ዋንኛው በአገሩ ካለው ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ሥርዓት ጋር የሚጣጣም ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅር መዘርጋት ነው::

በዚህ ምዕራፍ በክፍል 4.1-4.2 በተለያዩ ሥርዓቶች በሚተዳደሩ አገሮች ተግባራዊ የሆኑ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅሮችን በተመለከተ ለማቅረብ ይሞክራል:: በክፍል 4.3 በኢትዮጵያ የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ሊኖረው የሚገባው ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅር ይቀርባል::

## 4.1 ወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅር ዓይነቶች

### 4.1.1 ወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ድርጅታዊ መዋቅር ዓይነቶች

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ድርጅታዊ መዋቅር በ2 ይከፈላሉ:: እነሱም የተማከለና ያልተማከለ ናቸው::

#### ሀ. የተማከለ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት

የተማከለ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት በአገር አቀፍ (በማዕከል) ጽ/ቤት ያለው ሆኖ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ከከፍተኛው እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር እርከኖች በመዘርጋት ከማዕከል ሆኖ የምዝገባውን ሂደት የሚቆጣጠር ሥርዓት ነው(መዋቅር 1 ይመልከቱ):: ምዝገባው የሚካሄደው በዝቅተኛዎቹ የገጠርና የከተማ የአስተዳደር እርከኖች (ቀበሌዎች) ይሆናል:: የምዝገባ መመሪያዎችና አስተዳደራዊ ትዕዛዞች የሚመነጩት ከማዕከሉ ሲሆን የተለያዩ የአስተዳደር ክፍሎችን ደረጃ እየጠበቁ እስከ ታችኛው የአስተዳደር እርከን (ቀበሌ) ይደርሣሉ:: መረጃ የተሞላባቸው መዝገቦች፣ ሴርቲፊኬቶችና የስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጾች ከምዝገባው ጽ/ቤቶች ተሰብስበው ወደ አገር አቀፍ (ማዕከላዊ) የምዝገባ ጽ/ቤት ይመጣሉ:: ማዕከላዊው የምዝገባ ጽ/ቤት በየአስተዳደር ክፍሎች ከሚገኙ የምዝገባ ጣቢያዎች የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለሕግ፣ ለአስተዳደርና ለስታቲስቲክስ አገልግሎት እንዲውሉ ያዘጋጃል::

የተማከለ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት የሚከተሉት ጥቅሞች ይኖሩታል::

መዋቅር 1 የተማከለ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት




መዋቅር 2 ያልተማከለ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዓት



- ጽንሰ ሃሳቦች፣ ትርጉሞችና መመሪያዎች ተመሣሣይ ይሆናሉ።
- ተመሣሣይ ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ አመራር ይኖራል።
- ተመሣሣይ የምዝገባ ሕግ ይኖራል።
- መዝገቦችና ሌሎች ዶክሜንቶች በአንድ ማዕከል እንዲከማቹ ይደረጋል።
- ማዕከላዊ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤት የሚከተሉት ተግባሮች ይኖሩታል።
- መዝገቦች፣ ቅጾች፣ መመሪያዎች፣ ትዕዛዞች... በየጊዜው በየአስተዳደር ክፍሉ መድረሳቸውን ይከታተላል።
- የምዝገባውን የቀን ተቀን ክንውኖችን ይቆጣጠራል።
- ህብረተሰቡን ይቀሰቅሳል፣ ያስተምራል
- አዳዲስ ምዝገባ ጣቢያዎችን በየጊዜው እየተከታተለ ያቋቁማል።
- የመዝገቦችና የሲርተፊኬቶች ኮፒ ወደ ማዕከል መላካቸውን ይቆጣጠራል።
- የስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጾች ወደ ስታቲስቲክስ ቢሮ መላካቸውን ይከታተላል።
- ሕጉ በትክክልና በተመሣሣይ ሁኔታ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል።
- በየጊዜው ጥናት በማድረግ የምዝገባውን ውጤት ይገመግማል ያሻሽላል
- የተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማስተባበር የተለያዩ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል።

የተባበሩት መንግሥታት በየአገሩ የተዘረጉትን የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ድርጅታዊ መዋቅርን አስመልክቶ ላደረገው ጥናት መልስ ከሰጡት 103 አገሮች መካከል በ88ቱ ሥርዓቱ

የተማከለ ሆኖ ተገኝቷል። መልስ ከሰጡት 19 የአፍሪካ አገሮች በሙሉ ሥርዓቱ የተማከለ ነው ( ሠንጠረዥ 4.1 ይመልከቱ)።

ሠንጠረዥ 4.1 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅር ዓይነቶች

| አገሮች | ድምር | ራሣቸውን ችለው የተቋቋሙ | በሌሎች መ/ቤቶች ሥር የሚተዳደሩ | ያልተ ማከሉ |
|---|---|---|---|---|
| አፍሪካ | 19 | 8 | 11 | 0 |
| ሰ.አሜሪካ | 15 | 7 | 3 | 5 |
| ደ.አሜሪካ | 10 | 5 | 2 | 3 |
| ኤሺያ | 20 | 15 | 5 | 0 |
| አውሮፓ | 32 | 15 | 11 | 6 |
| ኤሺያና | 7 | 5 | 1 | 1 |
| ድምር | 103 | 55 | 33 | 15 |

ምንጭ፡ UN, 1985. Hand Book of Vital Statistics Systems and Methods, Volume II Review of National Practices.

የተማከለ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት በአብዛኛው የተዘረጋው አሀዳዊ መንግሥት ሥርዓት በሚከተሉ የአገሩ ስፋትና የሕዝቡ ቁጥር አነስተኛ በሆነባቸው አገሮች ነው። ይህ ሥርዓት በአብዛኛው የሚገኘው እንግሊዝኛ ተናጋሪ በሆኑ አገሮች ነው።

## ለ. ያልተማከለ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት

ባልተማከለ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ባመዛኙ ማዕከላዊ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤት የለም። እያንዳንዱ

የአስተዳደር ክልል የራሱን የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በኃላፊነት ያካሂዳል(መዋቅር 2 ይመልከቱ)። በእያንዳንዱ የአስተዳደር ክልል ዋና ከተማ የአስተዳደር ክልሉ የምዝገባ ጽ/ቤት ይኖራል። ይህ ጽ/ቤት በየንዑሣን የአስተዳደር ክፍሎችና በየምዝገባ ጣቢያዎች የሚካሄዱትን ምዝገባዎች ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ይመራል። የምዝገባው ሕግ፣ ደንብና መመሪያ በየአስተዳደር ክልሉ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ይሆናል። በሌሎች አገሮች በአገር አቀፍ ደረጃ ሕግ ይኖርና እያንዳንዱ ክልል ይህንን ሕግ መሠረት በማድረግ የሞዴል ሕግ ይቀርጻል። በሠንጠረዥ 4.1 እንደተመለከተው ድርጅታዊ መዋቅርን አስመልክቶ መልስ ከሰጡት 103 አገሮች መካከል በ15ቱ አገሮች ሥርዓቱ ያልተማከለ ነው።

### 4.1.2 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት አስተዳደራዊ መዋቅር ዓይነቶች

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት አስተዳደራዊ መዋቅር በሁለት ይከፈላል። እነርሱም ራሱን ችሎ የሚተዳደርና ራሱን ችሎ የማይተዳደር ናቸው።

#### ሀ. ራሱን ችሎ የሚተዳደር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት

ራሱን ችሎ የሚተዳደር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት በቀጥታ በማዕከላዊ ወይም በፌዴራል መንግሥት ቁጥጥር ሥር ሆኖ የራሱ በጀት ያለውና ራሱን በራሱ የሚያስተዳድር ነው። ይህ ተቋም የተማከለና በየአስተዳደር ክልሉ የራሱ ቅርንጫፍ የምዝገባ ጽ/ቤቶች የሚኖሩት ይሆናል። ቀደም ብሎ በተጠቀሰው የተባበሩት መንግሥታት ጥናት መሠረት ከ103 አገሮች መካከል በ55ቱ ሥርዓቱ ራሱን ችሎ የሚተዳደር ነው። የዚህ ዓይነት ሥርዓት በብዛት የሚገኘው በእንግሊዝኛ ተናጋሪ አገሮች (ለምሳሌ ሕንድ፣ ኬንያ፣

ስኮትላንድ፣ ሰሜን አይርላንድ) ሲሆን ሬጅስተር ጀነራል ጽ/ቤት (National Register General Office) ተብሎ ይጠራል (መዋቅር 3 ይመልከቱ)::

## ለ. ራሱን ችሎ የማይተዳደር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት

ራሱን ችሎ የማይተዳደር የምዝገባ ሥርዓት ከበላዩ ሆኖ የሚያስተዳድር መንግሥታዊ መሥሪያ ቤት ይኖራል:: በሌሎች ሥር የሚተዳደር የምዝገባ ሥርዓት የተማከለም ያልተማከለም ሊሆን ይችላል:: የተማከለ ሆኖ በሌላ የመንግሥት መ/ቤት ሥር በሚተዳደር የምዝገባ ሥርዓት በየንዑስ የአስተዳደር ክፍሎች ያሉት የምዝገባ ጽ/ቤቶች የሚተዳድሩት በአስተዳዳሪው መ/ቤት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሥር ይሆናሉ(መዋቅር 4 ይመልከቱ):: በመሆኑም በአስተዳዳሪነት የሚመደበው ሚ/ር መ/ቤት በየአስተዳደር ክልሎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንዲኖሩት ያስፈልጋል::

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓትን የሚያስተዳድረው መ/ቤት ከአገር አገር ይለያያል:: በአብዛኛዎቹ አገሮች የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የሚተዳደረው በአገር አስተዳደር ሚ/ር መሥሪያ ቤት ሥር ነው:: ቀደም ብሎ በተጠቀሰው የተባበሩት መንግሥታት ጥናት መሠረት በተገኘው መረጃ ለጥናቱ መልስ ከሰጡት 103 አገሮች መካከል በ33ቱ ሥርዓቱ የሚተዳደረው በአገር አስተዳደር ሚ/ር መ/ቤት ሥር ነው:: ቀጥሎ በተለይ በእንግሊዝኛ ተናጋሪ አገሮች ሥርዓቱ የሚተዳደረው በፍትህ ሚኒስቴር ሥር ነው:: እንዲሁም በአንዳንድ አገሮች አስተዳዳሪዎቹ መ/ቤቶች ጤና ጥበቃና ፕላን ሚኒስቴር መ/ቤቶች ናቸው::

ያልተማከለ ሆኖ በሌሎች መ/ቤቶች ሥር በሚተዳደር የምዝገባ ሥርዓት በየአንዳንዱ የአስተዳደር ክልል

መዋቅር 3

የተማከለና ራሱን ችሎ የሚተዳደር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት




መዋቅር 4

የተማከለና በሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሥር የሚተዳደር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት



የተቋቋመው የምዝገባ ጽ/ቤት በየክልሉ በሚገኙ መ/ቤቶች ሥር ሆኖ ከበላይ ምዝገባውን የሚቆጣጠረው ይኸው መ/ቤት ነው:: የአስተዳዳሪ መ/ቤት ምርጫም እንደየ አገሩና ክልሉ የአስተዳደር ሥርዓት መሠረት ነው:: (መዋቅር 2 ይመልከቱ)::

## 4.2 የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅር ዓይነቶች

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓትን ለማቋቋም ሲፈለግ በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓትና በወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት መካከል የሚኖረውን ግንኙነት አብሮ ማስብና ማቀድ ያስፈልጋል:: በርግጥ የሁለቱም ተግባር የተለያየና በተለያዩ መ/ቤቶች ሊከናወን የሚችል ነው::

የምዝገባ ጽ/ቤት ተግባር ወሳኝ ኩነቶችን መመዝገብ ሲሆን የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ተግባር የወሳኝ ኩነቶችን መረጃ መተንተን ማጠናቀርና ለስታቲስቲካዊ ጥቅም እንዲውሉ ማድረግ ነው:: ሆኖም የስታቲስቲክስ ቢሮው የምዝገባውን ተግባር የማስተባበር፣ የጽንስ ሃሣቦች ፍችና ትርጉም በማዘጋጀት መሣተፍ ይኖርበታል::

### 4.2.1 የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ድርጅታዊ መዋቅር ዓይነቶች

የተማከለ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ባለበት አገር የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት የተማከለም ያልተማከለም ሊሆን ይችላል:: እንዲሁም በተመሣሣይ ሁኔታ ያልተማከለ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ባለበት አገር የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት ሊማከልም ላይማከልም ይችላል::

### ሀ. የተማከለ የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት

በተማከለ የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት በአገር አቀፍ (በማዕከል) ደረጃ የተዋቀረ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ጽ/ቤት አለ(መዋቅር 5 ይመልከቱ)፡፡ በተማከለ የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት በተለያዩ አካባቢዎች የተቋቋሙት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽህፈት ቤቶች የተመዘገቡትን የወሳኝ ኩነቶችን መረጃ በስታቲስቲክስ ሪፓርት ቅጽ ሞልተው በተከታታይና በወቅቱ ለማዕከላዊው የወሣኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤት ይልካሉ፡፡ማዕከላዊው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤት መረጃውን ለማዕከላዊው የወሳኝ ኩነቶች ጽ/ቤት ይልካል፡፡ ማዕከላዊው የወሣኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ጽ/ቤት መረጃውን ተቀብሎ በመተንተንና በማጠናቀር ለተጠቃሚ ያዘጋጃል፡፡ ከዚህም ባሻገር ማዕከላዊው የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ጽ/ቤት የወሳኝ ኩነቶችን ምዝገባ መረጃ አመዘጋገብን፣ ሕጎችንና ደንቦችን፣ የጽንስ ሃሣቦች ፍቺና ትርጉሞች፣ የመረጃ አያያዝን፣ አጠባበቅን፣ አሳላክን... ወዘተ መመሪያዎችን ከምዝገባ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፡፡

### ለ. ያልተማከለ የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት

ያልተማከለ የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት ማዕከልነትን ያልጠበቀ እያንዳንዱ የአስተዳደር ክፍል የራሱን የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ የሚያዘጋጅበት ሥርዓት ነው፡፡ ባልተማከለ የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት በየአስተዳደር ክፍሉ በተቋቋሙት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽህፈት ቤቶች የተመዘገቡት መረጃዎች በየአስተዳደር ክፍሉ ወደ ተቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ጽ/ቤት ይልካሉ፡፡ የየአስተዳደር ክፍሉ የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ጽ/ቤቶችም የአስተዳደር ክፍሉን የወሳኝ ኩነቶች መረጃ

መዋቅር 5

የተማከለና በሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሥር የሚተዳደር የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት



ተንትነውና አጠናቅረው ለተጠቃሚዎች ያዘጋጃሉ (መዋቅር 6 ይመልከቱ)::

### 4.2.2 የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ አስተዳደራዊ መዋቅር ዓይነቶች

የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት አስተዳዳሪ መ/ቤቶችን በተመለከተ የተለያዩ አማራጮች ይኖራሉ::

<u>የመጀመሪያው አማራጫ</u> የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስን ሥርዓት በአንድ የመንግሥት መ/ቤት ሥር እንዲተዳደር ማድረግ ነው:: የዚህ ዓይነት አስተዳደራዊ መዋቅር የተማከለም ያልተማከለም ሊሆን ይችላል:: በተማከለው ሥርዓት የወሳኝ ኩነቶች ጽ/ቤት በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ መ/ቤት ሥር ወይም በሌላ የመንግሥት መ/ቤት ሥር ሊተዳደር ይችላል (መዋቅር 5 ይመልከቱ):: ባልተማከለው ሥርዓት የወሳኝ ኩነቱ ጽ/ቤት በእያንዳንዱ የአስተዳደር ክፍል በሚገኝ የመንግሥት መ/ቤት ሥር ይተዳደራል(መዋቅር 6 ይመልከቱ)::

የወሳኝ ኩነቶችን ስታቲስቲክስ በማዕከላዊ የስታቲስቲክስ ጽ/ቤት ሥር ማድረግ የወሳኝ ኩነቶች መረጃ በይበልጥ ለስታቲስቲክሱ ጥቅም በሚሰጡት ላይ እንዲያተኩር ያደርጋል:: ሌሎች መ/ቤቶች ከሚተዳደረው ሥርዓት ጋር ሲነፃፀር የሚሰበሰበውም መረጃ በጣም ሰፊ ያለና ጥልቀት ያለው ይሆናል::

ሆኖም ማዕከላዊው ስታቲስቲክስ ጽ/ቤት የሕዝብ ቆጠራንና የናሙና ጥናቶችን በሚያካሂድበት ጊዜ ለወሳኝ ኩነቶች ፕሮግራም ተገቢውን ትኩረት የመስጠት አቅሙ ይቀንሳል:: ምክንያቱም ሁሉንም ፕሮግራም በተመሣሣይ ሁኔታ ማካሄድ አቅም ስለማይኖረው ነው:: በመሆኑም በተከታታይ

የሚያዘጋጁት የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክሶች የጥራትና የጊዜ መዛባት ሊገጥማቸው ይችላል።

ሁለተኛው አማራጭ የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓቱ በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤት አስተዳደር ሥር እንዲሆን ማድረግ ነው (መዋቅር 3 ይመልከቱ)። ሆኖም የምዝገባ ሥርዓቱ የተቀረፀው ለሕጋዊ መረጃዎች ማግኛ ከሆነ የስታቲስቲክሱ ድርሻ አነስተኛና በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ይሆናል።

ሦስተኛው አማራጭ የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት ከእያንዳንዱ ኩነት ጋር ቀጥታ ግኑኝነት ካላቸው መንግሥታዊ መ/ቤቶች አስተዳደር ሥር ማድረግ ነው። ለምሳሌ የልደትና የሞት ስታቲስቲክስ በጤና ጥበቃ ሚ/ር እንዲዘጋጅ ማድረግ የጤና ስታቲስቲክስ በተሻለና ከተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር የሚሄድ የጤና መረጃ እንዲገኝ ሊያደርግ ይችላል። እንዲሁም ፍርድ ቤቶች የፍችና የጋብቻ ስታቲስቲክስ እንዲያዘጋጁ ማድረግ ለኩነቶቹ በፍርድ ቤቶች በኩል ትኩረት እንዲሰጥ ሊያደርግ ይችላል።

አራተኛው አማራጭ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባንና ስታቲስቲክስን በአንድ ሚ/ር መ/ቤት ሥር ማድረግ ነው። ይህ ሥርዓት የተማከለም ያልተማከለም ሊሆን ይችላል። በተማከለው ሥርዓት ምዝገባውና ስታቲስቲክሱ ሁለቱ በአንድነት በአንድ መ/ቤት ሥር በማዕከል ይቋቋማሉ። የምዝገባው ዘርፍ በየክልሉ የሚካሄዱትን ምዝገባዎች ሲከታተል የስታቲስቲክሱ ዘርፍ ደግሞ በየአስተዳደር ክልሉ የተመዘገቡትን መረጃዎች በምዝገባው ክፍል በኩል ተቀብሎ የየአስተዳደር ክልሉንና የአገር አቀፉን ስታቲስቲክስ ያዘጋጃል(መዋቅር 7 ይመልከቱ)።

መዋቅር 6 ያልተማከለና በሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሥር የሚተዳደር የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት



መዋቅር 7

የተማከለና በሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሥር ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጋር
በአንድነት የሚተዳደር የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት




መዋቅር 8

ያልተማከለና ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጋር በአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሥር የሚተዳደር
የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት



ባልተማከለው ሥርዓት ምዝገባውና ስታቲስቲክሱ በየአስተዳደሩ በሚገኝ አንድ መንግሥት መ/ቤት ሥር ይተዳደራሉ፡፡ የምዝገባ ክፍሉ ምዝገባን ሲከታተል የስታቲስቲክሱ ክፍል ከምዝገባው የተገኙትን የአስተዳደር ክፍሉን ስታቲስቲክስ ያዘጋጃል (መዋቅር 8 ይመልከቱ)፡፡

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ በአንድ መ/ቤት ሥር በሚተዳደሩበት ሥርዓት የሥራ ዕቅድ፣ ፖሊሲና ውሳኔ በተጣመረና በተቀናጀ መልክ በአንድ ላይ ይከናወናል፡፡ ቀደም ብሎ በተጠቀሰው የተባበሩት መንግሥታት ጥናት መሠረት ለጥናቱ መልስ ከሰጡት 103 አገሮች መካከል በ16ቱ የምዝገባውና የስታቲስቲክሱ ጽ/ቤቶች በአንድነት በአንድ መሥሪያ ቤት ሥር የሚተዳደሩ መሆኑ ታውቋል፡፡

የወሳኝ ኩነቶች የምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓቶች በአንድ መ/ቤት አስተዳደር ሥር ሲሆኑ የሚከተሉት ጥቅሞች ይኖሩታል፡፡

- ቀልጣፋ አስተዳደር ይኖረዋል፣ ተመሣሣይ ትርጉሞችና ጽንሰ ሃሣቦች ይኖሩታል፣
- በመረጃ አሰባሰብና በመረጃ ማጠናቀር መካከል ያለውን ጊዜ መባከን ይቀንሳል፣
- የሰው ኃይል፣ ጊዜና ገንዘብ ይቆጥባል፣
- በጽህፈት ቤቶች መካከል ከፍተኛ መቀራረብ፣ የሃሣብ መለዋወጥና መተባበር ይኖራል፣
- የበላይ አስተዳደሩም የሁለቱን ጽህፈት ቤቶች የሥራ አፈጻጸምና ቅንጅት በቅርብ እንዲከታተል ያስችለዋል፣

- በተባባሪ መሥሪያ ቤቶችና በጽህፈት ቤቶቹ መካከል ያለው ትብብር ይጠናከራል።
- የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ የቀን ተቀን እንቅስቃሴ በመግባባትና በመረዳዳት ስለሚሆን ወደ ተተለመው ግብ እንዲደርሱ ይረዳል፣
- የፎርሞች፣ የቅጾች፣ የሠንጠረዦች፣ ቅርጽና ይዘት የተጠቃሚዎችን ፍላጎት የሚያሟላ ይሆናል።
- የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሕግና ደንብ በሚገባ ተግባራዊ መሆኑን በመቆጣጠርና አስፈላጊውን እርምጃ በአስቸኳይ ለመውሰድ ይረዳል።
- ትዕዛዞችና መመሪያዎች ከላይ ወደታች አንድ ወጥ በሆነና ጊዜ ሣይባክን እንዲተላለፉ ያደርጋል።

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት በአንድ መ/ቤት ሥር መተዳደራቸው ከላይ የተገለፁት ጥቅሞች ቢኖሩትም የሚከተለው ችግር ሊከሰት ይችላል። ይኸውም ቀልጣፋ የአስተዳደር መዋቅር ከሌለ መመሪያዎችና ትዕዛዞች ከላይ ወደታች በሚተላለፉበት ጊዜ በያንዳንዱ ቅርንጫፍ አስተዳደር ለመድረስ ጊዜ ስለሚወስዱ በምዝገባ ጣቢያዎች አንዳንድ መመሪያና ትዕዛዝ የሚጠይቁ ሥራዎች ከመስተጓጎላቸው ባሻገር የምዝገባውን ሽፋንና ጥራት ዝቅ ያደርጋል።

## 4.3 በኢትዮጵያ የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅር፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀው አንድ አገር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ሲዘረጋ ምን ዓይነት ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅር መዘርጋት እንዳለበት የሚወስነው ባገሩ ተዘርግቶ ያለው ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ መዋቅር ይሆናል:: ከዚህም ባሻገር በአገሩ ያለው ስታቲስቲካዊ ሥርዓት፤ የአገሩ ስፋት፤ የሕዝቡ ብዛትና እንዲሁም የኢኮኖሚው፤ ማህበራዊውና ባህላዊው ሁኔታም ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ::

### 4.3.1 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅር፡

#### ሀ.የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ድርጅታዊ መዋቅር

ኢትዮጵያ የምትተዳደረው በፌደራል ሥርዓት ከመሆኑም ባሻገር ከአገሪቱዋ የቆዳ ስፋትና ከሕዝብዋ ቁጥር ከፍተኛነት አንፃር የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ያልተማከለ መሆን ይኖርበታል(መዋቅር 9 ይመልከቱ):: ይህ ማለት እያንዳንዱ ክልል የራሱን የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በራሱ ኃላፊነት ያካሂድ ማለት ነው::

ያልተማከለ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የተለያዩ ችግሮች ይኖሩታል:: የችግሮቹ ዋናው ምንጭ በተለያዩ ክልሎች በሚካሄዱት የወሳኝ ኩነቶች የምዝገባ እንቅስቃሴ መካከል የቅንጅትና የትብብር ማነስ ነው:: በዚህ ምክንያት በመረጃውና በመረጃ አመዘጋገቡ ላይ የሚከተሉት ድክመቶች ሊከሰቱ ይችላሉ::

- ተመሣሣይነት የሌለውና ማዕከልነት የጎደለው የመረጃ አሰባሰብ፣
- ተመሣሣይነት ሌላቸውና ደረጃቸውን ያልጠበቁ መረጃዎች ከአንዱ ክልል ወደሌላ ክልል መሠራጨት፣
- ጥራትና ተመሣሣይነት የሌላቸው መረጃዎች በአንድነት ለአገር አቀፍ ማጠቃለል፣
- በተለያዩ ሕጎች መሥራት
- የተለያዩ ዕንስ ሃሳቦች መጠቀም

ሆኖም ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች እንዳይከሰቱ አስፈላጊውን ጥንቃቄ አስቀድሞ ማድረግ ይቻላል። ይኸውም በማዕከል ተቋቁሞ በየአስተዳደር ክልሉ የሚካሄደውን የምዝገባ ሂደት የሚከታተል ማዕከላዊ የምዝገባ ጽ/ቤትና አስተባባሪ ኮሚቴ ማቋቋምና ለሁሉም ክልል በተመሣሣይነት የሚያገለግል የምዝገባ ሕግ መቅረጽ ናቸው።

የማዕከላዊ የምዝገባ ጽ/ቤት የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል። በእያንዳንዱ ክልል የሚካሄደውን የምዝገባ ሥራ መከታተል፣ መገምገምና የማሻሻያ ሃሣብ ለየክልሉ የምዝገባ ጽ/ቤቶች ማቅረብ። የጽንሰ ሃሣቦችን፣ የፍችዎችንና የትርጉሞችን ተመሣሣይነት መከታተል። የመዝገቦች፣ የሰርቲፊኬቶችና የስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጾች ይዘት ተመሣሣይ እንዲሆኑ ማድረግ። ለሁሉም ክልል የምዝገባ ጽ/ቤቶች የሚያገለግል መመሪያ ማዘጋጀት። የምዝገባው ሕግና ደንብ ተመሣሣይ እንዲሆኑና በተመሣሣይ ሁኔታ ተግባራዊ መሆናቸውን መመርመር። በእያንዳንዱ ክልል የተቋቋሙትን የምዝገባ ኮሚቴዎችን ከአገር አቀፉ ኮሚቴ (መዋቅር 9 ይመልከቱ) እና ከተለያዩ መ/ቤቶች ጋር ማስተባበር።

## መዋቅር 9

### በኢትዮጵያ የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት



ማዕከላዊ የምዝገባ ጽ/ቤት የሚተዳደረው በፌደራል የፍትህ ሚኒስቴር ሥር ቢሆን ይመረጣል(መዋቅር 9 ይመልከቱ)። የፍትሕ ሚ/ር ኃላፊነትና ተግባር በየአስተዳደር ክልሉ የሚካሄደውን የምዝገባ ሂደት በማዕከላዊው የምዝገባ ጽ/ቤት አማካኝነት መከታተል ይሆናል። የፍትህ ሚኒስትር መ/ቤት በተለይ ለሁሉም ክልል በተመሣሣይ ሁኔታ የሚያገለግል ሕግ መደንገግ፣ ሕጉ በሁሉም ክልል በተመሣሣይ ሁኔታ ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፣ በአንድ ክልል የተሰጡ የምስክር ወረቀቶች በሌሎች ክልሎች ተቀባይነት እንዲኖራቸው ማድረግና ይዘታቸው ተመሣሣይ መሆኑን መከታተል ይሆናል።

## ለ. የወሳኝ ኩነቶች የምዝገባ ሥርዓት አስተዳደራዊ መዋቅር

የምዝገባው ሥርዓት ያልተማከለ እንደመሆኑ መጠን መተዳደር ያለበት በየክልሉ በሚገኝ የመንግሥት መ/ቤት ይሆናል። ይህ መ/ቤት ከክልል እስከ ቀበሌ ማዘዝ የሚችል መሆን አለበት። ለዚህ ተግባር የክልሉ አስተዳደር መ/ቤት ትክክለኛ ምርጫ ይሆናል። ምክንያቱም ከክልል እስከ ከተማና ገጠር ቀበሌ ድረስ ያለውን የምዝገባ ሂደት ለመቆጣጠር፣ ለመከታተልና ለማስተባበር የሚችለው ይኸው መ/ቤት ስለሚሆን ነው።

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ መካሄድ ያለበት በገጠርና በከተማ ቀበሌዎች መሆኑ ቀደም ብሎ ተጠቁሟል። ሆኖም እያንዳንዱ የቀበሌው ጽ/ቤት ምዝገባውን ራሱ ያካሂድ ወይስ በቀበሌው ጽ/ቤት ሥር የሚተዳደር ነገር ግን ራሱን የቻለ የሰው ኃይልና ሌሎች የጽህፈት መሣሪያዎች ሁሉ የተሟሉለት ንዑስ ክፍል ተመሥርቶ ምዝገባውን ያካሂድ የሚለው ሃሳብ በጥንቃቄ ታስቦ መወሰን ይኖርበታል።

## 4.3.2 የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅር፣

### ሀ. የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት ድርጅታዊ መዋቅር

እንደ ተባበሩት መንግሥታት አመለካከት የሚመረጠውና መሆን ያለበት የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት ድርጅታዊ መዋቅር የተማከለው ነው:: ለዚህ ምክንያቱ በአንድ አገር የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት የተማከለ ወይም በአንድ ማዕከል ቁጥጥር ሥር ሲሆን ጽንሰ ሃሣቦች፣ ትርጓሜዎችና፣ የሚዘጋጀው ስታቲስቲክስ በተመሣሣይ ሁኔታ ሊከናወን ይችላል:: በማዕከል የተቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ጽ/ቤት በተለያዩ አካባቢዎች የሚካሄደውን የመረጃ አሰባሰብን በማስተባበር፣ በአንድ መመሪያና በተመሣሣይ ሁኔታ እንዲሰበሰብ ያደርጋል:: የተማከለ ሥርዓት ስህተቶችንና ድግግሞሽን ለመከላከል፣ የሰው ኃይል፣ ገንዘብንና ጊዜን ለመቆጠብ ይረዳል::

ከሌሎች ልምድ እንደምንግረው በአብዛኛው አገሮች የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ አደረጃጀት የተማከለ ነው:: ለምሳሌ ቀደም ብሎ ለተጠቀሰው የተባበሩት መንግሥታት ጥናት መልስ ከሰጡት 103 አገሮች መካከል በ85 አገሮች የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት የተማከለ ነው:: በመሆኑም የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት የተማከለ ቢሆን ይመረጣል:: ይኸውም ሥርዓቱ በማዕከል የተቋቋመ የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ጽ/ቤት ኖሮት በየክልሉ የተመዘገቡትን የወሳኝ ኩነቶች መረጃ ተቀብሎ የእያንዳንዱን ክልልና አገር አቀፉን የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ የሚያዘጋጅ ይሆናል::

የተማከለ የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት የሚከተሉት ጥቅሞች ይኖሩታል።

- ብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሕግ ያዘጋጃል
- ተመሣሣይ የጽንስ ሃሣብና ትርጉም እንዲኖር ያደርጋል።
- የመረጃዎች የጥራት ደረጃ ተመሣሣይና ከፍተኛ እንዲሆን ያደርጋል።
- መረጃዎች በተመሣሣይና ጥራት ባለው መንገድ እንዲተነተኑና እንዲጠናቀሩ ያደርጋል
- የስታቲስቲክስ ሪፖርት ፎርሞች ይዘትና ቅርጽ ተመሣሣይና ጥራት ያላቸው እንዲሆኑ ያደርጋል።
- በየጊዜው ከመረጃው ፍላጎት ዕድገት ጋር የሚሄዱ መረጃዎች እንዲሰበሰቡና እንዲሻሻሉ ያደርጋል።
- የተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑትን ድርጅቶችንና የየአስተዳደር ክልሎችን ያስተባብራል።
- የየክልሉና ማዕከላዊው ኮሚቴዎች በየጊዜው እየተገናኙ ስለምዝገባው ሂደት እንዲወያዩ ያስተባብራል።

## ለ. የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት አስተዳደራዊ መዋቅር

በኢትዮጵያ ማዕከላዊነትን በጠበቀ መልኩ የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት መተዳደር ያለበት በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ሥር መሆን ይኖርበታል። በአሁኑ ወቅት በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ሥር በመምሪያ ደረጃ የተዋቀረ የቫይታል (የወሳኝ ኩነቶች) ስታቲስቲክስ ምዝገባ፣ ጥናትና ምርምር

መምሪያ ይገኛል። ይህ መምሪያ አሁን በማካሄድ ላይ ካለው ጥናትና ምርምር ሥራ ባሻገር ወደፊት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በአገሪቱ ሲቋቋም ከምዝገባው የሚገኘውን የወሳኝ ኩነቶች መረጃ ከየክልል ተቀብሎ በመተንተን፣ በማቀናበርና የእያንዳንዱን ክልልና አገር አቀፉን የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ በማዘጋጀት ለተጠቃሚዎች የማሠራጨት ተግባር ማካሄድ ይኖርበታል። ይህ እንዲሆን የሚፈለግበት ዋናው ምክንያትም አንደኛ በአገሪቱ አሁን ተቋቁሞ ያለውን ተቋም በተቻለ መጠን መጠቀም ከከፍተኛ ወጪ ስለሚያድን ነው። በተጨማሪም ያለውን የሰለጠነ የሰው ኃይልና ማቴሪያል በሚገባ ለመጠቀም ይረዳል። ይህ መምሪያ በስታቲስቲክስ መረጃ አሰባሰብ፣ አጠናቃቀርና አሰረጫጨት ከፍተኛ ልምድ ያካበተ ከመሆኑም በላይ የሚቋቋመውን የምዝገባውን ሥርዓት በጽንሰ ሃሣብ፣ በትርጉም፣ በማስተባበርና መመሪያዎችን በማዘጋጀት ግንባር ቀደሙን ሚና ሊጫወት ይችላል።

መዋቅር 9 በኢትዮጵያ የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች የምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ሊኖረው የሚገባውን ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅር ያመለክታል። ይህ ድርጅታዊ መዋቅር የሚያመለክተው ያልተማከለ የምዝገባ ሥርዓትና የተማከለ የስታቲስቲክስ ሥርዓትን ነው። አስተዳደራዊ መዋቅሩ የሚያመለክተው ምዝገባውም ሆነ ስታቲስቲክሱ በሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሥር የሚተዳደሩ መሆናቸውን ነው። የአገር አቀፉ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባር ሁለቱን ማለትም የምዝገባውንና የስታቲስቲክሱን ጽ/ቤቶች በማስተባበር በየክልሉ የሚካሄደው ምዝገባ እንዲሣካ ጥረት ማድረግ ይሆናል።

### 4.3.3 የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

ከወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ጽ/ቤት ተግባሮች መሃከል ዋንኞቹ፡ ለስታቲስቲክሱ ሥራ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ዓይነት መወሰን፡ ወሳኝ ኩነቶችንና ከወሳኝ ኩነቶች ጋር ግኑኝነት ያላቸውን ጽንሰ ሃሣቦች ፍች ማዘጋጀት እንዲሁም የምዝገባውና የስታቲስቲክሱ ጽ/ቤቶች የሚጠቀሙባቸውን ዶክሜንቶች ማለት መዝገቦች፡ ሰርተፊኬቶች፡ ሪፓርት ቅጾች፡ መመሪያዎች... ወዘተ ከምዝገባው ጽ/ቤት ጋር ተባብሮ ማዘጋጀት ይገኙበታል። በተጨማሪም ጽ/ቤቱ ከምዝገባው የተገኙትን መረጃዎች በኮምፒዩተር በማጠናቀርና በየጊዜው ለማደስ የሚያስችሉ ቴክኒካዊ አሠራር መመሪያዎች ማዘጋጀት ይጠበቅበታል።

የመዝገቦችና የሪፓርት ቅጾች ቅርጽም እንደ ይዘታቸው በሚመለከታቸው ተጠቃሚዎች ታይቶና ተመርምሮ መወሰን ይኖርበታል። ቅጾቹ ለአያያዝና ለሥራ ቅልጥፍና አመቺና ተጨማሪ ወጭ የማያስከትሉ መሆን ይኖርባቸዋል። መዝገቦች በብትን ወረቀቶች ወይም በካርዶች ወይም በጥራዞች መሆን እንዳለባቸው መወሰን ይኖርበታል። በተመሣሣይም የስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጾች ከሦስቱ አማራጮች ማለትም «የተናጠል»፡ «የጋራ» ወይም ከመዝገብ ጋር በአንድነት የሚሆነው ከወጭና ከአያያዝ አመቺነታቸው አንፃር ተጠንቶና ተመርምሮ መወሰን ይኖርበታል።

በመዝገቦች፡ በሰርቲፊኬቶችና በሪፓርት ቅጾች የመረጃ አሞላልና እንዲሁም የካርታ አነባበብ፡ የመረጃ ማረምና የኮድ ማድረግ መመሪያዎች መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ስለዚህ የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ጽ/ቤት ከላይ የተጠቀሱት ዶክሜንቶች በሚዘጋጁበት ጊዜ ከሙያውና ከሥራው ጋር

ባለው ቀጥታ ግኑኝነት የተነሣ ከፍተኛ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅበታል።

ለወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ለወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት መሣካት ዋናው መሣሪያ የሰለጠነ የሰው ኃይል መኖር ነው። የሰው ኃይል ሲባል የምዝገባው፣ የስታቲስቲክስ ጽ/ቤቶችና የተባባሪ ድርጅቶች ሠራተኞችና ሕብረተሰቡን ጭምር ያጠቃልላል። በመሆኑም የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ጽሕፈት ቤት የሰው ኃይል ማሰልጠን ከተግባሮቹ አንዱ ይሆናል።

አስተማማኝ የወሳኝ ኩነቶች መረጃ ማግኛ ዘዴ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ መሆኑ በተደጋጋሚ ተገልጿል። ሆኖም ሥርዓቱ አዲስ በመሆኑ፣ ከሕብረተሰቡ ዝቅተኛ ግንዛቤና ትብብር ማነስ ምክንያት ለተወሰኑ ዓመታት ሽፋኑ ዝቅተኛ እንደሚሆን ይገመታል። በመሆኑም ሌሎች የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችን በመጠቀም ተጨማሪ የወሳኝ ኩነቶች መረጃ መገኘት ይኖርበታል።

ሌላው የወሳኝ ኩነቶች ጽህፈት ቤት ተግባር የሥርዓቱን ደካማና ጠንካራ ጎኖችን የሚያመለክቱ ቁጥጥሮች፣ ጥናቶችና ግምገማዎች ማካሄድና በተገኘው ውጤት መሠረት አስፈላጊው የማሻሻል እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ነው።

የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ጽ/ቤት ሌላው ተግባር የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሪፓርት የሚደረግበትን ፕሮግራም ማዘጋጀትና የሪፓርቶችን በጊዜ መድረስ ቁጥጥር ማካሄድ ይሆናል። ቁጥጥሩ በሪፓርቶች በጊዜ መድረስ ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን በመጠንና በዓይነት የተሟሉ መሆናቸውን ጭምር መከታተል ይኖርበታል።

የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ጽ/ቤት ከምዝገባ ጽ/ቤት በተላለፈለት የስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጽ ውስጥ የሥፈሩትን መረጃዎች ማረምና ኮድ ማድረግ፣ በኮምፒውተር ውስጥ ማስገባት፣ መረጃ ማጽዳት፣ ሠንጠረዥ ማዘጋጀት፣ ሪፖርት ማዘጋጀትና ማሰራጨት አለበት። ሪፖርቶች ወርሃዊ፣ የሦስት ወር፣ የስድስት ወር፣ የአመትና ልዩ ልዩ ሊሆኑ ይችላሉ።

የወሳኝ ኩነቶች ሪፖርት በወቅትና በተከታታይ መዘጋጀትና ለተጠቃሚዎች መሠራጨት አለበት። የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ጽ/ቤት የመረጃው ተጠቃሚዎችንና የሚፈልጉትን የመረጃ ዓይነት በቅድሚያ ማወቅ ይኖርበታል። ሪፖርቱን ለተጠቃሚዎቹ በአድራሻቸው መላክ ይኖርበታል። የታተሙ ሪፖርቶች ለሕብረተሰቡና ለተባባሪ ድርጅቶች በወቅቱ ካልደረሱ ተባባሪ ድርጅቶችም ሆኑ ሕበረተሰቡ የሚፈለግባቸውን ትብብር ላይሰጡ ይችላሉ። የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ጽ/ቤት ሪፖርቶችን ማዘጋጀት ዋንኛው ተግባሩ እንደመሆኑ መጠን እነዚህን መረጃዎች ከላይ ለተጠቀሱት ተጠቃሚዎች በጊዜ መድረሳቸውንም በጥንቃቄ ማከናወንና መከታተል ይኖርበታል።

ቀጥሎ የተመለከተው ቻርት በማዕከላዊ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤት፣ አስተባባሪ ኮሚቴና የስታቲስቲክስ ጽ/ቤት የስራ ኃላፊነትና በመካከላቸው ሊኖር የሚገባውን የስራ ግኙኝነት ያመለክታል።

ማዕከላዊ የምዝገባ ጽሕፈት ቤት፣ የስታቲስቲክስ ጽሕፈት ቤትና አገር አቀፍ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት



## ምዕራፍ 5

# የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ተባባሪ ድርጅቶችና አስተባባሪ ኮሚቴዎች

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ሊሳካ የሚችለው በአንድ ድርጅት ጥረት ብቻ ሳይሆን የብዙዎቹ ከስርዓቱ ጋር ግንኙነት ሊኖራቸው ከሚችል መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑና አገር አቀፍና የውጪ ድርጅቶች ትብብር ሲገኝ ነው:: ስለሆነም የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ሲቋቋም ስርዓቱን በማደራጀት መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መተባበር ይኖርባቸዋል:: በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ከብዙ ዓመታት በፊት የተቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ስርዓት የሸፋኑ ምጣኔ ደካማ ከሆነባቸው ምክንያቶች አንዱ ስርዓቱ በአንድ ድርጅት ትከሻ ላይ በመውደቁ ነው::

## 5.1 የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት ተባባሪ ድርጅቶች

በኢትዮጵያ ከሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ስርዓት ጋር ቀጥታና ተዘዋዋሪ ግኑኝነት የሚኖራቸው ድርጅቶች ቀጥለው የተዘረዘሩት ይሆናሉ::

ሀ. ፍትህ ሚ/ር
ለ. ጤና ጥበቃ ሚ/ር
ሐ. ማስታወቂያ ሚ/ር
መ. ትምህርት ሚ/ር
ሠ. የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚ/ር
ረ. የከተማ ልማትና ቤት ሚ/ር
ሰ. ማዕከላዊ ስታቲስቲክስለ ሥልጣን

ሸ. የሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት
ቀ. የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት
በ. የክልል ጉዳይ ንዑስ ዘርፍ
ተ. የክልል መስተዳድሮች
ቸ. የኢትዮጵያ የቤተሰብ መምሪያ
ኀ. የሃይማኖት ድርጅቶች
ነ. የመረዳጃ ማህበራት (ዕድሮች)
ኘ. የተባበሩት መንግስታት የሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት (UNFPA)
አ. አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሥነ ሕዝብ ጥናት ማዕከል
ከ. አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የሕግ ፋክልቲ

## 5.2 የተባባሪ ድርጅቶች ዋና ዋና ተግባርና ኃላፊነት

የፍትህ ሚኒስቲር የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ሕግን የመደንገግና የማስፈፀም ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡ የሕጉን ይዘት በምዕራፍ 6 ይመልከቱ፡፡ የፍትህ ሚኒስቴር ሌላው ተግባር በየፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረት የሚፈፀሙ ፍቺዎችን መረጃ ወደ ምዝገባ ጽ/ቤት በተከታታይ የሚተላለፍበትን ሥርዓት መቀየሥና ተግባራዊ ማድረግ ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ የምዝገባውን ሽፋን ከፍ እንዲል ይረዳል፡፡

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከምዝገባ የሚገኘውን መረጃ ከተጠቃሚዎች አንዱ እንደመሆኑ መጠን በየሆስፒታሉና በየክሊኒኩ በየቀኑ የሚፈፀሙት ልደቶችና ሞቶችን በአንዳንድ ኮፒ ለምዝገባ ጽህፈት ቤት እንዲደርሱ በማድረግ የምዝገባውን ሽፋን ማጠናከር ይኖርበታል፡፡ እያንዳንዱ የጤና ድርጅት ቢያለበት ይህንን ተግባር እንዲፈጽም በሕጉም የሚደነገግ ሲሆን ጤና ጥበቃ ሚኒስቴርም በመመሪያ መልክ በማስተላለፍ ግፊት ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በየሆስፒታሉና የጤና ድርጅቶች ወሳኝ

ኩነቶቹ፣ የተፈፀሙላቸው ግለሰቦችና ቤተሰቦች በየምዝገባው ጽህፈት ቤት በመገኘት እንዲያስመዘግቡ በማስተማርና በመቀስቀስ የሕብረተሰቡ ተሣትፎ እንዲጐለብት ማድረግ አለበት::

ማስታወቂያ ሚኒስቴር ባህላዊ እምነቶች በምዝገባው ላይ የሚያደርሱትን ተጽንአ ለማስወገድ ሕብረተሰቡን በማስተማር ተሣትፎ ማድረግ ይኖርበታል:: የሬዲዮ፣ የቴሌቪዥንና የፕሬስ ድርጅቶችም ስለምዝገባው ጥቅም የሚያስተዋውቁ፣ የሚያስተምሩና የሚቀሰቅሱ መድረኮችን በመክፈት ሕብረተሰቡን ሊያስተምሩ የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል::

ትምህርት ሚኒስትር በየትምህርት ቤቱ ስለምዝገባው የሚያስተምሩ ፕሮግራሞችን በመክፈትና በማስተማር የህብረተሰቡን ተሣትፎና ትብብር ከፍ ማድረግ ይችላል:: በተጨማሪም ማንኛውም ትምህርት ቤት የሚገባ ልጅ የዕድሜውን ልክ የሚያመለክት የልደት ሰርተፊኬት ማቅረብ እንዳለበት በመጠየቅ የልደት ሴርቲፊኬቶች ተፈላጊነት ከፍ እንዲል ማበረታታት ይኖርበታል::

የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር ሌላው የወሳኝ ኩነቶች መረጃ ተጠቃሚ መ/ቤት ነው:: በመሆኑም ምዝገባው የሚደራጅበትን ዕቅድ ማውጣት፣ ማስተባበር፣ መከታተልና መቆጣጠር ይጠበቅበታል:: እንዲሁም የሰው ኃይል በማሰልጠንና የምዝገባውን ሂደት በየጊዜው በመገምገምና ጉድለቶችን በመጠቆም እየተሻሻለ እንዲሄድ ማድረግ ይጠበቅበታል:: በተጨማሪም የተለያዩ መ/ቤቶችን፣ ድርጅቶችንና ኮሚቴዎችን በማስተባበር፣ ሰሚናርና ዐውደ ጥናቶች በማካሄድ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ከፍ ማድረግ ይሆናል::

የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ከምዝገባው በሚያገናኛቸው መረጃዎች በከተሞች የጤና፣ የትምህርት፣ የመንገዶች፣ የትራንስፖርት... ወዘተ ዕቅድ ለማዘጋጀት ይችላል። በመሆኑም በከተሞች የሚቋቋመውን የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባን በመከታተል፣ በመቆጣጠር፣ በሃሣብና በማቴሪያል አስፈላጊውን እርዳታ በመስጠት ምዝገባው በከተሞች እንዲሣካ የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር የበኩልን አስተዋፅኦ ማድረግ ይኖርበታል።

ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የወሳኝ ኩነቶችን ስታቲስቲክስ በማዕከል ደረጃ የሚያዘጋጅ ከመሆኑም ባሻገር በሙያው የሠለጠኑና ልምድም ያላቸው ሠራተኞች ያሉት በመሆኑ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ እንዲሣካ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል። ባለሥልጣኑ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማስተባበር፣ የመዝገቦችን ቅርጽና ይዘት ፣ የጽንሰ ሃሣቦች ትርጉምና የመዝገቦች አሞላል መመሪያ በማዘጋጀት ተሣትፎ ማድረግ ይኖርበታል። እንዲሁም የሰው ኃይል ማሠልጠንና ቴክኒካዊ ድጋፍ መስጠትም ከኃላፊነቱና ተግባሮቹ አንዱ ይሆናሉ። በተጨማሪም ከምዝገባው የሚገኙትን መረጃዎች መተንተን፣ ማጠናቀርና፣ ለተጠቃሚዎች ማሠራጨት ሌሎች ተግባሮቹ ይሆናሉ። የምዝገባውን ጥራት፣ ሽፋንና ትክክለኛነት በተመለከተ የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም መገምገምና በውጤቱም መሠረት የምዝገባውን ድክመትና ጥንካሬ በመጠቆም የማሻሻያ ሃሣቦችንም በማቅረብ ምዝገባው እንዲጠናከር ማድረግ ይጠበቅበታል።

የሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽህፈት ቤት ከሌሎች ድርጅቶች የበለጠ ኃላፊነት አለበት። ይኸውም የሥነ የሕዝብ ፖሊሲን ተግባራዊ ለማድረግ ውጤቱንም ለመገምገም ለመከታተልና ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የሚገኘው መረጃ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይሰጣል። በሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽህፈት ቤት ፖሊሲ

ዶክሜንት ከሠፈሩት ተግባሮች አንዱ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓትን ማቋቋምና መከታተል ነው:: በመሆኑም የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በሰው ኃይል፣ በገንዘብና በማቴሪያል የሚጠናከርበትን ሁኔታ የመፍጠር ተግባር የበለጠ የጽህፈት ቤቱ ኃላፊነት ይሆናል::

<u>የሴቶች ጉዳይ ጽህፈት ቤት</u> በባህልና በሌሎች በተለያዩ ምክንያቶች በሴቶች ላይ የሚደርሱትን ተፅዕኖዎች ለማስወገድ በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ መሆኑ ይታወቃል:: ከእንቅስቃሴዎቹ አንዱ የቤተሰብ ሕግን አሻሽሎ መደንገግ ነው:: የቤተሰብ ሕግን ተግባራዊ ለማድረግ የወሳኝ ኩነቶች ሥርዓትን ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑ በተደጋጋሚ ተገልጿል:: የምዝገባው ሥርዓት መቋቋምና ከምዝገባው የሚገኘው መረጃ ለቤተሰብ ሕግ ተፈጻሚነት ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግ ስለሚታወቅ የሴቶች ጉዳይ ጽህፈት ቤት ለምዝገባው መጠናከርና ግብ መምታት ከፍተኛ ሚና መጫወት እንዳለበት ይጠበቃል:: ይኸውም የወሳኝ ኩነቶች እንዲመዘገቡ በማድረግ፣ የምዝገባው ሕግና ደንብ ከቤተሰብ ሕግና ደንብ ጋር እንዲጣጣም በማድረግ፣ የምዝገባው ሥርዓት ከተቋቋመ በኋላ የሕብረተሰቡ በተለይ የሴቶች ትብብር እንዲገኝ በማስተማር፣ በመቀስቀስና፣ በመከታተል አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይኖርበታል::

<u>የክልል ጉዳይ ንዑስ ዘርፍ</u> በየክልሉ የሚቋቋሙትን የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ለማጠናከር በማዕከላዊው መንግሥትና በክልል አስተዳደሮች መካከል እንደ ድልድይ በመሆን አስፈላጊው ድጋፍ የሚገኝበትን ሁኔታ መፍጠር ይጠበቅበታል::

<u>የክልል መስተዳድር ጽ/ቤቶች</u> በየክልላቸው የሚቋቋሙትን የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት መምራት ኃላፊነት አለባቸው:: የምዝገባው ሥርዓት በመመሪያውና በሕጉ

መሠረት መካሄዱን መከታተልና መቆጣጠር ይኖርባቸዋል። በተለይ ምዝገባው አዲስና ያልተለመደ ተግባር ከመሆኑም ባሻገር በየአካባቢው የተለመዱና የተለያዩ ባህሎች ከፍተኛ ተፅዕንኖ የሚያሣድርበት ስለሆነ የክልል አስተዳደሩ በየቀኑ ተከታትሎ የሚከሰቱትን ችግሮች በመፍታት ምዝገባው የተሣካ እንዲሆን ማድረግ አለበት።

የክልል መስተዳድርዎች የሚከተሉትን ተግባራት መፈጸም ይጠበቅባቸዋል።

- ዶክመንቶች ወደ የቀበሌዎቹ የምዝገባ ጽህፈት ቤቶች መላካቸውን መቆጣጠር።
- የተሞሉት መዝገቦች ወደ ክልሉ የምዝገባ ጽ/ቤት መላካቸውን መከታተል።
- አዳዲስ የምዝገባ ጽህፈት ቤቶች ማቋቋም።
- ምዝገባ በተቋቋመባቸው ቀበሌዎች የምዝገባ ሂደቱን መገምገምና ማሻሻል።
- በክልል በዞን፣ በወረዳና በየቀበሌው አስተባባሪ ኮሚቴዎች ማቋቋም።
- ሕብረተሰቡን ስለምዝገባው ጥቅም ያለማቋረጥ ማስተማር፣ መቀስቀስ።
- የሎጂስቲክ ክፍል ማቋቋም።
- የምዝገባ ሥርዓት ሕግና ደንብ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ።
- ለምዝገባው በጀት መመደብ።
- ሌሎችን መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ማስተባበር

<u>የኢትዮጵያ የቤተሰብ መምሪያ</u> ከምዝገባው በሚያገኘው መረጃ መሠረት ለዓላማው መሣካት የሚያከናውናቸውን ተግባራት ውጤት ለመገምገምና የተሻለ ሥራ ለመሥራት ያስችለዋል። በመሆኑም በየገጠሩና በየከተሞች በተሰማሩት

የቤተሰብ መምሪያ አባሎች አማካይነት ስለምዝገባው ህብረተሰቡን በማስተማርና በመቀስቀስ ምዝገባው የተሣካ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅበታል።

<u>የሃይማኖት ድርጅቶች</u> ምዕመናንን በማስተማርና በመቀስቀስ አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በተለይ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የልደት፣ የሞትና የጋብቻ፣ ምዝገባ እንደምታደርግ ይታወቃል። እነዚህን ወሳኝ ኩነቶች በተመለከተ ለሕጋዊ ምዝገባ ሥርዓት ጽህፈት ቤት በየጊዜው ሪፖርት በመላክ የምዝገባው ሽፋን አስተማማኝ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል። በተለይም የመቃብር ስፍራዎችን አጠቃቀም በተመለከተ ከምዝገባ ጽህፈት ቤት የምዝገባ ሰርቲፊኬት ላመጡ ምዕመናን ብቻ ክፍት እንደሚሆን በማስታወቅ ሞት እንዲመዘገብ በተዘዋዋሪ መንገድ ግፊት ልታደርግ ትችላለች። ሌሎች የሃይማኖት ተቋማትም ተመሣሣይ እርምጃ በመውሰድ የምዝገባውን ሥርዓት ማጠናከር እንደሚችሉ ይገመታል።

<u>ዕድሮች</u> በየከተማውና በየገጠሩ ተስፋፍተው ከሚገኙት ሕዝባዊ ማህበራት ዋናውና ከእያንዳንዱ የሕብረተሰብ አባልና ቤተሰብ ጋር ቀጥተኛና የማያቋርጥ ግንኙነት ያለው መረዳጃ ማህበር ነው። ዕድሮች የተለያየ ይዘትና መልክ አላቸው። ዕድሮች ለሀዘንም ሆነ ለደስታ ከእያንዳንዱ ቤተሰብና ግለሰብ ጋር ግንኙነት ስለሚኖራቸው ልደት፣ ሞት፣ ጋብቻና ፍቺ በአካባቢውና በእያንዳንዱ ቤተሰብ ሲፈፀም ወዲያውኑ ያውቁታል። የቤተሰብ አባል በሞት፣ በልደት፣ በጋብቻና በፍቺ ሲጨምርና ሲቀንስ ይመዘግባሉ። በመሆኑም በየቀበሌው ለተቋቋመ የምዝገባ ጽሕፈት ቤት ይህንን የመዘገቡትን መረጃ በሌላ ቅጽ ሞልቶ በመላክ የምዝገባውን ሽፋን ከፍ ከማድረጋቸው ባሻገር ዓላማውም እንዲሣካ ሊያደርጉ ይችላሉ። ከዚህም ባሻገር እያንዳንዱን የዕድር አባልና ቤተሰብ በየቤታቸው የሚከሰተውን ልደት፣ ሞት፣ ፍችና

ጋብቻ ሪፓርት እንዲያደርጉ መቀስቀስ ይኖርባቸዋል:: በተጨማሪም ዕድሮች በየጊዜው በሚያደርጉአቸው ስብሰባዎች የምዝገባው ጽ/ቤት አባላት እየተገኙ ትምህርታዊ ቅስቀሳ እንዲያደርጉ መድረክ ሊዘጋጁላቸው ይችላሉ::

የተባበሩት መንግሥታት የሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በትክክል ከተካሄደ በየዓመቱ የሚከሰቱትን የወሳኝ ኩነቶችን ብዛት ሙሉ በሙሉ ሊያስገኝ የሚችልና አማራጭ የሌለው የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ መሆኑን ያምናል:: በመሆኑም የምዝገባ ሥርዓቱ በተለይ በማደግ ላይ ባሉ አገሮች እንዲቋቋምና እንዲጠነክር ከፍተኛ እርዳታ በገንዘብ፣ በማቴሪያልና በሰው ኃይል ሲያደርግና በማድረግ ላይ ያለ ድርጅት መሆኑን በሚያሣትማቸው መጽሔቶችና በሚያካሂዳቸው ስብሰባዎች በየጊዜው እየተገለጸ ነው:: በመሆኑም በኢትዮጵያ ለሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት የተባበሩት መንግሥታት ትብብር ከተጠየቀ በገንዘብ፣ በባለሙያና በሌሎች ማቴሪያሎች እርዳታ እንደሚያደርግ ታውቆ አስፈላጊውን ትብብር መጠየቅ ያስፈልጋል::

የአዲስ አበባ የኒቨርስቲ የሥነ ሕዝብ ሥልጠናና ምርምር ማዕከልና የሕግ ፋክልቲ የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት እንዲያድግና እንዲደራጅ ከፍተኛ ሚና መጫወት ይጠበቅበታል:: ተቋማቱ የሰው ኃይል በማሠልጠን፣ ምርምሮች በማካሄድ፣ የጽንስ ሃሣቦች ትርጉሞችና መመሪያዎችን በማዘጋጀት፣ ስብሰባዎችና ወርክሾፖች በማካሄድ፣ ከአገሪቱ ባህልና ልማድ ጋር የሚሄድ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት የሚደራጅበትን ሁኔታ ለመፍጠር መጣር ይኖርባቸዋል::

## 5.3 አስተባባሪ ኮሚቴዎችና ተግባራቸው

ለወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ መሳካት የተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ትብብር ማስፈለጉ ተጠቅሷል:: እነዚህን ድርጅቶች የሚያስተባብር አገር አቀፍ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ አስተባባሪ ኮሚቴ(መዋቅር 9 ይመልከቱ) መቋቋም አስፈላጊ ይሆናል:: የኮሚቴው አባላት ከላይ የተዘረዘሩት መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ መ/ቤቶችና ድርጅቶች ይሆናሉ:: ኮሚቴው ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ተግባራት ያከናውናል::

- የእያንዳንዱን ድርጅት ተሳትፎ ማረጋገጥና ችግሮችም ሲኖሩ ማስተካከልና መፍትሔ መስጠት፣
- የምዝገባው አፈጻጸም በትክክልና በጥራት መከሄዱን ማረጋገጥና ችግሮችም ካሉ መፍታት፣
- የምዝገባውን ድርጅታዊና አስተዳደራዊ አወቃቀር መከታተል::
- የመረጃ ማጠናቀር፣ ህትመትና ስርጭት ተግባር መከታተል::
- ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚከናወነውን የምዝገባ ሂደት መገምገም፣
- ምዝገባው በተለያዩ ክልሎች በተመሳሳይ ሁኔታ መከናወኑን መከታተል
- የምዝገባው የሥራ ሂደት የሚገመገምበትን አሠራር መቀየስ

አገር አቀፉ ኮሚቴ በንዑሳን ኮሚቴዎች ተከፋፍሎ መንቀሳቀስ ይችላል:: የንዑሳን ኮሚቴዎች ኃላፊነትና ተግባር በተለያዩ አርእስቶች ላይ ትኩረት በማድረግ መሥራት ይሆናል:: ይኸውም ለምሳሌ የቴክኒካል ኮሚቴ፣ የሕብረተሰብ

የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ፡ የሰው ኃይል ሥልጠናና ማሻሻያ ኮሚቴ...ወዘተ ናቸው። በአጠቃላይ የኮሚቴዎች አባላት ጥንቅርና የንዑሳን ኮሚቴዎች ይዘት እንደየአካባቢውና በየጊዜው በሚገኘው የምዝገባ ሂደት ልምድ መሠረት ይሆናል።

ኮሜቴዎች ከማዕከል እስከ ክልል፡ ዞን፡ ወረዳ፡ ገጠርና ከተማ ቀበሌዎች ሁሉ መቋቋም ይኖርባቸዋል። በተለይም በወረዳ በገጠርና በከተማ ቀበሌዎች የሚቋቋሙት ኮሚቴዎች ያገር ሽማግሌዎችን፡ ታዋቂ ሰዎችንና ለምዝገባው መሳካት አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ግለሰቦችንና ድርጅቶን ሁሉ ማጠቃለል ይኖርባቸዋል። በገጠርና በከተማ ቀበሌዎች የሚቋቋሙት ኮሚቴዎች ሕብረተሰቡን በማስተማር ከፍተኛ ሚና መጫወት ይችላሉ።

## ምዕራፍ 6

# የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሕግ አስፈላጊነት

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሲቋቋም በቅድሚያ መዘጋጀት ያለበት የምዝገባው ሕግ ነው፡፡ ለምዝገባው አፈጻጸም፣ አስገዳጅነት፣ ቋሚነትና ተከታታይነት ሕግ ዋናው መሠረት ነው፡፡

የሕጉ መኖር ግለሰቡ፣ ሕብረተሰቡ፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ኃላፊነታቸውንና ግዴታቸውን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ያደርጋል፡፡ ሕጉ የምዝገባ አሰራር መመሪያና ማስፈፀሚያ ደንብ በመሆን የምዝገባው ስርዓት እያደገ፣ እየተሻሻለና እየጠነከረ እንዲሄድ ያደርጋል፡፡ ሕጉም ራሱ ቢሆን ከሕብረተሰቡ ማህበራዊና ባህላዊ ዕድገት ጋር አብሮ የሚያድግ ይሆናል፡፡

የምዝገባውን ሥርዓት ለማቋቋም የሚቀረፀው ሕግ የምዝገባውን የተለያዩ ይዘቶችን፣ ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅሩን፣ የምዝገባውን አፈጻጸም... ወዘተ ግልጽ በሆነ መንገድ ማብራራትና መተርጎም ይኖርበታል፡፡

ሕጉ ሲቀረጽ ከአገሩ ሕገ መንግሥትና ከተለያዩ አለም አቀፍ ሕጎች ጋር በማይጋጭና በማይቃረን መንገድ መቀረጽ አለበት፡፡ ሕጉ በአገሪቱ ያለውን የስታቲስቲክስ ሕግ፣ ደንብ፣ አወቃቀርና አስተዳደር ከምዝገባው ጋር የሚኖረውን ግኑኙነት በሚያጠናክር መንገድ መደንገግ ይኖርበታል፡፡

ሕጉ አጠቃላይ የሆነና ከሚገባው በላይ ያልጠበቀ መሆን ይኖርበታል፡፡ የሕጉ አጠቃላይ ይዘት የምዝገባውን

ድርጅታዊና አስተዳደራዊ መዋቅር፣ የጽንስ ሃሣቦችን ትርጉም፣ የምዝገባ አፈጻጸምን፣ የምዝገባ ዓላማን፣ የተለያዩ ድርጅቶችና ግለሰቦች ኃላፊነትና ተግባር፣ በጀት... ወዘተ በግልጽ ይዘረዝራል።

ሕጉ የሚመዘገቡት ወሳኝ ኩነቶችን ዓይነት፣ ኩነቶችንና ከኩነቶች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ግለሰቦች የሚመለከቱ መሠረታዊ መረጃዎችን ዓይነት፣ ማን መዝጋቢና ማን አስመዝጋቢ እንደሚሆን፣ የምዝገባውንና የስታቲስቲክስ ዶክሜንቶች ይዘት፣ የሽፋንና የጥራት (የዓይነትና የመጠን) ቁጥጥር እንዴት መከናወን እንዳለበት፣ የሚመዘገበው ኩነት በርግጥ መከሰቱን እንዴት ማረጋገጥ እንደሚቻል የሚመራ ይሆናል።
ከሚገባው በላይ ያልጠበቀ ሕግ የምዝገባውን ሥርዓት የሚያንቀሳቅሱት ግለሰቦችና ድርጅቶች ጥንቃቄ የተሞላበትን አስተዳደራዊ ውሣኔ ለመስጠት የሚኖራቸውን ነፃነት ይመለከታል። ይኸውም ከሕጉና ከደንቡ ባላፈነገጠ መንገድ የራሣቸውን ውሣኔ የሚሰጡበት ነፃነት እንዲኖራቸው ማድረግ ይኖርበታል።

የተባበሩት መንግሥታት በተለይ በማደግ ላይ ባሉ አገሮች በተመሣሣይ ሁኔታ የሚሠራ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ሊያዘጋጅ ሞክሮ እስከአሁን አልተሣካለትም። ምክንያቱም በየአገሮቹ ያለው ታሪካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ፣ የመሬቱ አቀማመጥና የአየሩ ጠባይ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት፣... ወዘተ ልዩነቶች ናቸው።

በመሆኑም እያንዳንዱ አገር በራሱ አገር ካለው ሁኔታ ጋር በማስተያየት የራሱን ሕግና ደንብ መቅረፅ ይኖርበታል።

## 6.1 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሕግ ይዘት

የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሕግና ደንብ ይዘት ከላይ በጥቂቱ የተጠቆመ ቢሆንም ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር ቀርቧል፡፡ ሕጉ በእያንዳንዱ አርዕስት አፈፃፀም ላይ በዚህ ዶክሜንት በተገለፀውና በተሻሻለ መንገድ ዘርዘር ያለ ሕግና ደንብ መደንገግ ይኖርበታል፡፡ የምዝገባው ሥርዓትም በሕጉ በተደነገገው መሠረት ተግባሩን ማከናወን አለበት፡፡

1- የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ትርጉም፣
2- የሚመዘገቡ የወሳኝ ኩነቶች ዓይነትና ትርጉም፣
3- የምዝገባ ጥቅምና ዓላማ፣
4- የአስመዝጋቢና የመዝጋቢ ኃላፊነትና ተግባር፣
5- የምዝገባ የጊዜ ገደብ፣
6- የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አፈጻጸም፣
7- የወሳኝ ኩነቶች ስለመከናወናቸው የሚቀርብ ማረጋገጫ፣
8- የምዝገባ ቦታ፣
9- የምዝገባ ዶክመንቶች ይዘትና ቅርጽ፣
10- የምስክር ወረቀቶች ማስረጃነት፣
11- የመዝገቦችና የሰርተፊኬቶች ይዘት፣
12- በሕግ ስለመገደድ፣
13- ቅጣት
14- የምዝገባ ዶክመንቶች አያያዝ፣ አስተላለፍ፣
15- የዶክመንቶች ሚስጥራዊነት፣
16- የሰው ኃይልና ስልጠና፣
17- ሕበረተሰቡን ስለማስተማርና መቀስቀስ፣

18- በጀት፡
19- የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤት ኃላፊነትና ተግባር፡
20- የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ ጽ/ቤት ኃላፊነትና ተግባር፡
21- የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ጽ/ቤቶችን የሚያስተዳድሩ ድርጅቶች ኃላፊነትና ተግባር፡
22- የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ አስተባባሪ ኮሚቴ ኃላፊነትና ተግባር፡
23- የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ተባባሪ ድርጅቶች ኃላፊነትና ተግባር፡
24- የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ስታትስቲክስ ስርዓት ድርጅታዊ አወቃቀር፡

## 6.2 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና አገራዊና አለም አቀፍ ሕጎች

### 6.2.1 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ሰብዓዊ መብቶች

ሕጋዊ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ተግባር ሕጋዊ ሰርቲፊኬት ለግለሰቦች መስጠት ነው:: ሕጋዊ ሴርቲፊኬት ግለሰቦች ሰብዓዊ መብታቸው ተከብሮ ሕይወታቸውን በተረጋጋና በሰላም እንዲመሩ ያስችላቸዋል:: ከሕጋዊ ሴርቲፊኬት የሚመነጨው ጥቅም ግለሰቦችና ህበረተሰቡ ለምዝገባው ከፍተኛ ትብብር እንዲያደርጉ ይገፋፋቸዋል::

የልደት፡ የሞት፡ የጋብቻና የፍቺ፡ ምዝገባ ማካሄድ በመሠረቱ የግለሰቦችን ሰብዓዊ መብትን ለመጠበቅና የህብረተሰቡ አካል መሆናቸውን ለማመልከት ነው:: ለግለሰቦች የሚሰጡት

የልደት፣ የሞት የጋብቻና የፍቺ ሕጋዊ ሴርቲፊኬቶች ግለሰቦች በየቀኑ ከሌላ ግለሰብ፣ ድርጅትና መንግሥታዊ ተቋም ጋር በሚያደርጉት ግኑኝነት እንደ ሕጋዊ መረጃ በመሆን ያገለግላሉ:: በመሆኑም ብዙዎችን የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ያገለግላሉ::

በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና በሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ መካከል ያለው ግኑኝነት ጐልቶ ሊታይ የቻለው ዓለም አቀፉ ኮንቬናንት በሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ላይ በ1974 ዓ.ም ባስተላለፋቸው ውሳኔዎች ነበር:: ለምሳሌ አንድ ሕፃን እንደተወለደ ወዲያውኑ መመዝገብ አለበት፣ ስምም ማግኘት አለበት፣ ማንኛውም ጋብቻ መመዝገብ አለበት የሚሉና የመሣሠሉ ናቸው:: ይህ በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና በሰብዓዊ መብቶች መካከል ያለው ግኑኝነት የተባበሩት መንግሥታት World Population Plan of Action ስብሰባ ላይ በሁለት እንዲከፈል ተደርጓል:: እነዚህም በእያንዳንዱ አገር የመመዝገብ መብት ያላቸውና በተመዘገቡ የወሳኝ ኩነቶች አማካይነት ተፈጻሚ የሚሆኑ ስብዓዊ መብቶች ተብለው ተከፋፍለዋል::

በእያንዳንዱ አገር የመመዝገብ መብት ያላቸው የወሳኝ ኩነቶች ልደት፣ ሞት ጋብቻና ፍቺ ሲሆኑ እያንዳንዱ አገር በአለም አቀፋዊው የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ መሠረት እነዚህን የመመዝገብ ግዴታ አለበት:: እያንዳንዱም የወሳኝ ኩነት የመመዝገብ መብት አለው::

የልደት መመዝገብ ሕጋዊ ማረጋገጫ ከማስገኘቱም ባሻገር ከልደቱ ጋር አብሮ የተመዘገቡት የሕፃኑን ማንነት፣ ስሙ፣ ወላጆቹን፣ የልደት ቀኑን፣ የተወለደበትን ቦታ መረጃዎች በአንድነት የአንድን ግለሰብ ሰብዓዊ መብት መከበሪያ ወይም መጠበቂያ አስፈላጊ መሣሪያዎች ናቸው:: እነዚህን ሰብዓዊ

መብቶች ለመጠበቅ እያንዳንዱ አገር አንድ ሕፃን እንደተወለደ ወዲያውኑ የማስመዝገብ ግዴታ አለበት።

የሞት መመዝገብ መብት በሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ በቀጥታ ባይሠፍርም በተዘዋዋሪ መንገድ ሠፍሮ ይገኛል። ለምሣሌ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ድንጋጌዎች ውስጥ የአንድ አገር ጤናማ እድገት ሙሉ በሙሉ እንዲሣካ አገሮች ዕድሜአቸው ከአንድ ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት ሞት የሚቀነስበትን ሁኔታ መፍጠር/ማመቻቸት እንዳለባቸው ይደነግጋል። ይህን ድንጋጌ ተግባራዊ ለማድረግ የሞት መረጃ ያስፈልጋል። የሞት መመዝገብ የሕፃናትንና የአዋቂዎችን ሞት ብዛት መረጃ ይሰጣል። እንዲሁም የመውረስ መብት፣ የማህበራዊ ደህንነት ጥበቃ መብት፣ የኢንሹራንስ ማግኘት መብትና የድጋሚ ጋብቻ መብቶች ከምዝገባው በሚገኘው ሴርቲፊኬት መሠረት ተፈፃሚ ይሆናሉ።

የጋብቻ መመዝገብ መብት እንደዚሁ በሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ ውስጥ በቀጥታ የገባ ባይሆንም ለሌሎች መብቶች ጥበቃና ተፈፃሚነት እንደ አንድ አስፈላጊ መረጃ በመሆን ያገለግላል። ለምሣሌ ጋብቻና የመጨረሻው ትንሹ የጋብቻ ዕድሜ የሚወሰነው ሥልጣን በተሰጠው አካል መሆን እንዳለባቸው ይጠቅሣል። የተባበሩት መንግሥታት የሴቶችን ሁኔታ አስመልክቶ በአዲሶቹና ባረጁ ሕጐችና ባህሎች ምክንያት የተነሣ የሚደርስባቸውን የሰብአዊ መብት ገፈፋ ለማስወገድ ሁሉም ጋብቻዎች መመዝገብ እንዳለባቸው ይደነግጋል። በተጨማሪም ትንሹ የጋብቻ ዕድሜንና ጋብቻው የሚመዘገብበትን ሁኔታ የሚወስን ሕግ እያንዳንዱ አገር እንዲደነግግ ይጠይቃል። ጋብቻ ሲመዘገብ የሁለቱም ተጋቢዎች ስም፣ ዕድሜ፣ የቀድሞ የጋብቻ ሁኔታ፣ ሥራ፣ የጋብቻ ቦታ፣ የጋብቻ ማረጋገጫ የሚመለከት መረጃ መመዝገብ እንዳለበት ይጠቅሣል።

የተባበሩት መንግሥታት የሴቶችን ሁኔታ አስመልክቶ በጠቅላላ ስብሰባ ቁጥር 843(1X) 1954 በወሰነው መሠረት እያንዳንዱ መንግሥት የፍችን ምዝገባ እንዲያካሂድ ይጠይቃል። በተመሣሣይ ሁኔታ በሌላ መድረክ በተላለፈው ውሣኔ ፍች ወይም ሕጋዊ መለያየት የሚፈቀደው በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል እንደሚሆንና ፍቹም መመዝገብና የምስክር ወረቀት እንዲኖረው ይጠይቃል።

ፍቺ የሚወሰነው በፍርድ ቤቶች ውሣኔ ነው። የፍርድ ቤትን ውሣኔ የያዘ ዶክሜንት ለፍቺው መፈፀም ማረጋገጫ ነው። ዶክሜንቱም በፍርድ ቤቶች መዝገብ ቤት ይቀመጣል። መረጃውንም የፈለገ ከፍርድ ቤቶች መዝገብ ቤት ግልባጭ (ኮፒ) ሊወስድ ይችላል። የፍቺ ምዝገባን በተመለከተ ግን ፍርድ ቤቶች የፍርዱን ውሣኔ ኮፒ ለምዝገባ ጽ/ቤቶች እንዲላኩ የሚደነገግ ሕግ ከሌለ አይልኩም። በመሆኑም ፍችው ሣይመዘገብ እንዳይቀር ይህንን የሚመለከት ሕግ መደንገግ አለበት። ከፍቺ ምዝገባ የሚገኘው መብት ደግሞ የማግባት መብት፣ የልጆች ጥበቃ መብት የመሣሠሉት ናቸው።

ከላይ የተዘረዘሩት ኩነቶች የመመዝገብ ግዴታና መብት ያላቸው ሲሆኑ በነዚህ በተመዘገቡት አማካይነት ተፈጻሚ የሚሆኑ ስብዓዊ መብቶች አሉ። እነዚህም የተባበሩት መንግሥታት «ሁለተኛው ቡድን ሰብዓዊ መብቶች» ብሎ የሚጠራቸው ናቸው። እነዚህም ቀጥሎ የተዘረዘሩት ናቸው።

1. ስም የማግኘት መብት
2. ወላጆችን የማወቅ መብት
3. የዜግነት- መብት
4. የጤና ጥበቃ አገልግሎት የማግኘት መብት
5. የቤተሰብ ጥበቃ ማግኘት መብት

6. የወጣት አጥፊዎች መብት
7. ትምህርት የማግኘት መብት
8. የጋብቻ መብት
9.ከግዴታ ጋብቻ የመጠበቅ- መብት
10. ምግብ የማግኘት-መብት
11. ልብስ የማግኘት-መብት
12. ቤት የማግኘት-መብት
13. ሥራ የማግኘት- መብት
14. ንብረት የመመሥረት- መብት
15. የመውረስ-መብት
16. የመፍለስ-መብት
17. የጡረታ- መብት
18. ሕፃናት የማሣደግ-መብት
19. የመምረጥና የመመረጥ- መብት

እነዚህ መብቶች የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻና የፍች ምዝገባ ሲካሄድ ተፈፃሚ ይሆናሉ። ለምሣሌ ስም የማግኘት መብት፣ የዜግነት መብት፣ የወጣት አጥፊዎች መብት፣ የትምህርት ማግኘት መብት፣ የጋብቻ መብት፣ የምግብ ማግኘት መብት፣ የልብስ ማግኘት መብት፣ ቤት የማግኘት መብት፣ሥራ የማግኘት መብት፣ ንብረት የማፍራት መብት፣ የመመውረስ መብት፣ የመምረጥና የመመረጥ መብት ከልደት ምዝገባ በሚገኘው ሕጋዊ ሰርቲፊኬት ተፈፃሚ የሚሆኑ ናቸው። እንዲሁም የጡረታ መጠበቅ መብት፣ የልጆች ማሣደግ መብት፣ ከሞት ምዝገባ በሚገኘው ሕጋዊ ሰርቲፊኬት ተፈፃሚ ይሆናሉ። ሌላው የቤተሰብ ጥበቃና አስገድዶ ማግባትን የመከላከል መብት የሚገኘው ከጋብቻ ምዝገባ ነው።

ኢትዮጵያ አለም አቀፍ ሰብአዊ መብት ጥበቃ ሕጎችን በመቀበል ከፈረሙት አገሮች አንዷዋ ነች። ሕጉን ተግባራዊ ለማድረግ አገር አቀፍ ሕጎችንና ደንቦችን በማውጣት ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት በማድረግ ላይ ትገኛለች።

ሆኖም ሕጎችንና ደንቦችን ማውጣት ብቻ በቂ አይደለም። አስተዳደራዊ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል። ከአስተዳደራዊ እርምጃዎች አንዱ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ተቋም ማቋቋምና ምዝገባ ማካሄድ ነው። ሌላው መመዝገብና ማስመዝገብ ግዴታና መብት መሆኑን በሕግና ደንብ ማረጋገጥና ማስፈጸም ያስፈልጋል።

የመመዝገብና የማስመዝገብ መብትና ግዴታ እስካልተከበረ ድረስ አንዱ የሰብአዊ መብት ክፍል አልተፈፀመም ማለት ነው። ይኸም ግለሰቦች የልደት፣ የሞትን የጋብቻንና የፍችን መከናወን ማረጋገጫ ጽሁፍ (ሴርቲፊኬት) እስካልያዙ ድረስ መብታቸውን ማስከበርና ግዴታቸውን መፈፀም አይችሉም።

### 6.2.2 የ1952 ዓ.ም ፍትሐ ብሔር ሕግ

የ1952 ዓ.ም የፍትሐብሔር ሕግ ከተደነገገ ወደ 39 ዓመቱ ነው። ሕጉ ስለቤተሰብ በደነገገው ሕግ ውስጥ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ እንዲካሄድ በዝርዝር የሚያስፈፀሚያ ደንቦችን አስቀምጧል። ሕጉ ምንም እንኳን በወቅቱ ካለው የአስተዳደር ሥርዓት፣ ከአመለካከት፣ ከኤኮኖሚና ከማህበራዊ እድገት ደረጃ ጋር የሚጣጣም ቢሆንም ተግርባራዊ ሣይሆን ቆይቷል።

በፍትሐብሔሩ ሕግ በምዕራፍ 3 ቁጥር 74 እያንዳንዱ ቀበሌና ቆንስላ የልደት፣ የሞትና የጋብቻ መዝገቦች እንደሚኖራቸው ተገልጿል። ስለ ልደት ምዝገባ ከሚጠቀሱት አንቀጾች መካከል በምዕራፍ 2 በቁጥር 37 ልጁ በተወለደበት ቀበሌ ለሚገኘው የክብር መዝገብ ጽሕፈት ቤት ሹም «ልጁ ከተወለደበት ቀን አንስቶ ባለው ተከታታይ ዘጠና ቀናት ውስጥ ለተወለደው ልጅ የተሰጠውን የግል ስም መገለጽ አለበት» ይላል።

ምዕራፍ 3 ቁጥር 100 እና 101 ደግሞ « ልጁ 48 ሰዓት ከኖረና የመወለድ ጽሑፉን ለማስመዝገብ የተመለከተው ጊዜ ከማለቁ በፊት ቢሞትም እንኳ መወለዱን ማስታወቅና የመወለዱን ጽሑፍ ማዘጋጀት አስፈላጊዎች መሆናቸውን ተገልጾ» የልጁን መወለድ ማናቸውም ሰው ለክብር መዝገብ ኃላፊ መግለፅ « እንዳለበትና ይህም የልጁ አባት፣ አባቱ የሌለ ቢሆን የልጁ እናት ወይም አሳዳጊ፣ እነዚህም ባይኖሩ ልጁን አግኝቶ ያነሳው ሰው ሊገልጽ ይገባዋል» ይልና «የክብር መዝገብ ኃላፊው የልጁን መወለድ ካወቀ በራሱ ስልጣን የልጁን መወለድ ለመመዝገብ ይችላል» ይላል። እንዲሁም በምዕራፍ 3 ቁጥር 104 እስከ 116 በየቀበሌው የሞተውን ሰው ስለመመዝገብ በምዕራፍ 3 ቁጥር 117 እስከ 120 ደግሞ ጋብቻን ስለማስመዝገብ ግዴታዎች ተዘርዝረዋል።

በፍትሐብሔሩ እንደተጠቀሰው የምዝገባው ይዘትና ዓላማ ለእያንዳንዱ ዜጋ ሕጋዊ መብቱን ለማስከበር የተደነገገ ሆኖ እናገኘዋለን። ነገር ግን ፍትሐብሔሩ ለሕብረተሰቡ የሶሻልና የኢኮኖሚ ልማት ለማቀድ የሚረዱ መረጃዎች መመዝገብ እንዳለባቸው አይገልጽም። ሕጉ የተጠቀሱትን ክንውኖች ሁሉ በማያወላውል ሁኔታ መመዝገብ እንዳለባቸው ካለማስገደዱም በላይ በሕግ የተጠቀሱትን ክንውኖች ምዝገባ ለማስጀመርና ሕጉንም ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስችልና ራሱን በራሱ ተፈጻሚ የሚያደርግበት መመሪያ የለውም። በመሆኑም እስከ አሁን በሚመለከተው አስተዳደር በኩል የተወሰዱ እርምጃዎች የሉም። ሕጉ ብዙዎችን የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አካል የሆኑ አሠራሮችን የጠቀሰ ቢሆንም በአብዛኛው ከወቅቱ ጋር የማይሄዱ ድንጋጌዎችን ይዞ ይገኛል። በመሆኑም ሕጉ እንደገና ከወቅቱ አስተዳደራዊ መዋቅር፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት ጋር የሚጣጣም ሆኖ መሻሻል አለበት። የሕጉ ይዘት በዚህ ዶክሜንት የተዘረዘሩትን

የአፈጻፀምና የፅንስ ሃሣብ ሁኔታዎችን የያዘ ሆኖ መዘጋጀት አለበት።

### 6.2.3 ሕገ መንግሥትና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ

ሁሉም ሕጐች በእኩል ደረጃ አስገዳጆች ናቸው። ነገር ግን ሁሉም ሕጐች በደረጃ እኩል አይደሉም። ከሁሉም ሕጐች በደረጃ የበላይ የሆነው የአገሪቱ ሕገ መንግሥት ነው። ይህ ሕግ የዜጐችን መብት ለማስጠበቅ፣ አስተዳደራዊና ሕጋዊ እንቅስቃሴዎች በተገቢው መንገድ እንዲከናወኑ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት እንዲፋጠን... ወዘተ ተብሎ የተዘጋጀ ሕግ ነው።

ሕገ መንግሥቱ ቀደም ብሎ የተጠቀሱትን ሰብዓዊ መብቶችን ተቀብሎ ለተፈጻሚነታቸውም ተገቢውን መመሪያ በውስጡ አስፍሯል። ሕገ መንግሥቱ ምንም እንኳን የግለሰቦች ሰብዓዊ ማንነት የሚገልፁ መረጃዎች የሚገኙበትን ምንጭ ባይጠቅስም በሕገ መንግሥቱ የሰፈሩትን ሕጐች ተፈጻሚ ለማድረግ ደንብ እንደሚዘጋጅ ግልጽ አድርጓል። በሚዘጋጀው ደንብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባም እንዲቋቋም እንደሚጠቀስ ይጠበቃል። የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሕግ ከሕገ መንግሥቱና ከደንቦች ጋር የሚጣጣምና የሕገ መንግሥቱን ዓላማ ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያገለግል መረጃ የሚገኝበትን ሥርዓት እንደሚመሠርት ይጠበቃል።

### 6.2.4 የቤተሰብ ሕግና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ

የቤተሰብ ሕግ ዓላማው የቤተሰብ ጥበቃን፣ በተጋቢዎች ሙሉ ፈቃድና ነፃነት ላይ የተመሠረተ ጋብቻ የሚፈፀምበትን፣ የሕፃናት መብትን፣ የሴቶች መብትን... ወዘተ በሰብዓዊ መብቶችና በሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ መሠረት ለማስፈፀም

ተብሎ ከ1952 ዓ.ም ፍታብሔር ሕግ ውስጥ ለቤተሰብ የተደነገገውን በማሻሻል የሚዘጋጅ ነው::

የሚሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ ተፈጻሚ ለማድረግ ከምዝገባ የሚገኘው መረጃ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል:: በመሆኑም ሕጉን ለማሻሻል በተደረገው ስብሰባ የምዝገባ ጽህፈት ቤት እንዲቋቋም ተወስኗል:: በሚሻሻለው ሕግም ጋብቻን አስመልክቶ የምዝገባ ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም መዝጋቢ (የክብር መዝገብ ሹም) ከፍተኛ ኃላፊነት ተሰጥቶታል:: የቤተሰብና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሕግ በአንድነት የምዝገባው ሥርዓት እንዲሣካ እንደሚያደርጉ ይታመናል::

## 6.3 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሕግን ማን ያውጣ ?

በኢትዮጵያ የሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ያልተማከለ እንደሚሆን ቀደም ብሎ ተጠቅሷል:: በዚህ መሠረት እያንዳንዱ ክልል የራሱን የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ በኃላፊነት ያካሂዳል::

በፌዴራል አስተዳደር ሥርዓትና በሕገ መንግሥቱ መሠረት ሕጉን የማውጣት ሥልጣን የእያንዳንዱ ክልል ሕግ አውጭ አካል ይሆናል:: ነገር ግን የምዝገባ ሕግን የማውጣት ሥልጣን ለፌዴራል መንግሥት ሕግ አውጭ ባልተሰጠበት የፌዴራል ሥርዓት የሚከተሉት ጥያቄዎች ይነሣሉ::

1. በሀገሩ ሕገ መንግሥት ሥርዓት መሠረት ሕጉን የማውጣት ሥልጣን የክልል ሕግ አውጭ አካል ነው በሚል ብቻ የፌዴራሉ አካላት የየራሳቸውን የተለያዩ የምዝገባ ሕጎች ማውጣት አለባቸው?

2. ተመሣሣይነት ያለውና ለሁሉም በጋራ የሚያገለግል የምዝገባ ሕግ በፌደራሉ ሕግ አውጭ ይውጣ?

### ሀ. የተለያዩ ሕጎችን የማውጣት አማራጭ

እያንዳንዱ ክልል የራሱን ሕግ ቢያወጣ ተመሣሣይነት የሌላቸው 11 ሕጎች ይኖራሉ። ከሌሎች ክልሎችና እንዲሁም ከጠቅላላው የሀገሪቱ የጋራ አመለካከቶች ጋር ያልተገናዘቡ፣ ያልተጣጣሙ ወይም ያልተስተካከሉ የምዝገባ ሕጎች ይኖራሉ። ይህ ደግሞ በቦታዎችና በሕዝቦች መካከል ሊኖርና ሊጠናከር ይገባል በሚባለው የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ፣ የፖለቲካና ባህላዊ ግንኙነቶች ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ከማስከተሉም በላይ ውስብስብ የሕጎች ግጭትን(Conflict of Laws) ይፈጥራል። የተለያዩ የምዝገባ ሕጎች በሥራ ላይ በሚውሉበት ጊዜ በአንድ ክልል የምዝገባ ሕግ መሠረት የተመዘገበ ኩነት የተለየ የምዝገባ ሕግ ባለው ሌላ ክልል ተፈጻሚ ለማድረግ አስቸጋሪ ይሆናል። ለምሳሌ ሁለት ተጋቢዎች በአንድ ክልል የምዝገባ ሕግ መሠረት ከተጋቡ በኋላ ወደ ሌላ ክልል መኖሪያቸውን ያዛውራሉ እንበል፣ በዚህ ጊዜ በአንደኛው ክልል የተሰጠው ሕጋዊ የጋብቻ ሰርቲፊኬት በሌላው ክልል ተቀባይነት የማግኘት ሁኔታ አጠያያቂ ይሆናል። ምክንያቱም በሕጎች መለያየት ምክንያት ጽንሰ ሃሣቦች፣ ትርጉሞች፣ ደንቦችና አፈጻጸማቸው የተለያዩ ስለሚሆን ነው። በሕጎች መለያየትና መብዛት ሳቢያ ግለሰቦች መብቶቻቸውንና ግዴታቸውን በውል ጠንቅቀው ማወቅ በጣም አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል።

### ለ. ተመሣሣይ ሕግ የማውጣት አማራጭ

በጋራ ለመጠቀም የሚያገለግሉ ተመሣሣይ ሕጎች ማውጣት ለሕዝቦች መቀራረብ መሠረት ነው። አስተማማኝ ያልሆነ

ሁኔታ፤ መደነጋገርንና ምስቅልቅል ሁኔታን ያስወግዳል። ተመሣሣይ ሕጐች መኖር የአሀዳዊና የፌደራል መንግሥት ሥርዓትን በሚከተሉ አገሮች ሁሉ ድጋፍ አለው። የተለያዩ ሕዝቦች ፍላጐት በጋራ ለማስተናገድ ያስችላል። ተመሣሣይ ጽንሰ ሃሣቦችና ፍችዎች እንዲኖሩ ያደርጋል።

ተመሣሣይ ባህሪ ያላቸው አማራጭ ሕጐች

1. በፌደራል መንግሥት የተዘጋጀውን በሞደልነት መጠቀም።
2. በስምምነት ተመሣሣይነት ያለው ሕግ ማዘጋጀት።
3. የፌደራል መንግሥት ያዘጋጀውን በጋራ መጠቀም።

1. ሞደል ሕግ መጠቀም

የፌደራል መንግሥት ሕጉን ያዘጋጃል። በፌደራል መንግሥት በተዘጋጀው ሕግ ላይ እያንዳንዱ ክልል በክልል ምክር ቤት ውይይት ከተደረገበት በኋላ አስፈላጊውን ለውጥ በማድረግና በማጽደቅ እንደሚገኘውም የክልሉ ሕግ በክልሉ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣና በሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ ነው።

2. በስምምነት ተመሣሣይ ሕግ ማውጣት

በዚህ አማራጭ መሠረት የሚዘጋጀው ተመሣሣይ ሕግ በክልሎች ስምምነት መሠረት የሚዘጋጁ ሕግ ነው። ክልሎች እንዲሁም የፌደራል መንግሥት በአገር አቀፍ ደረጃ ተፈፃሚነት ሊሰጠው በሚገባው ሕግ-ረቂቅ ውይይት አድርገው ከተስማሙበትና ከፈረሙበት በኋላ ያህንኑ ሕግ ለምክር ቤቶቻቸው በማቅረብ እንዲፀድቅ

ያደርጉታል፡፡ከዚያም በየክልሉና በፌደራል መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ ማድረግ ነው፡፡

### 3. በፌደራል መንግሥት የወጣን ሕግ በጋራ መጠቀም

ሌላው ተመሣሣይ ሕግን የማዘጋጀት አማራጭ የፌደራል መንግሥት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕጉን እንዲያወጣ ሲደረግ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የሕዝብ ተወካዩች ምክር ቤት የፌደራሉን ሕገ መንግሥት መሠረታዊ መርሆዎችን በሚያከብር መልክ ሕጉን አዘጋጅቶ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ እንዲታተም ከአደረገ በኋላ በየክልሉ ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡

### ኢትዮጵያ የትኛውን አማራጭ ትከተል? ለምን ?

በኢትዮጵያ የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት መርሆዎችን እስካልተቃረነ ድረስ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት ሕግ ለሁሉም በጋራ ሊያገለግል የሚችል ሕግ ቢወጣ የተሻለ ይሆናል፡፡ ይህን የመሰለ የጋራ ባህሪ ያለው ሕግ ለአፈጻጸም ምቹ ከመሆኑም ባሻገር በኢኮኖሚ፣ በሶሻልና በፖለቲካ መስኮች ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

ሆኖም በሕገ መንግሥቱ የተካተቱትን ልዩ ልዩ መርሆዎች ማክበር የግድ ከሆነ ሕጉን ለማመሣሠል ከተጠቆሙት ሦስት አማራጮች መካከል የፌደራል መንግሥት ያዘጋጀውን ሕግ እያንዳንዱ ክልል በሞዴልነት ቢጠቀም ከሌሎች አማራጮች የተሻለ ይሆናል፡፡ በዚህ መሠረት በፌደራሉ መንግሥት ሕግ ከውጪ አካል የወጣውን ሕግ የክልል ምክር ቤቶች ተወያይተውበትና አስፈላጊውን ለውጥ በማድረግ ሊያፀድቁ ይችላሉ፡፡ ይህም አሠራር ከኢፌዲሪ ሆነ ከክልል ሕግጋተ መንግሥት መርሆዎች ጋር የተጣጣመ ይሆናል፡፡

# *Bibliography*


1. IIVRS: Technical Paper on the Organizational and Vital Statistics Systems: Vito. Logrillo, 9650 Rockville Pike Bethesda, MD 20814-3998; U.S.A.

2. IIVRS: Civil Registration and Vital Statistics: A Collection of Papers, UNFPA

3. IIVRS: Improving Civil Registration, Editors. Forrest E. Linder and Iwao M. Moriyama 9650 Rockville Pike Bethesda, MD 20814-3998 U.S.A

4. Eli S. Marks et.al: Population Growth Estimation, A Hand Book of Vital Statistics Measurement, The population Council , New York

5. Benjamin Gil: The Kenya Civil Registration Demonstration Project. A Strategy for a Rapidly Developing Country in Africa, Published by the Department of the Registrar General.of Kenya

6. The Government of Kenya and UNFPA: Training of Registration Informants, A Guide for Diffusion 7 Instructor, Department of the Registrar General, Nairobi, 1982

7. Eurostat: Denmarks Statistic, Statistics on Persons in Denmark; A Register-based Statistical System

8. ECA: Working Group on Registration Systems and Vital Statistics Collection in Africa , Nairobi, 21-25 July 1980 Review of the Status and Problems of the Civil Registration Systems in Africa, ECA/STAT/WG.VS/5, 2 June 1980

9. IIVRS: Chronicle, Number 91, November 1993

10. IIVRS: Chronicle, Number 18, April 1981

11. IIVRS: Chronicle, Number 99, July 1995

12. IIVRS: Chronicle, Number 94, June 1994

13. ECA: Working Group on Civil Registration Systems and Vital Statistics Collection in Africa, Nairobi, 21-25 July 1980 Collection,

Processing, Evaluation, Analysis, Publication and Dissemination of Vital Registration information ECA/STAT/WG.VS/7, 15 May 1980

14. ECA: Working Group on Civil Registration Systems and Vital Statistics Collection in Africa, Nairobi, 21-25 July 1980 Review of Methods of Obtaining Vital Statistics Information ECA/STAT/WG.VS/4, 5 May 1980

15. DESA: Statistics Division. ST/STAT/SER.F/71, Hand book on Civil Registration and Vital Statistics Systems, Preparation of a Legal Framework, Series F, No. 71, United Nations, New York, 1998

16. CSA 1995: Population Analysis and Studies Center (PASC), Report on Experimental Sample Vital Registration System in Rural Ethiopia 1986/87

17. CSA 1990: Population Analysis and Studies Center (PASC), Report on Experimental Sample Vital Registration System in Rural Ethiopia Volume I, The Analysis of Vital Events

18. SOUN: Department of Economic and Social Affairs, Studies in Methods Series F No. 7, New York; April 1955

19. DESA: Statistical Office of the United Nations, Statistical Papers, Principles and Recommendations for a Vital Statistics System , United Nations, New York, 1973

20. DESA: Statistical Office, Studies in Methods ...Series F No 35, Handbook of Vital Statistics Systems and Methods, Volume 1: Legal, Organizational and Technical Aspects; United Nations , New York, 1991

21. DESA: Statistical Office of the United Nations , Statistical Papers ...Series M No. 19, Rev.1, Principles and Recommendations for a Vital Statistics System, United Nations, New York, 1973

22. CSA: A Note on the Status of Vital Statistics Registration Activities in Hospitals, Municipality and Religious Institutions in Addis Ababa , July 1981

23.CSA: 1992: Population Analysis and Studies Center (PASC), Report on Experimental Vital Registration System (ESVRS) in Rural Ethiopia, Volume II; The Analysis of Local Moves and Internal Migration

24. የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት: 1952, የፍትሐ ብሔር ሕግ, ነጋሪት ጋዜጣ ቁ.1 /1952 ዓ.ም. በተለይ የወጣ. አዲስ አበባ

25. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ: 1987 የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ:ህገ መንግሥት.

## Notes:-

IIVRS- International Institute for Vital Registration and Statistics
ECA- Economic Commission for Africa
DESA- Department of Economic and Social Affairs
SOUN-Statistical Office of the United Nations
CSA-Central Statistical Office